# ትምህርት አሥራ አንድ

ኢሳይያስ 28–33

**የመጀመሪያ ቀን** ኢሳይያስ 28–29

1ኛ ጥያቄ፡– መንፈስ ቅዱስ በጎጢአት ውስጥ እየተመላለስህ ሳለ ወቀሰህ እንበል። ሀ) በኢሳይያስ 28–29 መሠረት፥ ስለተሳሳተ አመለካከትህ ማስጠንቀቂያ የሚሰጡህ አንዳንድ ዐበይት መንፈሳዊ መርሆዎች የትኞቹ ናቸው? ለ) ንስሐ እንገባ ዘንድ ለማበረታታት እግዚአብሔር የሚሰጠን አንዳንድ የተስፋ ቃሎች ምንድን ናቸው? ሐ) በእነዚህ ሁለት ምዕራፎች ውስጥ የሚገኙና ለቤተ ክርስቲያንህ አባላት ልታስተምራቸው የሚገቡ አንዳንድ ጠቃሚ ትምህርቶች የትኞቹ ናቸው?

ከመንፈስ ቅዱስ ዐበይት አገልግሎቶች አንዱ ጎጢአት በምንሠራበት ጊዜ መውቀስና ወደ ንስሐ መምራት ነው። እግዚአብሔር ንጉሥ ዳዊት ከቤርሳቤህ ጋር ስለፈጸመው ጎጢአት ለመጋፈጥ ነቢዩ ናታንን እንደላከው፥ ዛሬም እኛኑ በመውቀስና በመመለስ ላይ ይገኛል። መንፈስ ቅዱስ በሚናገርበት ጊዜ እኛ የምንሰጠው ምላሽ ወሳኝ ነው። ተገቢ ባልሆነ መንገድ ምላሽ ከሰጠን ልባችን ይደነድናል፤ መንፈሳዊ ዕድገታችን ይታቀባል፤ ብሎም መንፈሳዊ ውድቀታችን ይጀምራል። ይህም የእግዚአብሔርን የከፋ ቅጣት የሚያስከትል ይሆናል። ይሁንና፥ ራሳችንን ዝቅ አድርገን ንስሐ ከገባን ወዲያውኑ ወደ ቀደመው ሰፍራችን እንመለሳለን። ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነትም ይቀጥላል፤ ያድጋልም።

ሕዝበ እስራኤል (ኤፍሬም) እና ይሁዳ (አርኤል) በእግዚአብሔር ፊት ጎጢአትን ፈጽመው ነበር። እግዚአብሔር በነቢያቱ አማካኝነት ስለ ጎጢአታቸው አጋፈጣቸው። የሚያሳዝነው ግን ሁለቱም አገሮች ለእግዚአብሔር የማጋፈጥ ተግባር የሰጡት ምላሽ የተሳሳተ ነበር። በነቢያቱ ላይ እየተሳለቁ፥ ኢሳይያስ እንደ ሕጻን ልጅ ጣእም የሌላቸውን ቃላት የሚደጋግም እንደሆነ መናገር ያዙ (28፡10)። «ከሞት» ጋር ቃል ኪዳን ስለተጋቡ፥ እግዚአብሔር ሊነካቸው እንደማይችል ተናገሩ (28፡15)። ከዚህም የተነሣ መንፈሳዊ መረዳታቸውን አጡ (29፡9–10)። ወዲያውም አምልኮ በእግዚአብሔር መንፈስ ፈንታ የሰዎች ሕግጋት የተካተቱበት ትርጉም–አልባ ተግባር ሆነ (29፡13)። አእምሮአቸው ስለጨለመ እግዚአብሔር እንደማያያቸው ወይም ስለሚያደርጉት ነገር ግድ እንደሌለው አድርገው አሰቡ (29፡15–16)።

2ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አንድ ክርስቲያን ስለ ጎጢአቱ ተጋፍጦ ንስሐ ለመግባት ባለመፍቀድ እንዲህ ያለ የተሳሳተ ምላሽ ስለሰጠበት ሁኔታ ግለጽ። ለ) ብዙ ክርስቲያኖች ራሳቸውን ዝቅ አድርገው ጎጢአት መሥራታቸውን አምነው ለመቀበልና ንስሐ ለመግባት የማይፈልጉት ለምን ይመስልሃል?

አንድ ሰው በኃጢአት በሚጋፈጥበት ጊዜ ንስሐ በመግባት፥ ተግባራቱን በመለወጥና የእግዚአብሔርን መንገዶች በመከተል ትክክለኛውን ምላሽ መስጠቱ እንዴት የተለየ ነገር ነው! ከሁኔታዎች ባሻገር፥ ለእንዲህ ዓይነቱ ሰው እግዚአብሔር አክሊልና የብርታት ምንጭ ይሆነዋል (28፡5)። እግዚአብሔር የሕይወቱ መሠረት ስለሆነ ከቶውንም አያፍርም (28፡16)። አይሁዶች ጠላት ሲያጠቃቸው፥ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን እንዲያሸንፉ ይረዳቸዋል (29፡5–8)። ጽልመት በነገሠባቸው ጊዜያት ሳይቀር መንፈሳዊ ግንዛቤ ይኖራቸዋል (29፡24)።

3ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እግዚአብሔር ንስሐ የሚገቡትን ሰዎች ለመባረክ ቃል ከገባ፥ መንፈስ ቅዱስ በሚወቅስበት ጊዜ በፍጥነት ንስሐ መግባቱ እጅግ ከባድ የሚሆነው ለምንድን ነው? ለ) ከመንፈስ ቅዱስ ጋር መዋጋቱን ትተህ ንስሐ በገባህ ጊዜ የእግዚአብሔር አስደናቂ ምሕረት በሕይወትህ ሲፈስ ያየኸው እንዴት ነው?

## ኢሳይያስ 28

4ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ ምዕራፍ 28ን አንብብ። (ሀ) ኢሳይያስ በቁጥር 1 የሚናገረው አክሊል ምንድን ነው? ኤፍሬም የትኛው አገር ነው? (ለ) እግዚአብሔር በከተማዪቱ ላይ ምን ያመጣል? ስለ የትኛዋ አገር ነው የሚናገረው? የዚህች አገር ተግባራት ውጤቶች ምን ይሆናሉ? (ሐ) «በዚያን ቀን» እግዚአብሔር ምን «አክሊል» ይሆናል (ቁ. 5)? ይህ ምንን ያመለክታል? (መ) እግዚአብሔር ካህናትንና ነቢያትን እንዴት ገለጻቸው? የተግባራቸው ውጤት ምንድን ነው? (ሠ) አይሁዶች በቁጥር 10 በኢሳይያስ ላይ ሲያፌዙ ለማስተላለፍ የፈለጉት መልእክት ምንድን ነው? እግዚአብሔር በእነዚያ ፌዘኞች ላይ ምን እንደሚያደርግ ተናገረ? ይህ እንዴት ተፈጸመ? (ረ) ሕዝቡ የምን ቃል ኪዳን ነበር የገቡት? (ቁ. 15)። ይህን ሲሉ ምን ማለታቸው ይመስልሃል? (ሰ) የጽዮኑ ድንጋይ ማን ነው? (ማቴ. 21፡42–44፤ የሐዋ. 4፡11፤ ሮሜ 9፡30–33፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡4–8 ተመልከት)። በዚህ ድንጋይ የሚታመኑ ምን ይሆናሉ? በዚህ ድንጋይ የማይታመኑ ምን ይሆናሉ? (ሸ) በምድሪቱ ላይ ስለወጣው ትእዛዝ ኢሳይያስ የሚናገረው ምንድን ነው (ቁ. 22)። በእርሱ ዘመን የአይሁድ ምላሽ ምን ይሆን ነበር? (ቀ) ከ23–29 የተላለፈው መልእክት ምንድን ነው? (በ) የዚህን ምዕራፍ ዐቢይ ትንቢት በራስህ አገላለጽ ጻፍ።

ምዕራፍ 28–35 የትንቢተ ኢሳይያስ ቀጣዩ ዓቢይ ክፍል ነው። የዚህ ክፍል ዐቢይ ጭብጥ እግዚአብሔር የታሪክ አምላክ እንደሆነ የሚገልጽ ነው። በሁሉም አገርና በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ በሥልጣኑ ይገዛል። እርሱ ታሪክን ስለሚቆጣጠር፥ ስለ ወደፊት የሰጠን የተስፋ ቃሎች ሁሉ የሚፈጸሙ መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። እግዚአብሔር በኢሳይያስ ዘመን እጅግ ኃያላን የነበሩትን ሁለት አገሮች ማለትም ግብፅና አሦርን በማንበረከክ በታሪክ ላይ ፍጹማዊ የበላይነት

እንዳለው አመልክቷል። ሕዝቅያስ ከአሦር እጅ ትታደገኛለች ብሎ የሚተማመንባት ግብፅ ምን ያህል ኃይል-አልባ እንደሆነች ለአይሁዶች አሳይቷል። ታላቁ የአሦር ሠራዊት እርባና ቢስ በመሆኑ እግዚአብሔር በአንድ ሌሊት ሊያጠፋ ችሏል።

ቀደም ባለው የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል (24-27)፥ የኢሳይያስ ዋነኛ ትኩረት በመጨረሻው ዘመን ላይ ነበር። ይኸውም ኢየሱስ ክርስቶስ ሊመለስ ሲል፥ በሚመለስበት ጊዜና ከተመለሰ በኋላ በሚከሰቱ ጉዳዮች ላይ መሆኑ ነው። ቀጣዩ የትንቢተ ኢሳይያስ ክፍል (28-35) ስድስት ተከታታይ ትንቢቶችን አካትቷል። እነዚህ ትንቢቶችም እያንዳንዳቸው «ወዮ» በሚል ቃል የሚጀምሩ ናቸው (28፡1፤ 29፡1፤ 29፡15፤ 30፡1፤ 31፡1፤ 33፡1)። የእነዚህ ምዕራፎች ዋነኛ ትኩረት በሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥት፥ በደቡባዊው የይሁዳ መንግሥትና በዓለም አገሮች ሁሉ ላይ የሚደርሰው የቅርብ ጊዜ ፍርድ ነበር። ይሁንና፥ በምዕራፎቹ ሁሉ ውስጥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች እና ስለ ልጆቹ የሚሠራቸው ነገሮች ተሰግስገው ይገኛሉ።

በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ የሚገኙ ትንቢቶች ቅደም-ተከተላቸውን የጠበቁ አይደሉም። በምዕራፍ 24-27 የቀረቡት ትንቢቶች ከእነዚህኞቹ ኋላ የተሰጡ ይመስላል። ኢሳይያስ ምዕራፍ 28 በሚጻፍበት ወቅት፥ ሰሜናዊው መንግሥት ገና በምርኮኛነት አልተወሰደም ነበር። ስለሆነም ይህ ትንቢት የተሰጠው ከ722 ዓ.ዓ. በፊት ነው ማለት ነው። ይሁንና፥ የሰማርያ ኃይል እየተፈረካከሰ በመሆኑ ወደዚሁ ዘመን (722) የቀረበ መሆን አለበት። (ማስታወሻ፡ ምንም እንኳ ከእነዚህ ትንቢቶች አንዳንዶቹ ወደ ሰማርያ ያነጣጠሩ ቢሆኑም፥ ቀዳሚ ትኩረታቸው በሰማርያ የነበሩ አይሁዶች ትምህርት እንዲያገኙና ከተመሳሳይ አደጋ እንዲተርፉ ማስጠንቀቅ ነበር።)

## 1. ወዮ ለሰማርያና ለእስራኤል (ኢሳ. 28፡1-29)

### ሀ. የሰማርያ ውድመት፥ የኤፍሬም አክሊል (ኢሳ. 28፡1-4)

የእስራኤል መዲና የነበረችው የሰማርያ ከተማ ውብ ነበረች። (ማስታወሻ፤ ኢሳይያስ ብዙውን ጊዜ እስራኤልን «ኤፍሬም» እያለ ይጠራል። ይህም ከሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ዋነኛ ነገድ የተወሰደ ስያሜ ነው።) ሰማርያ በወይን አትክልት ባሸበረቀ ኮረብታማ አካባቢ የተከበበች ስትሆን፥ በዙሪያዋ ለምለም ሸለቆዎች ሞልተው ነበር። በመሆኑም በውብ አረንጓዴ መሬት ላይ የሚገኝ አክሊል ትመስል ነበር። ሕዝበ እስራኤል ለተለያዩ ምክንያቶች በከተማቸው ይመኩ ነበር። እንደ ኢየሩሳሌም ደረቅ ሳትሆን በለምለም አካባቢ ትገኝ ነበር። በጥሩ ሁኔታ የተገነባች ስትሆን፥ ብዙ ውብ ሕንጻዎች ነበሩአት። ከከተማዪቱ ዙሪያ የተሠራው ግዙፍ ቅጥር ለነዋሪዎቿ እንደማይደፈር

ጽኑ ምሽግ ነበር። የሕዝበ እስራኤል ፖለቲካዊና ሃይማኖታዊ ማዕከል ነበረች። ኢሳይያስ ከተማዪቱ «አክሊል» ወይም የውበት ማዕከል እንደሆነች ይገልጻል። ይህም የሰሜኑ የእስራኤል መንግሥት ነዋሪዎች ሁሉ ይመኩባት እንደነበር ያሳያል። (አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች ኢሳይያስ አበቦችን ከራሳቸው ላይ እንደ አክሊል እየደፉ ሰክረው ስለሚንገዳገዱት የኤፍሬም መሪዎች አእምሮአዊ ሥዕል እየሣለ እንደሆነ ያስባሉ። እነዚህ መሪዎች ከኮረብታ ላይ እንደ አክሊል የተሰየመችውን የሰማርያን ከተማ በተምሳሌትነት ያመለክታሉ።)

እውን ከተማዪቱ ውብ ነበረች? ነዋሪዎቿ ባያውቁላትም፥ የሰማርያ ከተማ ውበት እንደተቀጠፈ አበባ መፍዘዝ ጀምሮ ነበር። የከተማዪቱን መንፈሳዊ ሁኔታዎች ለመመልከት የሚያስችል መንፈሳዊ ዓይን ያላቸው ሰዎች ውድቀቷን ለማየት ይችሉ ነበር። በወቅቱ እስራኤል በአሦር አገዛዝ ሥር ስለነበረችና በቅርብ ጊዜ ውስጥ በምርኮኛነት ስለምትጋዝ፥ ፖለቲካዊ ውድቀት ነበር። ሕዝቡ ከእውነት እየራቀ በመሄድ ላይ ስለነበር ግብረገባዊ ውድቀትም ነበር። ሰካራምነት በተለይም የመሪዎች መቅሰፍት ሆነ። (በ8ኛው ዓ.ዓ ሰማርያ በብልጽግና የተሞላች ከተማ በመሆኗ፥ መሪዎችና ገንዘብ ያላቸው ሰዎች እስኪሰክሩ ድረስ ከመጠጥ ቤቶች አይለዩም ነበር (ኢሳይያስ 5፡11–13፤ አሞጽ 6፡4–7)። በመሪነት ስፍራ የተቀመጡ ሰዎች የእግዚአብሔርን ሕዝብ በትክክል ለመምራት ይችሉ ዘንድ ብሩኅ አእምሮ ያስፈልጋቸው ነበር። እነርሱ ግን በሰካራምነት ኃጢአት ውስጥ ተዘፍቀው የጠራ አሳብ የሚያስተናግዱበትን አእምሮ ተነጥቀዋል። ከዚህም የተነሣ በቀላሉ በጠላት ሊሸነፉ በቅተዋል። ኢኮኖሚያዊ ውድቀትም ነበር። ለአሦር የሚከፈለው ግብር እየጨመረ ሲመጣ ከተማዪቱን ንጹሕና ውብ አድርጎ የማቆየቱ ዓቅም የማይሞከር ሆነ። አሁንም ሰማርያ ውብና ኃያል እንደሆነች በትምክሕት የሚናገሩ ሰዎች ቢኖሩ እነዚያው ሰካራሞች ብቻ ነበሩ።

ኢሳይያስ ግን አንድ ብርቱና ኃያል ሰው እንደሚመጣባቸው ይናገራል። ይህ የአሦርን ንጉሥ የሚያመለክት ነበር። አሦር በወቅቱ እጅግ ኃያል አገር ነበረች። በወጨፎ፥ በዝናብ፥ በነፋስና በጎርፍ እንደሚታጀብ ማዕበል የአሦር ንጉሥ ከሰማርያ ላይ ዘምቶ ያጠፋታል። በአንድ ወቅት ውብ ሆና የታየችው ከተማ (አክሊል) የሠርግ ማድመቂያ አበቦች ከጠወለጉ በኋላ እንደሚጣሉ ከመሬት ላይ ትጣላለች። የአሦር ሠራዊት ሰማርያን መጥቶ ባወደማት ጊዜ፥ ከተማዪቱ ብዙ ውበት አልተረፋትም ነበር። ግድግዳዎቿ፥ ሕንጻዎቿ፥ መናፈሻዎቿ፥ ወዘተ. . . ፈራረሱ።

ኢሳይያስ የሰማርያን ከተማ ከወቅቱ ቀድመው ከደረሱት ጥቂት የበለስ ዛፎች ጋር ያነጻጽራል። በለሲቱ ተቀጥፋ ለመበላት ደርሳለች።

አንድ መንገደኛ በዚያ በኩል ሲያልፍ ያለምንም ድካምና አሳብ አንሥቶ ይበላታል። በችኮላ ስለበላት ጣእሟን እንኳ ለመለየት አልቻለም። እንደዚሁም እግዚአብሔር ሰማርያን የሚቀጣበት ጊዜ ሲደርስ፥ የአሦር ሠራዊት ያለ ብዙ ድካም ያሸንፋታል። በዚህ ጊዜ በአንድ ወቅት ታላቅ የነበረችው ሰማርያ የምታደርገው ነገር አይኖራትም።

ለ. መጭው የእግዚአብሔር ቁጣ (ኢሳ. 28፡5-6)

ሌላም ኢሳይያስ የሚናገርለት አክሊል አለ። ከቀደመው አክሊል ማለትም ከሰማርያ በተቃራኒ፥ ይኸኛው አክሊል አይጠወልግም፤ አይፈዝም፤ ወይም አይጠፋም። ይህ አክሊል እውነተኛ አክሊል ወይም ለሕዝበ እግዚአብሔር እውነተኛ የውበት ምንጭ የሆነውን እግዚአብሔርን ያመለክታል። ኢሳይያስ ሰዎች በሁለት ነገሮች እንዳይመኩ አስጠንቅቆአቸዋል። በመጀመሪያ ደረጃ የሰው ልጆች ስኬታማነት አክሊል ወይም ጊዜያዊ ውበት አለ። ይህ ለጊዜው መልካም ቢመስልም፥ አንድ ቀን ይደበዝዛል። ሁለተኛ፥ ዘላለማዊ፥ ሊሸነፍ የማይችልና ሊወድቅ የማይችል የእግዚአብሔር አክሊል አለ። ኢሳይያስ ይህንን ዘላለማዊ አክሊል በሚከተሉት መንገዶች ይገልጻል።

1. በዚያን ጊዜ ትክክለኛው አክሊል ይመጣል። ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ ይህ የተለየ ጊዜ እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ በሚያስደንቅ መንገድ የሚሠራበት ይሆናል። ምንም እንኳ ይህ ትንቢት እግዚአብሔርን የሚፈሩ አይሁዶች ከእስራኤል ወደ ይሁዳ መጥተው እግዚአብሔርን እንዲያመልኩ በጋበዙት እንደ ሕዝቅያስ በመሳሰሉ መንፈሳዊ መሪዎች ለጊዜው የተፈጸመ ሊሆን ቢችልም፥ በዋናነት የሚፈጸመው በመጨረሻው ዘመን ይሆናል። ይህም ኢየሱስ ክርስቶስ መጥቶ በሚያምኑት ላይ ሲነግሥ ነው። በዚህ ጊዜ ክፉዎች ይጠፉና እግዚአብሔርን የሚፈሩት ብቻ ይቀራሉ።
2. አክሊሉ ሁሉን የሚችል አምላክ ይሆናል። በጥንት ዘመን ድል ነሺዎች የአበባ አክሊሎችንና ውብ ነገሮችን ለጊዜው ከራሳቸው ላይ ያደርጉ ነበር። ወይም የውበትና የኃይል ቋሚ ተምሳሌት የሆነውን ዘውድ ይደፉ ነበር። በዕብራይስጥ የቃሉ ፍች አክሊል ወይም ዘውድ ሊሆን ይችላል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያቀደውን ሁሉ ለማጠቃለል በሚመጣበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ገዥና የውበት ምንጭ ይሆናል። እግዚአብሔር ኃይልን ሁሉ የያዘ ሁሉን የሚችል አምላክ ስለሆነ አይሸነፍም። ይህ በዓለም ሰዎች ከሚኩራሩባቸው ጊዜያዊ ነገሮች ሁሉ የሚቃረን ነበር። አይሁዶች የእስራኤል አክሊል በነበረችው በሰማርያ ቢመኩም፥ በአሦር ሠራዊት ተደምስሳለች።

3. አክሊሉ የከበረና ውብ ነው። ይህ በክብርና በውበት የተሞላውን አምላክ ያመለክታል። ውበቱም ውጫዊ ሳይሆን በፍቅር፥ በምሕረት፥ በጸጋ፥ በፍትሕ፥ ወዘተ. . . ባሕርዩ ውስጥ የሚገኝ ነው። እንደ ሰማርያ ካለች ምድራዊት ከተማ አላፊ ውበት በላይ የእግዚአብሔር ውበት እውነተኛና ዘላለማዊ ነው።
4. ይህ ልዩ አክሊል ከሕዝበ እግዚአብሔር ቅሬታ ጋር ልዩ ግንኙነት አለው። በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት በማድረግ ላይ የሚገኙትን ሰዎች ለማመልከት «ቅሬታ» የሚለውን ቃል ተጠቅሟል።
5. እግዚአብሔር «በፍርድ ወንበር ላይ ለሚቀመጠው የፍርድ መንፈስ» ይሆንለታል። ይህ ወደፊት በእስራኤል ላይ የሚነግሠውን መሢሕ የሚያመለክት ነው። እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ በሚነግሥበት ጊዜ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ኢሳይያስ በብርቱ የሚናፍቀው አንድ ባሕርይ ቢኖር ፍትሕ ነበር (ኢሳ. 1፡17፥ 27፤ 5፡7፤ 9፡7፤ 11፡3–4፤ 32፡1)። ለዚህም ምክንያቱ ከንጉሥ ጀምሮ እስከ መሳፍንቱ፥ ካህናቱና ነቢያቱ ሳይቀር ኢሳይያስ ፊቱን ባቀናበት ስፍራ ሁሉ ፍትሕን ሊያገኝ አለመቻሉ ነበር። ሁሉ የራሱን ጥቅም ያሳድድ ስለነበር፥ ድሆችና ደካሞች ተሠቃዩ። በመጨረሻው ዘመን ግን እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የፍትሕን መንፈስ ስለሚሰጥ ሀብታሞችም ሆኑ ድሆች፥ ኃያላንም ሆኑ ደካሞች በሙሉ በአክብሮትና በእኩልነት ይስተናገዳሉ።

5ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዛሬ በኢትዮጵያ ፍትሕ የጎደለው እንዴት ነው? ለ) ብዙውን ጊዜ በቤተ ክርስቲያንም ፍትሕ የማይታየው እንዴት ነው? ሐ) ኢየሱስ ክርስቶስ የቤተ ክርስቲያንህ ወይም የአገርህ መሪ ቢሆን፥ በፍትሕ ከመሥራቱ የተነሣ ነገሮች እንዴት ሊቀየሩ ይችላሉ? መ) ኢየሱስ ክርስቶስ የሚፈልገውንና ወደፊት አንድ ቀን የሚገዛበትን ሁኔታ ለማንጸባረቅ ዛሬ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር እንዴት ሊለወጥ እንደሚገባ ግለጽ።

6. አክሊል የሆነው እግዚአብሔር ጠላትን ለማሸነፍ የኃይል ምንጭ ይሆናል። የሰማርያ ከተማ በቅጥር የተከበበች ብትሆንም፥ የእስራኤል ሠራዊት አሥራውያንን ከውጭ ለማስቀረት አልቻሉም ነበር። ከብዙ ዓመታት ውጊያ በኋላ፥ አይሁዶች ተሸነፉ። ከተማዪቱ ተደመሰሰች፤ ሕዝቡም በምርኮኝነት ተወሰደ። ይኸው ተመሳሳይ ሁኔታ በኋላ በይሁዳ ላይ ይደርስና ባቢሎን ከተማዪቱን ትደመስስ ነበር። ይሁንና፥ አንድ ቀን ነገሮች ይለወጣሉ። ሕዝቡ እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ስለሚያመልክና በታዛዥነት ስለሚመላለስ፥ እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን ሙሉ ለሙሉ ድል ይነሡ ዘንድ ኃይልን ይሰጣቸዋል።

6ኛ ጥያቄ፡– ሁሉን የሚችል አምላክ ለሕዝቡ አክሊል የሚሆንበትን ጊዜ እንዴት በናፍቆት ልንጠባበቀው ይገባል? ይህ እውነት ዛሬ እንዴት ሊያጽናናን ይችላል?

## ሐ. የእስራኤል ሃይማኖታዊ መሪዎች ለምሳሌነት አለመብቃት (ኢሳ. 28፡7–8)

እግዚአብሔርን በመታዘዝ እንዴት እንደሚኖሩ አርአያነት ያለው ሕይወት በመምራት ሕዝበ እግዚአብሔርን ወደ እውነት ሊመሩ የሚገባቸውና በኢየሩሳሌም የሚኖሩ መንፈሳዊ መሪዎችስ ምን ይመስሉ ነበር? ኢሳይያስ እነዚህ ሰዎች እንዴት የእግዚአብሔርን ሕዝብ ወደ እውነት ለመምራት እንዳልቻሉ ገልጾአል። ካህኑ የእስራኤልን ሕዝብ በእግዚአብሔር ፊት የመወከል ኃላፊነት ነበረበት። የእግዚአብሔርን ቃል የማስተማርና ከሕዝቡ ሕይወት ጋር የማዛመድ ኃላፊነት ነበረበት። ነቢዩ ደግሞ ለሕዝቡ የእግዚአብሔር ቃል አቀባይ ነበር። እግዚአብሔር እውነቱን ለሕዝቡ የሚያስተላልፈው በነቢዩ አማካኝነት ነበር። እንደዚህ ዓይነት ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተሞልተው እንደ እግዚአብሔር ትእዛዛት ሊመሩ ይገባቸው ነበር። እግዚአብሔር የሚፈልገውን የፍትሕ ባሕርይ ማንጸባረቅ ነበረባቸው። (ማስታወሻ፡ አንዳንድ ምሑራን የምዕራፉ አጽንኦት እዚህ ጋ ከሰማርያ ወደ ይሁዳ እንደሚለወጥ ይናገራሉ። የሰማርያ ሰዎች በጠጭነታቸው ይታወቃሉ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚባሉት የይሁዳ ሰዎችም እንደ እነዚያው የከፉ ነበሩ። እነርሱም ጠጭዎች ነበሩ።)

የሚያሳዝነው እንደ ፖለቲካዊ መሪዎች ሁሉ እነዚህም የእግዚአብሔር አገልጋዮች ጠጭዎች ሆነው መገኘታቸው ነው። (በዚያን ጊዜ መጠጥ የእግዚአብሔር ሕዝብ ዋነኛ ችግር እንደነበር ከትንቢተ ኢሳይያስ፥ አሞጽና ሌሎችም የትንቢት መጻሕፍት እናነባለን።) ግብረገባዊ ሕይወታቸው የተበላሸ በመሆኑ፥ እግዚአብሔር ለነቢያት ራእይን ሲሰጥ ወይም ስለ አንድ ጉዳይ እንዲናገሩ ሲልካቸው ከመስከራቸው የተነሣ ምን እንዳላቸው ይጠፋቸው ነበር። ከዚህም የተነሣ በእግዚአብሔር ፋንታ ለሕዝቡ የመናገር አገልግሎታቸውን ለመወጣት ሳይችሉ ይቀራሉ። የራሳቸው ግብረገባዊና መንፈሳዊ ሕይወት የተቦረቦረ በመሆኑ፥ የሕዝቡን ሕይወት ለመለወጥ የሚጫወቱት ሚና አልነበረም። ኢሳይያስ የእነዚህን መንፈሳዊ መሪዎች ባሕርይ በሥዕላዊ ተዘክሮ ያቀርብልናል። እጅግ ከመስከራቸው የተነሣ ትውኪያቸው ቤቱን ሞልቶ ሳለ ሊያውቁና ሊጠርጉ አለመቻላቸውን ይገልጻል። ኢሳያስ ይህንን የከፋ ተምሳሌት የተጠቀመው መንፈሳዊ መሪዎች በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት እንደዚያ መሆናቸውን ለማሳየት ይመስላል። ራሳቸውን ለመቆጣጠር እንደማይችሉና በቆሻሻ እንደተሸፈኑ ሰካራሞች ሁሉ፥ እነዚህም

መሪዎች በመንፈሳዊ ሁኔታ የቆሸሹና የክህነት ብሎም የነቢይነት ሚናቸውን ለመጫወት ያልቻሉ ነበሩ።

7ኛ ጥያቄ፡– ሀ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እንዲህ ላለ ግብረገባዊ ወይም መንፈሳዊ ችግር ከመጋለጣቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል መስማት፥ መረዳት፥ ወይም ለሕዝቡ ማወጅ ከማይችሉበት ደረጃ የሚደርሱባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከዚህ ደረጃ ላለመድረስ ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

**መ. መንፈሳዊ ነገሮችን አለመረዳት ሰዎች በእግዚአብሔር ላይ እንዲሳለቁ ያደርጋል (ኢሳ. 28፡9–22)**

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ቃል ሲናገር ሕዝቡ አይሰሙም። ምናልባትም መጀመሪያ ጉጉዎች ነበሩ። ኋላ ግን ተሰላቹ። ሕዝቡ ወዲያው በኢሳይያስና በመልእክቱ ላይ ያላግጡ ጀመር። በዚህ የሕዝቡ ልብ ደንድኖ እንዴት የኢሳይያስን መልእክት ሊሰሙ እንዳልፈለጉ የሚያሳዩ ሁለት ምሳሌዎች አሉ። ከዚህም የተነሣ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚደርስባቸው የተረጋገጠ ሆነ።

1. **ኢሳይያስ ባለማቋረጥ የእግዚአብሔርን ቃል እንዲታዘዙ ስለጠየቃቸው አላገጡበት (ኢሳ. 28፡9–13)**

የይሁዳ ሕዝብ የተወሳሰቡ ነበሩ። ኢሳይያስ የሚሰብከው የንስሐና የታዛዥነት ትምህርት ከደረጃቸው ጋር የማይመጣጠን አነስተኛ ነገር መሰላቸው። «ጡት የጣልን ሕጻናት መሰልነው እንዴ? ከእርሱ በላይ እናውቃለን። የሚያስተምረው ሁሉ ከንቱ ድግግሞሽ ነው። እኛ የምናደርገውን እናውቃለን። ኢሳይያስ እንዲሰብከን አንፈልግም» ሲሉ ተናገሩ። (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «እውቀትን ለማን ያስተምረዋል? ወይስ ወሬ ማስተዋልን ለማን ነው ይሰጣል?» ሲል ይጠይቃል። ቁጥር 9 የሚተረጎምበት ሌላው መንገድ «መልእክቱን ለማን ነው የሚያብራራው?» የሚል ይሆናል።)

በዕብራይስጥ ቋንቋ ቁጥር 10 እንዴት እንደሚተረጎምና ፍች እንደሚሰጥ መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። ብዙ ዓይነት አተረጓገሞች አሉ።

ሀ) ቃላቱ ሕጻን ልጅ እንደሚያሰማቸው ድምፆች ትርጉም የሌላቸው ናቸው።

ለ) ምናልባትም ከሰካራምነታቸው የተነሣ የኢሳይያስን መልእክት ሙሉ ለሙሉ እንዳልተረዱና ብዙም ስሜት እንዳልሰጣቸው የሚያሳይ ይሆናል። ይህም ሕጻናት አንዳንድ የሚደመጡ ቃላት እንደሚናገሩና ሙሉውን ዓረፍተ ነገር ለመገንዘብ እንደሚያስቸግር ማለት ነው።

ሐ) ምናልባትም በኢሳይያስ ላይ በመሳለቅ፥ «ውድ ኢሳይያስ፥ ወዴትም ብንመለስ አንተ ወዳልሃቸው የተለያዩ ነገሮች መመለሳችን

ነው። ይሁንና፥ እነዚህ ነገሮች ግልጽ ያልሆኑ ብጥስጣሾች ናቸው። ምን እንደሚሉም አናውቅም! ግልጽ ሁንልን!» እያሉ ይሆናል።

መ) ምናልባትም በዚህ ስፍራ እንደተተረጎመው፥ በኢሳይያስ ላይ ለመሳለቅ የተጠቀሙት ምሳሌያዊ አነጋገር ይሆናል። «ኢሳይያስ እንዲህ አድርግ እንዲያ አድርግ እያለ ሥርዓትን ያከታትልብናል። ይህንኑ ቀላል ትምህርት አሁንም አሁንም ይደጋግምብናል። እንዴት ያሰላቻል!» ማለታቸው ይሆናል። እንደ መልካም አስተማሪ፥ ኢሳይያስ መንፈሳዊ መርሆችን ቀስ በቀስ እያስተማረ ነበር። ይህንንም የሚያደርገው ወደጠለቁት እውነቶች ለመምራት ይችል ዘንድ ከሰዎቹ ሕይወት እድገት ምልክቶችን እየተመለከተ ነበር። አንድ ቀን ወደ ቃሉ አጥንት ይደርሳሉ በሚል ተስፋ የእግዚአብሔርን ቃል ወተት እየገመገባቸው ነበር። ሕዝቡ ግን የእርሱን አሳብ ሳይረዱ ስለ ቀላሉ ትምህርት ይሳለቁበት ጀመር።

ኢሳይያስ ስላቃቸውን ወደ ጠንካራ ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያነት ለወጠው። ለእነርሱ ግን የእርሱ ቃላት እንደ ሕጻን ልጅ ንግግር ድግግሞሽ ብቻ ሆነባቸው። ስለሆነም፥ የባዕድ አገርን ልሳን ማለትም የአሦርና የባቢሎንን ይሰማሉ። እነዚህም ለአይሁዳውያን ትርጉም በማይሰጥ በባዕድ ልሳን የሚናገሩ ይሆናሉ። አይሁዶች የአሦርን ወይም የባቢሎንን ቋንቋ አያውቁም ነበር። ነገር ግን ከእግዚአብሔር ኃይለኛ ፍርድ ሳቢያ ወደ ምርኮ ለመሄድ ይገደዳሉ። በአሦር፥ በባቢሎንና ቋንቋዎቻቸውን በማያውቋቸው ሌሎች የአሕዛብ ሕዝብ መካከል ሲኖሩ፥ ከጌቶቻቸው የሚሰነዘሩ ቃላት ትርጉም-የሌለው ጫጫታ ይሆንባቸዋል። እግዚአብሔር የማረኳቸውን ሰዎች ትርጉም የሌለው ጫጫታ እንዲሰሙ በማድረግ ይፈርድባቸዋል።

እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል ባመጣላቸው ቃል አማካኝነት ዕረፍትን ሰጥቶአቸዋል። እነርሱ ግን በቃሉ ተሳልቀው እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ያሳርፋቸው ዘንድ ያቀረበላቸውን ዕረፍት ወደ ዳር ገፍተዋል። በተጨማሪም እግዚአብሔርን በማወቅና ለዘላለም መንግሥቱ የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች ከፍጻሜ እንደሚደርሱ በመረዳት ልበ ሙሉነትን ተጎናጽፈው መንፈሳዊ ዕረፍት ሊያገኙ አልቻሉም። እነርሱ የሚፈልጉትን መርጠዋል። ስለሆነም እግዚአብሔር የተሳለቁበትን ወደሚመስል ሁኔታ በግድ ያስገባቸዋል። (ከእግዚአብሔር በተጨማሪ በሌላ ሰው ላይ እንዳንደገፍ የተሰጠውን ማስጠንቀቂያ ከኢሳይያስ 8፡14-15 አንብብ።)

(ማስታወሻ፥ ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮንቶስ 14፡21 በልሳን ስለመናገር እያስተማረ ሳለ ኢሳይያስ 25፡11-12ን መጥቀሱ አስገራሚ ነገር ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ፥ ሰዎች የማያውቁትን ቋንቋ መስማታቸው የፍርድ ምልክት ነበር። በአዲስ ኪዳንም እንደዚሁ በአደባባይ የአምልኮ

ስፍራዎች በልሳን መናገር እግዚአብሔር በማያምኑ ሰዎች ላይ የሚያመጣውን ፍርድ በማሳየት ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እንዲመለሱ ምልክት የሚሆን ነበር። ይህንን መረዳታችን እግዚአብሔር በሰጠን የጸጋ ስጦታ እንድንጠቀም ሊያበረታታን ይገባል።)

2. ከሞትና ከመቃብር ጋር ቃል ኪዳን እንደተጋቡና ከእንግዲህ ሞት እንደማይነካቸው በመግለጽ በኢሳይያስ ላይ ተሳለቁ (ኢሳይያስ 28፡14-22 አንብብ)

ኢሳይያስ ሕዝቡ የእግዚአብሔር ፍርድ እንደሚጠብቃቸው ሲያስቡ ያሳዩትን የሞኝነት አመለካከት ሁለተኛ ምሳሌ በመጠቀም መናገሩን ይቀጥላል። በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ የአይሁዶችን ትዕቢት አዘል አመለካከት ጠቅለል አድርጎ ማቅረቡ እንጂ እውነትም ከሞት ጋር ቃል ኪዳን መጋባታቸውን መግለጹ አይመስልም። ወይም ደግሞ የይሁዳ መሪዎች ወደ ግብፅ በመሄድና ቃል ኪዳን በመጋባት ከፖለቲካዊ ሞት እንደሚያመልጡ አስበው ይሆናል። ይሁንና፥ ይኸው አመለካከታቸው ለአሥርና ባቢሎን ምርኮኛነት አልፈው መሰጠታቸውን ከማፍጠን የተሻለ ሚና አልነበረውም። ምናልባትም ሕዝቡ፥ «ኢሳይያስ፥ በቅርቡ በምርኮኛነት ተወስደን እንደምንሞት ደጋግመህ ትነግረናለህ። ይሁንና፥ ወደ ጠንቋይ እንደሄደ ሰው ወይም ከጣዖቶቻቸው ጋር ቃል ኪዳን እንደተጋቡ ሰዎች ራሳችንን ለመከላከል የሚያስችል ኃይል አለን። አሥር ሲያጠቃን ግብፅና ጣዖቶቿ ሁሉ ይታደጉናል። ስለሆነም አንተ እንደምትተነብየው ለፖለቲካዊም ሆነ መንፈሳዊ ሞት አንዳረግም። እኛ ልንሸነፍ የማንችል ሰዎች ነን» ማለታቸው ይሆናል። በኢየሩሳሌም የሚገኙ አይሁዶች ስለ ሰማርያ መማረክ ቢሰሙም፥ ከግብፅ ጋር አዲስ ቃል ኪዳን ከመጋባታቸው የተነሣ ለእንዲህ ዓይነት ችግሮች የሚያጋለጡ አልመሰላቸውም። በምንም ዓይነት ወደ ምርኮ እንደማይሄዱ እርግጠኞች ነበሩ።

ኢሳይያስ ስለ ሁለት ነገሮች ማረጋገጫ በመስጠት መለሰላቸው።

1. እውነተኛ ነፃ መውጣት የሚገኘው ከአንድ ስፍራ ብቻ ነበር። ይህም የተፈተነው፥ የከበረውና መሠረቱ የጸናው የጽዮን ድንጋይ ነበር። በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ ስለ ሁለት ዓይነት ድንጋዮች እየተናገረ ሊሆን ይችላል። የመጀመሪያው የማዕዘን ድንጋይ ነው። በጥንት ዘመን፥ አዲስ ሕንጻ በሚታነጽበት ጊዜ አናጺዎች የሚወስዱት የመጀመሪያው እርምጃ በአራት ማዕዘን መልክ የሚቀርጹትን ግዙፍ ድንጋይ መፈለግ ነበር። ይህንኑ ድንጋይ ከመሠረቱ ማዕዘን ላይ ያስቀምጡታል። ይህ ጠንካራና በትክክል የተቀረጸ በመሆኑ፥ የተቀረው የሕንጻ ክፍልም ጠንካራና የተስተካከለ እንዲሆን ያደርጋል። ይህ ድንጋይ ደካማና በአግባቡ ያላተስተካከለ እንደሆነ፥ ጠቅላላው መዋቅር ይዝልና የኋላ

ኋላ ለውድቀት ይዳረጋል። የማዕዘን ድንጋዩ ከቦታው ተስተካክሎ ከተቀመጠ፥ ሌሎች የመሠረትና የግድግዳ ድንጋዮች ከማዕዘኑ ድንጋይ ጋር በሚስማማ መልኩ ተጠርበው ይገባሉ። የማዕዘኑ ድንጋይ መለወጥ አያስፈልገውም። ነገር ግን ለሕንጻው ግንባታ የሚያስፈልጉ ሌሎች ድንጋዮች ሁሉ ሕንጻውን ቀጥተኛና ጠንካራ ለማድረግ ከማዕዘኑ ድንጋይ ጋር መስማማት አለባቸው። በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ የሚናገረው ሌላው ድንጋይ የመደምደሚያው ድንጋይ ነው። ይህ ሌሎችን ድንጋዮች ሁሉ የሚያያይዝ በመሆኑ ለጥንካሬና ለውበት ሆን ተብሎ የሚመረጥ ነው።

«የጽዮን ድንጋይ» የሚለውን ሐረግ በሁለት መልኩ መተርጎም ይቻላል። በመጀመሪያ ደረጃ «በጽዮን የሚገኝ ድንጋይ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ወይም ደግሞ «ጽዮን የተባለ ድንጋይ» ተብሎ ሊተረጎም ይችላል። ሁለተኛውን አተረጓጎም የምንከተል ከሆነ፥ ኢሳይያስ የዳዊት ከተማ በሆነችው ጽዮን የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች እንደሚፈጸሙ የሚናገር መሆኑን እንረዳለን። ሕዝቡ የሚድኑት እንደ ግብፅ ባሉት አገሮች በመታመን ሳይሆን በጽዮን ባለው እግዚአብሔር በመደገፍ ነው።

የመጀመሪያውን ትርጉም ከተከተልን፥ ኢሳይያስ በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ ሕዝቡ የታነጸበት እውነተኛ መሠረት እንዳለ እየተናገረ መሆኑን እንረዳለን። ይህ ድንጋይ የተመሠረተው በእግዚአብሔር እንጂ በሰው አልነበረም። ስለሆነም ሰው ሊሠራው ከሚችለው መሠረት ሁሉ በላይ ያስተማምናል። ይኸው ድንጋይ ብቻ ነበር ደኅንነትን ሊያመጣ የሚችለው። በቀዳሚነት ይህ ድንጋይ ራሱ እግዚአብሔርን ያመለክት ነበር። እውነተኛው፥ ሕያውና ሁሉን የሚችል አምላክ የሆነው እግዚአብሔር በጽዮን በቤተ መቅደስ ውስጥ ይኖር ነበር። ከጠላት ለመዳን ሙሉ ነጻነት የሚገኘውና ሕዝቡ ከጠላት ድኖ ለምእተ ዓመታት የሚኖረው በዚያ ነበር። እግዚአብሔር በባሕርዩና በእገዛው ጠንካራ፥ የማይነቃነቅና ግለሰብን ወይም ሕዝብን ለመታደግ ጽኑ ድጋፍ ነው። ሕዝቡ ያ ድንጋይና የዚያ ድንጋይ (እግዚአብሔር) ባሕርይ የእምነታቸው መሠረት እንዲሆን ከፈቀዱና በዚያ ድንጋይ መሰፈርት ከተመላለሱ፥ አስተማማኝ ዋስትና ነበራቸው። ያ ድንጋይ ፍትሕና ጽድቅን ይፈልጋል። ያ ደግሞ ለሕዝቡ መለኪያ ይሆነዋል። የድንጋዩን መሰፈርት ያላሟላ ማንኛውም አገር፥ መሪ ወይም ግለሰብ በማዕበል እንደሚወሰድ ያህል ለጥፋት ይዳረጋል። ለዘላለም የሚኖረው የእግዚአብሔር መንግሥት አካል አይሆንም። አይሁዶች ለሕዝባቸው ያላቸውን የደኅንነት እምነት በዚያ የመሠረት ድንጋይ ላይ ካላሳረፉ፥ እግዚአብሔር ሕዝባቸውን የሚያጠፋ ድንጋይ ይሆንባቸዋል።

ሌሎች ምሑራን ድንጋዩ የዳዊት ንጉሣዊ አገዛዝ እንደሆነ ያስባሉ። ጥበቃ የሚመጣው ከአሦር፥ ከግብፅ ወይም ከባቢሎን አይደለም። ይህ በእግዚአብሔር ስለተመሠረተ፥ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎችና ጥበቃ ተግባራዊ የሚሆነው በመሢሑ ተፈጻሚነትን ባገኘው የዳዊት አገዛዝ ነው።

በአዲስ ኪዳን ውስጥ ኢየሱስ ክርስቶስ የማዕዘን ድንጋይ እንደሆነ ተገልጾአል። የአሐዱ-ሥሉስነት ሁለተኛ አካል እንደመሆኑ፥ መሢሑ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢሳይያስ የገለጸውን የማዕዘን ድንጋይ ይወክላል። እርሱ ሕይወታችንና አብያተ ክርስቲያናችን የሚታነጹበትን መሠረት ይሰጠናል ወይም ሕይወታቸውን በእርሱ ምሳሌነት የማይቀርጹትን ሰዎች ያጠፋል (ሮሜ 9፡33፤ 10፡11፤ 1ኛ ጴጥ. 2፡4-8 ተመልከት)።

ሕይወታችንን እግዚአብሔር ባዘጋጀልን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረት ላይ ልናንጽ እንችላለን። አልያም ሕይወታችንን የራሳችን ሕልሞችና ተስፋዎች በሞሉበት አሸዋማ መሠረት ላይ ልንመሠርት እንችላለን። ምርጫው የራሳችን ነው። ይሁንና፥ ኢሳይያስ ምርጫችን በሚያስከትላቸው ውጤቶች መሠረት መኖር እንዳለብን ያስገነዝበናል። ኢየሱስ ክርስቶስን ብንመርጥ ዘላለማዊ ዋስትና አለን። ራሳችንን ብንመርጥ በድንጋዩ እንደመሰላለን።

2. አይሁዶች የእግዚአብሔርን መሠረታዊ መንገዶች ተከትለው በማይኖሩት ሰዎች ላይ ጥፋት እንደሚመጣ ማወቅ ይገባቸው ነበር። ሕንጻውን ለመለካት ሜትርና ስንዝር እንደሚጠቀም አናጺ እግዚአብሔር አይሁዶችን መዝኖአቸዋል። እነርሱን ለማነጻጸር የተጠቀመበት መመዘኛ ጽድቅና ፍትሕ ነበር። ነገር ግን ጽድቅም ሆነ ፍትሕ በእነርሱ ዘንድ ስላልነበር፥ እግዚአብሔር ከተማዪቱን ያጠፋታል። አይሁዶች ከተማቸው እንደምታድናቸው በማሰብ የልብ ልብ ተሰምቶአቸዋል። ወይም ደግሞ ግብፅ ትታደጋቸው ዘንድ ተማምነውባታል። ነገር ግን ለእስራኤል አሦራውያን፥ ለይሁዳ ደግሞ ባቢሎናውያን እንደ ኃያል ማዕበል እንደ ጎርፍም ይሆናሉ። መጀመሪያ አሦራውያን፥ ከዚያም ባቢሎናውያን ከተማዪቱ እስክትደመሰስ ድረስ ይመጡባቸዋል። በአሦራውያን እጅ ውስጥ እንደሚገኝ ጅራፍ እስኪቆስሉ ድረስ ይገረፋሉ። በግለሰብም ሆነ በከተማ ደረጃ ከሞት እንደሚተርፉ የሚናገሩት ትምክሕት ከንቱ ይሆናል።

የኢሳይያስን ቃል የሰሙት ሰዎች መጀመሪያ ትኩረት የሰጡት አይመስልም። የአሦር ሠራዊት ገና ማጥቃት አልጀመረም ነበር። ቅጥሮቻቸው ገና አልወደቁም። ነገር ግን የኢሳይያስን ትንቢት ለመረዳት የሚገደዱበት ጊዜ ይመጣል። ውጤቱንም በመገንዘብ ለፍርሃት ይጋለጣሉ። በዚህ ጊዜ ግን ምንም ሊያደርጉ እስከማይችሉ ድረስ ጊዜው ይረፍዳል። ከሞት ጋር እንደተጋቡ የተናገሩት ቃል ኪዳን

ከንቱ ይሆንና የእግዚአብሔርን የሞት ፍርድ ለመጋፈጥ ይገደዳሉ። «አልጋውን ያዘጋጀ ሊተኛበት ይገባል» የሚል የእንግሊዞች አባባል አለ። አባባሉ የተነገረው አንድ ሰው ምርጫው ያስከተላቸውን መዘዞች መቀበል እንዳለበት ለማመልከት ነው። ኢሳይያስም ለአይሁዶች ተመሳሳይ አባባል ተጠቅሞአል። አይሁዶች ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ተጋብተዋል። የሚፈልጉትን የመረጡ ሲሆን፥ አሁን ግን የመረጡት አልጋ የእነርሱ ልክ እንዳልሆነ ተረድተዋል። አጭር አልጋ የሚገዛ ቅልጥማም ሰውም ሆነ፥ በብርዳማ ስፍራ አጭር ብርድ ልብስ ለብሶ የሚተኛ ግዙፍ ሰው ዕረፍት ሊያገኙ አይችሉም። የይሁዳ ሕዝብም ከእግዚአብሔር ውጭ ባሉት ነገሮች ላይ በመደገፍ ዕረፍት ሊያገኙ አይችሉም። የእስራኤልና የይሁዳ ሕዝብ በቅርብ ቀን ለሚደርስባቸው አደጋ አልተዘጋጁም። በእግዚአብሔር ላይ በማመፅ ላይ ስለነበሩ፥ ግብረገባዊ ዝግጅት አላደረጉም። ለጠላት የሚሸነፉ መሆናቸው ደግሞ ወታደራዊ ዝግጅት አለማድረጋቸውን ይጠቁማል። የፈሩት ፍርድ (መከራ) ከተማዪቱ ሙሉ ለሙሉ እስክትደመሰስ ድረስ በተከታታይ ይደርስባቸዋል።

ኢሳይያስ ውድመቱ አይቀሬ መሆኑን ለማሳየት፥ እግዚአብሔር በከፍተኛ ኃይል ጠላቶቹን ያጠፋባቸውን ሁለት ታሪካዊ ክስተቶች ይጠቅሳል። በመጀመሪያ፥ እግዚአብሔር ለዳዊት በበአልፐራሲም ተራራ በፍልስጥኤማውያን ላይ ድልን የሰጠበት ወቅት ነበር (2ኛ ሳሙ. 5፡20 ተመልከት)። ሁለተኛ፥ ኢያሱ አሞራውያንን በቤትሖሮን ድል እንዲመታቸው አድርጎአል (ኢያ. 10፡10-11)። በእነዚህ ቀደምት ሁኔታዎች እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተዋግቶላቸዋል። አሁን ግን እግዚአብሔር ለሕዝቡ ጠላት ሆኖ ይዋጋል። እግዚአብሔር አሦራውያንንና ባቢሎናውያንን በመጠቀም በሕዝቡ ላይ ፍርዱን ይገልጣል። በመቶዎች ለሚቆጠሩ ዓመታት መሠቃየትና በዓለም ሁሉ መበተን ይከተላል። ይሁንና፥ ወደ በኋላ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ እንደተጠቀሰው አንድ ቀን አይሁዶች እንደገና ተሰብስበው አዲስ የተባበረ ሕዝብ ይመሠርታሉ። መሢሑም በእነርሱና በዓለም ሁሉ ላይ ይነግሣል።

ኢሳይያስ እግዚአብሔር እንቅልፍ እንዳሸለበው ገልጾአል። (ፍርዱን ከማምጣቱ በፊት እስራኤላውያን ንስሐ ይገቡ ዘንድ ይጠብቃቸዋል።) ከመቅጽበት ነቅቶ የፍርድ ዕቅዱን ተግባራዊ ማድረግ ይጀምራል። ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ዕቅድና ሥራ እንግዳ እንደሆነ ይገልጻል። የእግዚአብሔር የወደፊት ዕቅድ በአይሁድ ሕዝብ ሕላዌ ላይ ይመሠረታል። አሁን ግን ሕዝቡን እያጠፋው ይመስላል። እግዚአብሔር እያጠፋ እያለ የሚሠራው እንዴት ነው? ይህ ትርጉም

የሚሰጥ ባይመስልም፥ የእግዚአብሔር ዕቅዶች ሁልጊዜም ከሁሉም የሚልቁ ናቸው።

ይህ እግዚአብሔር በአንድ የተወሰነ መንገድ ብቻ ይሠራል ብለን እንዳንተነብይ ሊያስጠነቅቀን ይገባል። የእግዚአብሔር መንገዶች ከሰው የተለዩ ናቸው። የሚሠራው እኛ በምንጠብቀው የጊዜ ሠሌዳ አይደለም። ወይም ደግሞ እኛ በምንጠብቀው መንገድ አይደለም። ውጤቱም እንዲሁ ከእኛ አሳብ የተለየ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በፍርድ ወይም በማዳን እንደሚሠራ እርግጠኞች ልንሆን እንችላለን። የመጨረሻው ውጤት ሁልጊዜም ለእርሱ ክብርን፥ ለልጆቹ ደግሞ ከሁሉ የተሻለ በጎነትን ያስከትላል።

ኢሳይያስ በቅርቡ በምርኮኛነት ለሚወሰዱት አይሁዶች ምክርን ይለግሳል። ሁሉን ቻይና የዓለም ገዥ የሆነው እግዚአብሔር በምድሪቱ ሁሉ ላይ ጥፋትን አውጆአል። (ይህ ምናልባትም ስለ እስራኤልም ስለ ይሁዳም የሚናገር ይሆናል።) ነገሩ ከረር ያለ በመሆኑ አይሁዶች ማፌዛቸውን ማቆም ነበረባቸው። ሕይወታቸውን መለወጥ ነበረባቸው። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መመላለስ ይኖርባቸዋል። ይህ የተወሰነባቸውን የምርኮኛነት ሠንሠለት አያስወግድላቸውም። በንስሐ አማካኝነት ከውድመት የመዳኛው ጊዜ አልፎአል። ነገር ግን ፍርዱ እጅግ በመረረ መልኩ እንዳይመጣባቸው ይከላከልላቸው ነበር። በተጨማሪም ምንም እንኳ ወደ ምርኮ ቢሄዱም መንፈሳዊ ሕይወታቸውን ይጠብቅላቸው ነበር።

8፡1 ጥያቄ፡– ሀ) እኛ (እንደ ክርስቲያኖች ወይም የአንድ አገር ዜጎች) እግዚአብሔር በዓለም ላይ ለሚያመጣቸው ማስጠንቀቂያዎች ግድየለሾች ልንሆን የምንችለው እንዴት ነው? ለ) ዛሬ እግዚአብሔር ከውብ ሕንጻው መጣበቃችንን ወይም መጥፋታችንን ለመለየት ላዋቀረው «የማዕዘን ድንጋይ» ምላሽ የምንሰጥባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

## ሠ. የእግዚአብሔር ፍርድ ሕዝቡን ሁሉ አያጠፋም (ኢሳ. 28፡23–29)

የእስራኤል መማረክ፥ የሰማርያ መውደምና በኋላም የኢየሩሳሌም መውደም የሕዝበ እስራኤል ፍጻሜ መሆኑ ነው? የእግዚአብሔር ፍርድ እጅግ የከፋና ሕዝቡን ፈጽሞ የሚያጠፋ ነውን? አሁንም የእስራኤል ሕዝብ እንደማይጠፋ ለማሳየት፥ ኢሳይያስ የእርሻን ማብራሪያ ተጠቅሞአል። በእርሻ ሂደት ውስጥ ነገሮች የሚካሄዱት በተወሰነ ቅደም ተከተል ነው። ገበሬው በማረስ ይጀምራል። ነገር ግን ሁልጊዜም አያርስም። መሬቱ ከተዘጋጀ በኋላ የተለያዩ እህሎችን ይዘራል። ምርቱን ካገኘ በኋላም እንደ ዘሩ ሁኔታ ለመከር መሰብሰቢያ የተለያዩ መንገዶችን ይጠቀማል። የትኛውንም ዓይነት የመውቂያ ዘዴ ቢጠቀም፥ እህሉን ለመጉዳት ተደርጎ የሚሠራበት ሁኔታ አይኖርም።

እግዚአብሔርም ከሰው ልጆች ጋር ተመሳሳይ አሠራርን ይከተላል። ገበሬ እንዴትና መቼ ማረስ እንዳለበት እንዲያውቅ ጥበብን የሚሰጠው እግዚአብሔር ነው። ይህን ጥበብ ለገበሬ የሚሰጥ ከሆነ፥ ከሕዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት የሚጠቀምበት ጥበብና ምክር እጅግ የላቀ መሆኑ እሙን ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚቀጣው ለማጥፋት አይደለም። ይልቁንም ከፍተኛ ፍሬ ለማውጣት ይፈልጋል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ሁልጊዜም በፍርድ ሲያርሳቸው አይኖርም። ወይም ደግሞ በጠላቶቻቸው ስደት ሲወቃቸው አይከርምም። እግዚአብሔር ለራሱ ዓለማ ሊጠቀም የሚፈልጋቸውን ዘሮች (አይሁዶች) አያጠፋቸውም። ይልቁንም የትኛው ዘር የቱ ጋ መዘራት እንዳለበት፥ ምን ያህል በቆሎ ስንዴ፤ ከሙን፥ ወዘተ. . . መዘራት እንዳለበት በመወሰን መስኩን በጥንቃቄ ያቅዳል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍሬያማ ሕይወትና ለራሱ ክብር በከፍተኛ ጥንቃቄ ይሠራል። (ማስታወሻ፡ የእግዚአብሔር ዓላማዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ ስለሚለወጡ የሰው ልጅ መንገዶቹን ሊተነብይ አይችልም። በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር ዕቅዶች ኢየሩሳሌምን በ701 ዓ.ዓ. እንዲያድን አድርገውታል። በሌላ ጊዜ ግን የእግዚአብሔር ዕቅዶች በ586 ዓ.ዓ. ኢየሩሳሌምን እንዲደመስስ አድርገውታል። እግዚአብሔር በአንድ ወቅት በአንድ መንገድ ተግባሩን አከናውኗል ማለት ሁልጊዜም እንደዚያው ያደርጋል ማለት አይደለም። የምናውቀው ነገር ቢኖር የመጨረሻው ውጤት የበለጠ ውጤታማና ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጣ መሆኑን ነው።) እግዚአብሔር የአይሁድን ሕዝብ ማረስ የሚያቆምበት ዘመን ይመጣል። በሚገባ ተወቅቶ የተበጠረ ስንዴ ለዳቦ እንደሚጠቅም ለእግዚአብሔር የሚጠቅሙ ይሆናሉ።

ይህ ለእስራኤል እውነት ከሆነ፥ ለእኛም እውነት ነው። እግዚአብሔር ከኃጢአታችን ለማንጻት ወይም እምነታችንን ለማጠናከር በቅጣት የሚያርሰን ወቅት ይኖራል። ይህም ቅጣት ደግሞ ስደት፥ በሽታ፥ የወዳጅ ሞት፥ የሥራ ማጣት ወይም ሌሎች ብዙ ነገሮችን ሊያካትት ይችላል። እምነታችንን ለመተው ወይም በእግዚአብሔር ላይ ለማጉረምረም ልንገደድ እንችላለን። ነገር ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቅ አለብን። እግዚአብሔር ነገሮችን የበለጠ ጠቃሚ ለማድረግ ይሠራል እንጂ አያጠፋም። ከቅጣቱ ስንማር ያ የቅጣት ወቅት ያልፋል። ሌሎችም የቅጣት ወቅቶች ይመጣሉ። የሚመጡት ግን እኛን ለማጥፋት ሳይሆን የበለጠ ፍሬያማ ሊያደርጉን ነው (ዕብራውያን 12፡4–11 ተመልከት)።

9ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እግዚአብሔር እንድታድግ ለመርዳት በሕይወትህ የተለያዩ ቅጣቶችን ሲያመጣ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር በቅጣት መካከል እንደማያጠፋ መገንዘቡ አስፈላጊ የሆነው ለምንድን ነው?

ኢሳይያስ 29

10ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 29ን አንብብ። (ሀ) በቁጥር አንድ «ወዮላት!» የተባለላት ከተማ ማን ነች? (ለ) እግዚአብሔር በአርኤል ላይ የሚያመጣው ፍርድ ምንድን ነው? (ቁ. 1–4 አንብብ)። (ሐ) እግዚአብሔር በጠላቶቿ ላይ የሚያደርገው ምንድን ነው? (ቁ. 5–8)። (መ) ነቢያት ምን ሆኑ? (ሠ) እግዚአብሔር የግብዝነት አምልኮ በሚያካሂዱት ሰዎች ላይ ምንን እንደሚያመጣ ተናገረ? (ረ) ሦስተኛው «ወዮ» የተነገረው ስለ ማን ነው? (ቁ. 15)። ስለ እግዚአብሔር የያዙት የተሳሳተ አሳብ ምን ነበር? (ሰ) ለድሆችና ለደንቆሮዎች ምን ይሆናል? (ሸ) ጨካኞችና ፌዘኞችስ? (ቀ) እግዚአብሔር በአርኤል የሚያከናውነው ተግባር የመጨረሻ ውጤት ምን ይሆናል? (በ) የዚህን ምዕራፍ ዐቢይ ትንቢት በራስህ አገላለጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

## 2. ሁለተኛው ‹ወዮ› በኢየሩሳሌም ላይ (ኢሳ. 29፡1–14)

### ሀ. የኢየሩሳሌም ዝቅ ማለት (ኢሳ. 29፡1–4)

ኢሳይያስ መዲናዪቱን በሰማርያ ካደረገችው እስራኤል የይሁዳ ርእሰ-ከተማ ወደሆነችው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰ። ኢሳይያስ ኢየሩሳሌምን «አርኤል» ሲል ይጠራታል። ምሑራን ይህ የኢየሩሳሌም መጠሪያ ከየት እንደመጣና ምን ማለት እንደሆነ በአሳብ ይለያያሉ። አንዳንዶች ኢሳይያስ ከሁለት የዕብራይስጥ ቃላት የፈጠረው ስም እንደሆነ ይናገራሉ። ለቃሉ ከቀረቡት ፍችዎች መካከል «የእግዚአብሔር አንበሳ፥ የእግዚአብሔር ቤት፥ የመሠዊያ ምድጃ» የሚሉ አሳቦች ይገኙባቸዋል። ኢሳይያስ በተጨማሪም ኢየሩሳሌምን «የዳዊት መናገሻ» ሲል ጠርቶአታል። ከዳዊት መንገሥ በፊት፥ ኢየሩሳሌም ኢያቡስ ተብላ ትጠራ የነበረች ስትሆን፥ በኢያቡሳውያን ቁጥጥር ሥር ነበረች። ዳዊት የእስራኤል ንጉሥ ሲሆን፥ ከተማዪቱን በመውረር የእስራኤል ርእሰ-ከተማ አደረጋት (2ኛ ሳሙ. 5፡7–9)።

ምንም እንኳ ነቢያት በኢየሩሳሌም ስለሚመጣው ውድመት ቢተነብዩም፥ የከተማዪቱ ሕይወት እምብዛም አልተሻሻለም ነበር። የተለያዩ ሃይማኖታዊ በዓላት በየዓመቱ ይካሄዱ ነበር። በውጫዊ ገጽታቸው የተሟሟቁ ሃይማኖታዊ በዓላት ሲካሄዱ፥ ሕዝቡ ከኃጢአታቸው የተነሣ የሚመጣባቸውን ፍርድ በፍጥነት ዘነጉ። በምጸታዊ አነጋገር፥ ኢሳይያስ ሕዝቡ የተለመደ አኗኗራቸውን እንዲቀጥሉ ነግሮአቸዋል። አንድ ቀን ግን ያ የተለመደ አኗኗር ያከትማል። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ዳዊት አንድ ቀን እንደወረራት ይወራታል። አሦር ኢየሩሳሌምን የምታጠቃበት ሁኔታ በተለይ በኢሳይያስ አእምሮ ውስጥ የነበረ ሲሆን፥ ቀጣዩ የባቢሎን ምርኮም እንዲሁ ይታየው ነበር። ከተማዪቱ ለሙታንና ለምርኮኞች ታነባለች።

ብዙዎች ስለሚሞቱ ኢየሩሳሌም ሰዎች የሚሠውባት መሠዊያ ትመስላለች። (በዕብራይስጥ ቋንቋ፥ «የመሠዊያ ምድጃ» የሚለው ቃል አርኤል እንደ ማለት ነው። አንድ የማብራሪያ መጽሐፍ አዘጋጅ አርኤል ማለት «የመሠዊያ ምድጃ» ማለት እንደሆነና በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ውስጥ የሚካሄደውን አምልኮና መሥዋዕት እንደሚያመለክት ያስባል። በቤተ መቅደሱ ያለው እግዚአብሔር አዳኝ እንደሆነ ሁሉ መሠዊያም የደኅንነት ስፍራ ተደርጎ ይታሰብ ነበር። አይሁዶች ያለ ምንም የልብ ለውጥ ለእግዚአብሔር ውጫዊ መሥዋዕት ማቅረቡ በቂ እንደሆነ ያስቡ ነበር። ብዙ መሥዋዕቶች እስከቀረቡለት ድረስ እግዚአብሔር ስለ ልባቸውና ሕይወታቸው የሚገደው አልመሰላቸውም። በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር ውጫዊ የመሥዋዕት አቅርቦቶች ደስ እንደማያሰኙት ይናገራል። ይልቁንም ልባቸውን ስላልለወጡ እግዚአብሔር ጠቅላላውን የከተማ ነዋሪ ወደ መሠዊያነት ይለውጠዋል። በዚያም በጦርነቱ የሚሞቱ ሰዎች እንደ መሥዋዕት ይሆናሉ። ስለሆነም መሠዊያው መሥዋዕቶችን እንደሚያቃጥል ሁሉ የእግዚአብሔር የመሠዊያ ቁጣ ይበላቸዋል።)

በዚህ ስፍራ እግዚአብሔር የከተማዪቱን መደምሰስ አልተነበየም። ትንበያው ወደ በኋላ ይመጣል። ኢሳይያስ ያተኮረው የሕዝቡ ኩራት እንደሚዋረድ በመግለጹ ላይ ነው። ከፍተኛ ውርደት የሚደርስበት ጊዜ ይመጣል። አንድ ምርኮኛ በሠራዊቱ ጄኔራል እግር ሥር እንዲንበረከክና ምሕረትን እንዲለምን እንደሚደረግ ሁሉ፥ ኢየሩሳሌምና የይሁዳ ሕዝብም በከፍተኛ ደረጃ ዝቅ ይላሉ። ሊያደርጉት የሚችሉት ነገር ቢኖር በኢሳይያስ አስተሳሰብ እየተዋጋቸው ባለው ታላቁ ሠራዊት ማለትም በእግዚአብሔር ፊት ወድቆ ምሕረትን መማጸን ብቻ ነበር። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለመውጋት የአሦርን ሠራዊት ተጠቅሞአል። ይህ ትንቢት እንዴት እንደተፈጸመ በኢሳይያስ 36–37 እናጠናለን።

### ለ. እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ጠላቶች ያጠፋል (ኢሳ. 29፡5–9)

የኢሳይያስ ትንቢት ከጽልመትና ጥፋት በፍጥነት ወደ ድል ይሻገራል። እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ለማዋረድ የአሦርን ሠራዊት ከተጠቀመ በኋላ እግዚአብሔር ወደ አሦራውያን ይመለሳል። (በዚህ ስፍራ አሕዛብ የተባሉት የአይሁድ ጠላቶች ናቸው።) አሦራውያን ከመቅጽበት ይወድሙና እንደ ገለባ ይበናሉ። ለውጡ እጅግ ቅጽበታዊ ስለሚሆን በኢየሩሳሌም ከተማ ላይ የተሰነዘረው ጥቃት ሲነጋ እንደሚዘነጋ የሌሊት ሕልም ይሆናል።

ኢሳይያስ የኢየሩሳሌምን ጥቃትና በፍጥነት ነፃ መውጣት በሕልሙ በልቶ ከሚጠግብ ረሃብተኛ ጋር ያነጻጽረዋል። ሲነቃ ግን እንደተራበ ይሆናል። ወይም ደግሞ በሕልሙ እንደሚጠጣና ሲነቃ ግን

እንዲተጠማ እንዳለ ሰው ይገልጸዋል። ኢሳይያስ አላሚዎቹ አሥራውያን እንደሆኑ የሚናገር ከሆነ፥ ኢየሩሳሌምን እያጠቁ ሳሉ በቅርቡ እንደሚያጠፋዋት የሚያስቡ መሆናቸውን መግለጹ ነው። ከድል ሕልማቸው ይነቁና ከተማዪቱን ለማጥፋት ባለመቻላቸው እንደተራቡና እንደተጠሙ መሆናቸውን ይገነዘባሉ። አሥራውያን በፍጥነት ስለሚደመሰሱ አይሁዶች ይዘነጉዋቸዋል። ኢሳይያስ አይሁዶች እንደሚያልሙ የሚናገር ከሆነ፥ አይሁዶች ከአሥራውያን የጥቃት ሕልም ከነቁና እግዚአብሔር ነፃ ካወጣቸው በኋላ፥ የቀደመውን አሰቃቂ የጥቃት ገጠመኝ እንደሚረሱ መግለጹ ይሆናል። እግዚአብሔር ራሱ ያለ ምንም የሰው ጦር እገዛ በአሥር ላይ ይዘምታል። እንደ ኃያል ማዕበል የአሥርን ሠራዊት ሙሉ ለሙሉ ያጠፋል።

በ701 ዓ.ዓ. የአሥር ሠራዊት የይሁዳን ጠቅላላ ግዛት በመውረር ወደ ኢየሩሳሌም በሮች ደረሰ። ኢየሩሳሌም ወዲያው እንደምትሸነፍ ግልጽ ነበር። በከተማዪቱ ውስጥ ጭንቀት ነገሠ። ንጉሡ ሕዝቅያስ ወታደሮቹ የመከላከል ዓቅም እንደሌላቸው ያውቅ ነበር። በጭንቀት እንደተወጠረ፥ የአሥርን ንጉሥ ደብዳቤ ወስዶ በቤተ መቅደስ ውስጥ በእግዚአብሔር ፊቱ አኖረው። በተዋረደ መንፈስ ደብዳቤውን ለእግዚአብሔር በማንበብ በጉዳዩ ውስጥ ጣልቃ እንዲገባ ተማጸነው። እግዚአብሔርም ሰማው። የአሥርን ሠራዊት በኢየሩሳሌም ላይ ያመጣው እግዚአብሔር ነበር። የሠራዊቱም መምጣት ዓላማውን ከዳር አድርሶአል። ይኸውም የይሁዳ ሕዝብ ራሱን ዝቆ አድርጎ ወደ እግዚአብሔር እንዲመለስ ማድረግ ነበር። ከዚያ በኋላ እግዚአብሔር የፍርድ መሣሪያው ወደነበረው ወደ አሥር ሠራዊት ፊቱን መለሰ፤ አጠፋውም። በአንዲት ምሽት አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ወታደሮች አለቁ። ሠራዊቱ ዳግም ችግሮችን ላለመፍጠር ተገዝቶ ከኢየሩሳሌም ወጣ። ለኢሳይያስ እንደተነገረው፥ የእግዚአብሔር ትንቢቶች ተፈጸሙ።

(ማስታወሻ፡ አንዳንድ ምሑራን ይህ ክፍል ስለ አንዲት ከተማ ሳይሆን፥ የእግዚአብሔርን ፍርድ የሚቀበሉትን ጠላቶች ሁሉ እንደሚያካትት ያስባሉ። ስለሆነም ይህ ትንቢት ድርብ ፍች እንዳለው፥ ማለትም መጀመሪያ ለአሥራውያን፥ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለመግዛት በሚመጣበት በመጨረሻው ዘመን ተፈጻሚነት እንደሚያገኝ ያስረዳሉ። ለዚህ ነው ወደ በኋላ በምዕራፉ ውስጥ የተጠቀሱት ክፍቶች መንፈሳዊ ይዘት ያላቸውና እንደ ጦርነት ወይም ምርኮኛነት ውጫዊ ያልሆኑት። ክፍት የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚያሸንፍ ሊመስል ይችላል። ይህ ሊጋፈጡት የሚገባው ቅዠት ነው። የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን በረከቶች ይናፍቃሉ።

ይሁንና፥ ቅዠቱ የሚያበቃው ኢየሱስ ክርስቶስ ለመግዛት ሲመጣ ብቻ ነው። በዚያን ጊዜ በምግብና በመጠጥ የተመሰለው የእግዚአብሔር በረከት በትክክል የእነርሱ ይሆናል።)

ሐ. የይሁዳ መለያ የሚሆን መንፈሳዊ ድንዛዜ (ኢሳ. 29፡9–14)

ምንም እንኳ ኢሳይያስ የኢየሩሳሌምን አካላዊ ነፃ መውጣት የተነበየ ቢሆንም፥ እንዳለመታደል ሆኖ መንፈሳዊ ባሕርያቸው አልተፈወሰም። በመንፈሳዊ ሁኔታዋ ኢየሩሳሌም ወደ ጠለቀ አዘቅት ትገባለች። ይህም የኋላ ኋላ በባቢሎን ወደ መደምሰስና ወደ ምርኮ የሚመራት ይሆናል። ጥሪውን በተቀበለበት ጊዜ ለኢሳይያስ የተሰጠው ትንቢት ይፈጸማል። የሕዝቡ መንፈሳዊ ሁኔታ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማትና ለመታዘዝ ከማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳል (ኢሳ. 6፡10)። ለእግዚአብሔር ነገሮች አእምሮአቸውን ለመጨፈን መርጠዋል። በትክክል ሊያስቡ እንደማይችሉ ሰካራሞች፥ የእግዚአብሔርም ሕዝብ በትክክል ሊያስቡና ሁኔታቸውን ሊረዱ አይችሉም። ስለሆነም ኢሳይያስ ቀደም ሲል በመረጡት መንገድ እንዲሄዱ ይመክራቸዋል። ሕዝቡ በባቢሎን እስኪደመሰስ ድረስ ይኸው ሁኔታ ይቀጥላል።

1. ነቢያት መንፈሳዊ ራእዮችን አያገኙም። እግዚአብሔር ለይሁዳ ሕዝብ መነቃቃትን ለማምጣት በመሻት ለብዙ ዓመታት ነቢያትን ሲልክ ቆይቶ ነበር። ምንም እንኳ ጊዜያዊ መንፈሳዊ መነቃቃቶች ቢከሰቱም፥ ዘለቄታዊ ለውጥ አልተስተዋለም ነበር። ነገሥታት እንደ አማካሪዎቻቸው አድርገው የሚጠቀሙባቸው በርካታ ሐሰተኛ ነቢያት ነበሩ (ለምሳሌ 1ኛ ነገ. 22፡1–8፤ 2ኛ ዜና 18፡1–27)። እግዚአብሔር የሕዝቡ መንፈሳዊ መሪዎች የነበሩት ነቢያት ፈቃዱን አይተው የሚረዱበትን ችሎታ በመንሳት እንደሚፈርድባቸው ገልጾአል። በመጭው ቀውጢ ወቅት ራሳቸውንም ሆነ ሌሎችን ሊረዱ የማይችሉና ዳሩ ግን ወዲያ ወዲህ እንደሚንገዳገዱ ሰካራሞች ይሆናሉ። ወይም ደግሞ ጭልጥ ካለ እንቅልፍ ነቅቶ ዓይኖቹን ለመግለጥ እንደሚያሻሽ ሰው ይሆናሉ። ነቢያት ከሌሉ ሕዝቡ የሚመጣበትን ሳያውቅ እንደ ዓይነ ስውር ሰው ሲዳብስ ይኖራል። እግዚአብሔር እስራኤል ለአሕዛብ ብርሃን ትሆን ዘንድ ጠርቶታዋል (ኢሳ. 42፡6፤49፡6 51፡4)። እነርሱ ግን ዓይነ ስውር ሆኑ። የአሦር ጭቆና በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ሊያደርጋቸው ይገባ ነበር። እነርሱ ግን ግራ ተጋቡ። ሆን ብለው እግዚአብሔርን ላለመስማት ፈለጉ። ከዚህም የተነሣ ለእግዚአብሔር ሥራ ዓይነ ስውራን ሆኑ። እውነቱን አይተው ሕይወታቸውን እንዳይለውጡ እግዚአብሔር የእንቅልፍን መንፈስ በመላክ ይፈርድባቸዋል።

የእግዚአብሔር ሕዝብ ለእግዚአብሔር ቃል ይፋዊ አለመታዘዝ ሲኖራቸው፥ ቅጣቱ ከሚፈጸምባቸው መንገዶች አንዱ ለእግዚአብሔር

መንገዶች በታወሩና ለድምፁ በደነቆሩ መሪዎች ሥር መተዳደሩ ነው። መንፈሳዊ መሪዎች ከሌሉ ሕዝቡ ይበልጥ ከእግዚአብሔር እያፈነገጠ መሄዱን ይቀጣላል። ዕድሉ እያለ የእግዚአብሔርን ቃል ለመስማት ያለመፈለጋቸውን ፍሬ ያጭዳሉ።

2. ቃለ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ይሰወራል። እግዚአብሔር ራእዩን እንደ ኢሳይያስ ላሉት ነቢያት ሰጥቶአቸዋል። እነርሱም መልእክቱን በጽሑፍ አሰፈሩት። አይሁዶች የእግዚአብሔር ቃል በእጃቸው እያለ እንኳ እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል የሚናገረውን አይረዱም ነበር። የኢሳይያስ ትንቢቶች ለእነርሱ ጠቃሚ ቢሆኑም የተዘጉ ነበሩ። የኢሳይያስ ትንቢት በመጽሐፍ መልክ የተጠረዘ ላይሆን ስለሚችል በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ምናልባትም የእግዚአብሔር መገለጥ ሊሆን ይችላል። የመጽሐፍ ጥቅልል በሰም ይታሸግ ነበር። ለማንበብ ሲፈለግ ማኅተሙ መፈታትና ወረቀቱ መተርተር ነበረበት። መጽሐፉ በሰም እስከታተመ ድረስ ማንበብ የሚችሉትን ጨምሮ ለማንም የሚሰጠው ትርጉም አይኖርም። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር ቃል የሆነው የመጽሐፍ ጥቅልል (የኋላ ኋላ ትንቢተ ኢሳይያስን ጨምሮ) ሁሉም ያነብ ዘንድ ከእጁ ላይ የተቀመጠ ቢሆንም፥ በሰም እንደታሸገና ለንባብ እንደተከለከለ ዓይነት ነበር። ይህም መንፈሳዊ ግንዛቤ ስላልነበራቸው ነው። ኢሳይያስ በምድሪቱ የሚገኙ ሰዎች ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ለማንበብ መንፈሳዊ ብቃት እንደሌላቸው አመልክቷል። ትንቢቱ የታተመ ወይም የተዘጋ በመሆኑ የተማሩት ሊያነቡት አይችሉም። ያልተማሩት ደግሞ ማንበብ ስለማይችሉ አያነቡትም። ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መገለጥ ለሕዝቡ በግልጽ የቀረበላቸው ቢሆንም፥ እግዚአብሔር የሚላቸውን ለማስተዋል የሚያስችል መንፈሳዊ ብቃት አልነበራቸውም።

3. ከልብ ሳይሆን ከባህል በመነጨ አምልኮ ይሰግዱለታል። አይሁዶች ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡትን አምልኮ ሙሉ ለሙሉ ይተዉታል? መሥዋዕቶቻቸውን ወደ መቅደሱ መሠዊያ ማምጣታቸውን ያቆማሉ? ወደ ሃይማኖታዊ በዓላትስ መምጣታቸውንስ ይተዋሉን? እንደዚያማ አያደርጉም። እንዲያውም አይሁዶች የበለጠ መንፈሳዊ እንቅስቃሴ ሲያደርጉና አንዳንድ ጊዜም ሙሴ ከሰጣቸው ሕግጋት በተጨማሪ ለአምልኮተ እግዚአብሔር የራሳቸውን ሕግጋት አክለው ሲሰግዱ እንመለከታለን። ይሁንና፥ እነዚህ የአምልኮ ተግባራት የሚካሄዱት ከልማድ ወይም ከባህል በመነጨ ስሜት ነበር። ለእግዚአብሔር እንደሚታመኑ በቃላት ቢገልጹም ልባቸው ከእግዚአብሔር የራቀ ነበር። (በማቴዎስ 15፡9 ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ የነበሩትን ፈሪሳውያን ለማመልከት ኢሳይያስ 29፡13ን ተጠቅሞአል።)

አምልኮ የሚመነጨው ከልብ ነው። አምልኮ በቤተ ክርስቲያን ሕንጻ ውስጥ ስላለን ብቻ የሚካሄድ ነገር አይደለም። ወደ ቤተ ክርስቲያን በምንሄድበት ጊዜ በልባችን ካልተዘጋጀን፥ የአምልኮ ሥርዓት ሲፈጸም በስፍራው ተገኝቶ መታዘብ ማለት ለእግዚአብሔር ምንም ማለት አይደለም። በአዘቦት ቀናት የሚታዘዝ ልብ ከሌለን የሰንበት አምልኮአችን እግዚአብሔርን አያስደስተውም። የእግዚአብሔርን ቃል እስካልተጻረረና አምልኮአችንም ከልባችን የሚፈልቅ እስከሆነ ድረስ የአምልኮ ባህሎችን ማዳበራችን እግዚአብሔርን አያሳስበውም። የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ከልብ የሚመነጨውን እውነተኛ አምልኮ የሚያቅቡ ባህሎችን(ትውፊቶችን) ላለማስለመድ መጠንቀቅ ይኖርባቸዋል።

11ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ዛሬ ክርስቲያኖች ከልባቸው ሳይሆን ከሰዎች ደንብ ቃላትና ትውፊት ከልብ ያልሆነ ከንቱ አምልኮ ሊያቀርቡ የሚችሉባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ለ) አምልኮ ከቃላት በላይ መሆኑንና ከልብ የወጣ መሆኑን ለማወቅ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

እግዚአብሔር ሕዝቡን አንድ ቀን ከመንፈሳዊ ድንዛዜ ሊቀሰቅሳቸው ቃል ገብቷል። ነገር ግን እነርሱ በጠበቁት መንገድ አይሆንም። ከግብፅ ባወጣቸውና ወደ ከነዓን ባመጣቸው ጊዜ በተአምራት ሕዝቡን አስደንቋል (ዘጸ. 15፡11)። በዚህ ጊዜ ግን በፍርዱ ያስደንቃቸዋል። የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደሚፈረድባቸው የሚያስቡት በጥቂቱ ነው። ከእውነት ርቀው የሚባዝኑትም ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ባልተጠበቀ መንገድ ይሠራል። ጥፋት በሚመስለው የባቢሎን ወረራ አይሁዶችን ያጠራል። ከዚያም ዘሩባቤል፥ ዕዝራና፥ ነህምያን በመሳሰሉ ሰዎች አመራር ዳግም ግንባታን ያካሂዳል። እግዚአብሔር በፍርድ ሲመጣ የሰው ጥበብ ጥቅም እንደሌለው ይገለጣል። ምክንያቱም ያ ጥበብ ሊያድናቸው አይችልምና።

### 3. ሦስተኛው ‹ወዮ› እግዚአብሔርን ልናታልል እንችላለን ለሚሉ ሰዎች (ኢሳ. 29፡15–24)

#### ሀ. እግዚአብሔርን ለማታለል የሚፈልጉ ሰዎች ራሳቸው ተታለዋል (ኢሳ. 29፡15–16)

አንድ ሰው ግልጽ ኃጢአተኛ ካልሆነና ኃጢአቱን የመደበቅ ዝንባሌ ካልኖረው በቀር፥ አብዛኛው ኃጢአት የሚፈጸመው «ማን ያየኛል?» ከሚል የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። ክርስቲያን ዝሙት የሚፈጽመው በግልጽ ሳይሆን በድብቅ ነው። በሥራ ቦታ ሌባው ገንዘብ የሚሰርቀው ሌሎች ሊያዩት በሚችሉበት ሁኔታ አይደለም። እነዚህ ሰዎች የዘነጉት ነገር ቢኖር ሰው ባያያቸውም እግዚአብሔር እንደሚያያቸው ነው። ከእርሱ የተሰወረ የለምና። (ሰዎችም እንኳ የኋላ ኋላ ጉዳዩን አሽትተው መድረሳቸው የማይቀር ነው።)

አይሁዶች እግዚአብሔር አላየንም በሚል ኃጢአታቸውን ከእግዚአብሔር ለመሰወር በመጣር ላይ ነበሩ። በዚህ ስፍራ ኢሳይያስ የሚያስበው አንድ ሁነኛ ኃጢአት ይኑር አይኑር የምናውቀው ነገር የለም። ኢሳይያስ ይህንን ትንቢት ከመናገሩ ጥቂት ቀደም ብሎ አካዝ ከአሦር ጋር ስምምነት ተፈራርሞ ነበር። በእነዚህ ቀናት ደግሞ ሕዝቅያስ ከግብፅ ጋር ስምምነት ለማድረግ ይሞክር ነበር። እግዚአብሔር ከዚህ እርምጃ እንዲታቀቡ ቢመክራቸውም በጅ አላሉም። ይሁንና፥ አሥራውያን፥ ሕዝቡና እግዚአብሔርም ሁኔታውን እንዲያውቁ ስላልፈለጉ በምሥጢር ነበር የፈጸሙት።

አይሁዶች እግዚአብሔር አያይም ብለው ማሰብ ሲጀምሩ፥ ስለ እግዚአብሔር በጣም የተሳሳተ አሳብ ይዘው ነበር። አንዳንድ ጊዜ እንደምናስበው፥ እነርሱም እግዚአብሔር እንደ ሰው የተወሰነ ነው ብለው አሰቡ። ሌላ ሰው ኃጢአታችንን አለማየቱ እግዚአብሔርም ኃጢአታችንን እንዳላየ አድርገን እንድናስብ ያደርገናል። እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂና ሁሉን ተመልካች እንደሆነ እንዘነጋለን። ሽክላ ሠሪው አምላክ እርሱ ከሠራው ሸክላ (ከሰው ልጅ) እጅግ የላቀ ነው። ሰው ከፈጠረው አምላክ በላይ እጠበባለሁ ማለቱ ምንኛ የተበላሸ አስተሳሰብ ነው! (መዝ. 94)።

**ለ. አንድ ቀን እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ይለውጣል (ኢሳ. 29፡17–21)**

በአይሁዶች መካከል አንዳንድ መንፈሳዊ ሰዎች ነበሩ። የዓለም ክፋት ሁልጊዜም ባለማቋረጥ እንደሚቀጥል በማሰብ ለእግዚአብሔር መኖራቸውን ሊተዉት ይቀላቸው ነበር። በአብያተ ክርስቲያናት መካከል የሚካሄደው ጦርነትና ክርስቲያኖች እርስ በርሳቸውና ከእግዚአብሔርም ጋር ፍቅር እንዳይመሠርቱ የሚከላከለው ኃጢአት ለዘላለም የሚቀጥል ይመስላል። እግዚአብሔር ግን ሁሉም ነገር የሚለወጥበትን ቀን አመልክቷል። ኢሳይያስ እንደገና ለሕዝበ እግዚአብሔር ወደሚመጣው የመቤዠት ቀን አሳቡን አዘነበለ። እንዲያውም እግዚአብሔር ይህ ቀን በቅርብ ጊዜ እንደሚፈጸም ተናግሯል። ይህ በሕዝቅያስ ዘመን የተከሰተውን ተሐድሶ የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እግዚአብሔር ጊዜውን የጠቀሰው ከራሱ አመለካከት አንጻር ነው። እግዚአብሔር እንደኛ በጊዜ ያልተገደበ አምላክ በመሆኑ፥ በተለያዩ የተስፋ ቃሎቹ መካከል የሚፈጸሙት ክፍለ-ዘመናት ለእርሱ አጭር ጊዜያት ናቸው። እግዚአብሔር በአጭር ጊዜ ውስጥ ዘላለማዊ መንግሥቱን እንደሚመሠርት ተናግሮአል። (ይህ ጴጥሮስ 1000 ቀናት ለእግዚአብሔር እንደ አንድ ቀን ነው ካለው አሳብ ጋር ይመሳሰላል 2ኛ ጴጥ. 3፡8።) በዚያን ጊዜ ብዙ ነገሮች ይካሄዳሉ።

1. ሊባኖስ እንደ ፍሬያማ እርሻ ፍሬያማውም እርሻ እንደ ዱር ይሆናል። ኢሳይያስ ይህን ሲል ሊያስተላልፍ የፈለገው አሳብ ምን እንደነበር መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። ምናልባትም የእግዚአብሔር መንግሥት በሚመጣበት ጊዜ ነገሮች ተገላቢጦሽ ውጤት እንደሚኖራቸው እየገለጸ ይሆናል። ሊባኖስ በታላቅ ደንነቱ ይታወቅ ነበር። ያ ኩራቱ ነበር። ነገር ግን ወደ ሜዳነት ይለወጥና ኩራቱ ይዋረዳል። ኃያል የምትመስለው አሦር (እና በኋላም የዓለም አገሮች) ዝቅ ትላለች። በተቃራኒው፥ እንደ ሜዳ ዝቅ ብለው የነበሩት (ይህ ምናልባትም ኢየሩሳሌምን፥ ይሁዳንና የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሁሉ የሚያመለክት ይሆናል) አንድ ወቅት ሊባኖስ ወደነበረበት የዱርነት ደረጃ ይለወጣሉ። አንዳንድ ምሑራን የዚህን አሳብ ምንነት ሲያስረዱ፥ እግዚአብሔር ምድርን ስለሚለውጥ ለምለም የእርሻ መሬት ተደርጎ ይታሰብ የነበረው ስፍራ ሁሉ በአንጻራዊነት በረሃን እንደሚመስል ያስተምራሉ።

2. እግዚአብሔር የሕዝቡን መንፈሳዊ ድንዛዜ ያስወግዳል። በመንፈሳዊ ድንቁርና ውስጥ የነበሩት ሰዎች የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው መረዳት ይጀምራሉ። ከኃጢአት የተነሣ በመንፈሳዊ ዓይነ ስውርነት የኖሩ ሰዎች የወንጌሉን ብርሃን ያያሉ። ከኃጢአት ጽልመት ይወጣሉ። የተዋረዱና የደኸዩ ከፍ ተደርገው በእግዚአብሔር ደስ ይሰኛሉ። እግዚአብሔር ድሆችና በተዋረደ ሁኔታ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ከመቅጽበት እንደሚባረኩ እየተናገረ አይደለም። ይልቁንም ኢሳይያስ «ደንቆሮ፥» «ዕውር፥» «የተዋረደ» እና «ድሀ» እያለ የሚናገረው ወደፊት የሚለወጠውን የሰዎችን መንፈሳዊ ይዘት ነው። እግዚአብሔር ሕዝቡ ቃሉን እንዳይረዳ ያደረገውን መንፈሳዊ ድንዛዜ ያስወግዳል። ይህ በኢሳይያስ 29፡13–14 ከተጠቀሰው መርገም በአንጻራዊነት የተገለጸ ነው።

3. እግዚአብሔር ሥራውን በመቃወም የጸኑትን ሰዎች ያጠፋል። የመጨረሻው ዘመን የበረከትና የታላቅ ፍርድ ወቅት ይሆናል። ኢሳይያስ ከእግዚአብሔር ጅምላ ጥፋት የሚያመጣባቸውን አቋም የያዙ የተለያዩ ሰዎችን ጠቃቅሶአል። ርኅራኄ ሳይኖራቸው የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚጨቁኑ ጨካኞች፥ በእግዚአብሔር፥ በእግዚአብሔር ነገሮችና በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚሳለቁ ፌዘኞች፥ ባለማቋረጥ ክፋትን ለማድረግ የሚፍጨረጨሩ ክፉዎች ነበሩ። በፍርድ ችሎት ንጹሑን ሰው በደለኛ የሚያደርጉ፥ በተንኮል ሰውን አጥምደው ሀብቱን የሚያስወስዱበት፥ ወይም ደግሞ ፍትሕን ለማዛባት የሐሰት ምስክር የሚጠሩ ሰዎች ነበሩ። ሕይወታቸው በእግዚአብሔርና በመንገዶቹ ላይ በሚፈጽሙት በደል የተመሠረተ ሰዎች ዳግም በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ አበሳ እንዳያስከትሉ ሙሉ ለሙሉ ይደመሰሳሉ።

ሐ. እግዚአብሔር የያዕቆብን ቤት ይለውጠዋል (ኢሳ. 29፡22-24)

ከዘመን አብርሃም እስከ አሁን ድረስ፥ አይሁዶችና ሕዝበ እግዚአብሔር በሙሉ ለእግዚአብሔር ያላቸውን ታማኝነትና ታዛዥነት ለመጠበቅ ተቸግረዋል። ከዚህም የተነሣ እግዚአብሔር ብዙውን ጊዜ ኃፍረትን በሚያከናንብ ቅጣት ተገናኝቶአቸዋል። ነገር ግን አንድ ቀን ነገሮች ሁሉ መልካቸውን ይለውጡና እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጎበኛል። የሽንፈትንና የመረገጥን ኃፍረት ከአብርሃምና ከያዕቆብ ዘሮች ላይ ያነሣል። ከማያቋርጥ ጦርነት፥ ጥፋትና ጭቆና የተነሣ በፍርሃት የገረጣ ፊታቸውን ይለውጠዋል። እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ እስከሚተዋቸውና ዳግም እንደ ቃል ኪዳን ሕዝቡ እስከማይመለከታቸው ድረስ በኃጢአት እንደወደቁ በማሰብ የሚፈሩበትን ሁኔታ ያስወግደዋል። እግዚአብሔር አሁንም ለአይሁዶች ዕቅዶች አሉት። አንድ ቀን ለአብርሃም ቃል እንደገባለት ዘራቸውን ያበዛዋል።

ከዚህም በላይ እግዚአብሔር ልባቸውን ይለውጠዋል። እነርሱም በስሙ የተጠሩበትን አምላክ ያከብሩታል፤ የእግዚአብሔር ልጆች ነበሩና። አባቶቻቸው አብርሃምና ያዕቆብ ያደርጉት እንደነበረው አምላካቸውን ያመልኩታል። (ኢሳይያስ ወደ ኋላ ተመልሶ አብርሃምንና ያዕቆብን የጠቀሰው እግዚአብሔር ስለሰጣቸው ዘላለማዊ የተስፋ ቃሎችና በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ እንደጠበቃቸው ለማስታወስ መሆኑ አይጠረጠርም።) በቃላት ሳይሆን ለእግዚአብሔር ቅዱስ ትእዛዛት ራሳቸውን ሰጥተው በመኖር የእግዚአብሔርን ቅዱስነት ያጸናሉ። ዓለምን የፈጠረና ሁሉን የሚችል ጌታ አምላክ መሆኑን ተገንዝበው በፊቱ በመንቀጥቀጥ ከእርሱ ጋር በተስማማ መንገድ ይመላለሳሉ። እግዚአብሔርም የኩብላይነት መንፈሳቸውን ያስወግደዋል። ይከተሉት ዘንድም እውነተኛ መንፈሳዊ መረዳትን ይሰጣቸዋል። ለእግዚአብሔር በመታዘዝ መኖሩ የከበዳቸው ሁሉ የእግዚአብሔርን ቃል ይሰማሉ።

ምናልባትም ይህ ትንቢት በሕዝቅያስ ዘመንና አንዳንድ መንፈሳዊ ሰዎች ይሁዳ ላይ በነገሡባቸው ጊዜያት በከፊል ተፈጽሞ ይሆናል። ነገር ግን ከፍሉ በተሟላ ሁኔታ የሚፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስ ነው። የሺህ-ዓመት-አልባ አመለካከት የሚያራምዱ ወገኖች ይህ ክፍል በቤተ ክርስቲያን በከፊል እንደተፈጸመና በዘላለሙ መንግሥት ሙሉ ለሙሉ እንደሚፈጸም ይናገራሉ። የድኅረ-ሺህ-ዓመት አመለካከት ያላቸው ወገኖች ወንጌሉ እየተስፋፋ ሲሄድ በቤተ ክርስቲያን ይበልጥ እየተፈጸመ እንደሚሄድ ያምናሉ። የቅድመ-ሺህ-ዓመት እይታ ያላቸው ሰዎች ግን ይህ ትንቢት ወደፊት ከዚህ በበለጠ በቀጥተኛ መልኩ እንደሚፈጸም ያምናሉ። ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ

ምድር በሚመለስበት ጊዜ አይሁዶች ከዓለም አካባቢ ከተሰባሰቡት ሌሎች ሰዎች ሁሉ ጋር በደስታ ያመልኩ ዘንድ ልባቸውን እንደሚለውጥ ያምናሉ።

12ኛ ጥያቄ፦ ሀ) እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር እንድንዛመድ ስለሚፈልግበት ሁኔታ ቁጥር 23 ምን ይላል? ለ) ከእነዚህ መካከል ለማድረግ የሚከብደው የትኛው ነው? ሐ) ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በዚህ ክፍል የተጠቀሰውን አሳብ የማይፈጽሙባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው?

13ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ ምዕራፍ 28–29ን በራስህ አገላለጽ ጻፍ።

## ሁለተኛ ቀን — ኢሳይያስ 30–31

### ኢሳይያስ 30

ጌታቸው የታወቀ የቤተ ክርስቲያን መሪ ነበር። በወንጌላዊነት ያገለገለ ሲሆን፥ በእርሱ አገልግሎት እግዚአብሔር ትልቅ ቤተ ክርስቲያን መሥርቷል። በቤተ ክርስቲያን አካባቢዎች ሁሉ የታወቀ ሲሆን በሄደበትም ሰዎች ያከብሩት ነበር። ይህ ሰው ለጋብቻ የደረሰች ልጅ ነበረችው። ብዙ ሰዎች ልጂቱን ለልጆቻቸው ለማጫት ጌታቸውን ጠይቀውት ነበር። ልጂቱን ለማግባት የፈለጉት ወጣቶች በአብዛኛው ጥሩ መንፈሳዊነት የሚታይባቸውና ለወንጌል አገልግሎት የተዘጋጁ ነበሩ። ደመወዛቸው ግን ትንሽ ነበርና ጌታቸው ለልጁ የተሻለ ነገር አሰበ። እርሱ የፈለገው ነገር ቢኖር ዝነኛና ሀብታም ሰው እንድታገባለት ነበር። አንድ ቀን አንድ የታወቀ ነጋዴ ወደ ጌታቸው ዘንድ መጥቶ ልጁን ከራሱ ልጅ ጋር ለማጋባት እንደሚፈልግ ገለጸለት። ጌታቸው ስለዚህ ነጋዴ የሚነገረውን ያውቅ ነበር። ሰውዬው በጣም የደከመ ክርስቲያን መሆኑንና ልጁም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ጥሩ ስም እንደሌለው ያውቃል። ነገር ግን እግዚአብሔር ልጁን ሊለውጥ ይችላል ሲል አሰበ። ስለሆነም ልጁን ለዚህ ነጋዴ ልጅ ለመዳር ተስማማ።

14ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 30፡1–2 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር ጌታቸው ባደረገው ነገር ደስ የተሰኘ ይመስልሃል? ለምን? ለ) ጋብቻው ምን ምን ችግሮችን ሊያስከትል ይችል ይሆን? ሐ) ጌታቸው የያዘውና የኃጢአት ሥር የሆነው አመለካከት ምን ነበር? መ) ክርስቲያኖች የተሳሳተ ልብ ሊኖራቸውና እግዚአብሔር ደስ የማይሰኝበትን ውሳኔ ሊያስተላልፉ የሚችሉት እንዴት ነው?

የትኞቹም ዓይነት ቃል ኪዳኖች ለክርስቲያን አደገኛ ናቸው። ጌታቸው ልጁን ለጋብቻ በመስጠት ከሌላ ቤተሰብ ጋር ቃል ኪዳን መሥርቷል። የዚህ ሰው ልብ ንጹሕ ስላልነበር ብዙውም ሳይቆይ በጋብቻው ውስጥ የእሴቶች መጣስ ተከሰተ። እርሷ ወደ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ስትፈልግ፥ ባሏ ጓደኞቹን ጋብዞ ቤት ውስጥ ሲዝናና ለመዋል ይፈልጋል። ወዲያው ከፍተት ተፈጠረ። ሰውዬው

ከሌላ ሴት ጋር ያመነዝር ጀመር። ይህም የኋላ ኋላ ፍችን አስከተለ። በንግድ ቃል ኪዳኖችም ውስጥ ተመሳሳይ ነገር ሊፈጸም ይችላል። ክርስቲያን ካልሆነ ሰው ጋር ቀላል የንግድ ስምምነት በማድረግ የተጀመረው ተግባር ክርስቲያኑ አንዳንድ ሕገ ወጥና የረከሱ ልምምዶችን እንዲከተል ሊገፋፋው ይችላል።

የይሁዳ ሕዝብ በተመሳሳይ ችግር ውስጥ ተዘፍቆ ነበር። ታላቁ የአሦር ሠራዊት እየመጣባቸው ነበርና ሊከላከሉት እንደማይችሉ ተገነዘቡ። ስለሆነም ምናልባት ተባብረው ይቋቋሙ እንደሆነ በማሰብ ከሌላ ኃያል አገር ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ፈለጉ። በመሆኑም ይሁዳ ወደ ግብፅ ፊቷን መልሳ ቃል ኪዳን ተጋባች። ኢሳይያስ ግን ይህንን ተግባር በመቃወም ከእግዚአብሔር ዘንድ የተቀበለውን ቃል ነገራቸው። እግዚአብሔር ይህ በእርሱ ላይ ባለመታመን የወለዱት እርምጃ እንደሆነ ገለጸ። እግዚአብሔር ለአይሁዶች እንደሚጠነቀቅና ከጠላቶቻቸው እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶላቸው ነበር። ስለሆነም ለጥበቃ ሲሉ ወደ ሌላ አካል መመለሳቸው አሳባቸውን እንደቀየሩ ያመለክት ነበር። እግዚአብሔር ስለሌለበት፥ ይህ ቃል ኪዳን ለሽንፈት ይዳረጋቸው ነበር። ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ጋብቻ ሲናገር፥ ክርስቲያኖች ካልሆኑት ሰዎች ጋር ቃል ኪዳን እንዳያደርጉ አስጠንቅቆአል። «ብርሃን ከጨለማ ጋር ምን ኅብረት አለው?» ሲል ጠይቋል (2ኛ ቆሮ. 6፡14–18)። እኛም ዛሬ ለእግዚአብሔር ሙሉ ፍቅር ከሌላቸውና ሊያገለግሉትም ከማይፈልጉ ሰዎች ጋር በምናደርጋቸው ግንኙነቶችና ቃል ኪዳኖች ላይ ጥንቃቄ ልናደርግ ይገባል።

15ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ ምዕራፍ 30ን አንብብ። (ሀ) በቁጥር 1 እስራኤላውያን የተገለጹት እንዴት ነው? እግዚአብሔር ምን አድርገዋል ሲል ነው የሚወቅሳቸው? (ለ) ከግብፅ ጋር የምታደርገው ቃል ኪዳን ለይሁዳ የሚያመጣው ነገር ምንድን ነው? (ሐ) በደቡብ ስላሉ እንስሶች የተነገረው ሸክም ትርጉም ምንድን ነው? (መ) ኢሳይያስ በአይሁዶች ላይ ያቀረባቸውን ክሶች ዘርዝር (ቁ. 8–11)። (ሠ) የሚፈርሰውና ከግብፅ ጋር የተያያዘው ግድግዳ ትርጉም ምንድን ነው? (ረ) የይሁዳ ደኅንነት ከየት ይመነጫል? (ሰ) የይሁዳ ሕዝብ ከጠላቶቻቸው ለመሸሽ ሲሞክሩ ምን ይፈጠራል? (ሸ) እግዚአብሔር በቁጥር 18 የተገለጸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚሰጠው የተስፋ ቃል ምንድን ነው? (ቀ) እግዚአብሔር ከቀጣቸው በኋላ የአይሁዶች የመጨረሻ ውጤት ምን ይሆናል? (በ) እግዚአብሔር በሕዝቡ ፈንታ በአገሮች ላይ የሚፈጽመው ተግባር ምንድን ነው? (ቁ. 27–33)። (ሰ) የዚህን ምዕራፍ ዐቢይ ትንቢት በራስህ አገላለጽ ጻፍ።

ባለፈው ሳምንት ያጠናነውና በዚህ ክፍል የሚገኘው ዐቢይ ዋይታ በሰሜናዊው የእስራኤል መንግሥትና በይሁዳ ላይ የተነገረው ነው።

ቀጣዮቹ ሁለት ዋይታዎች ይሁዳን የሚመለከቱ ናቸው። የእነዚህ ሁለት ዋይታዎች ሥረ-መሠረት ንጉሥ ሕዝቅያስ ከግብፅ ጋር ያደረገው ቃል ኪዳንና እግዚአብሔር በይሁዳ ሕዝብ ላይ ያወጀው ፍርድ ነው።

1. ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን የማድረግ ሞኝነት (ኢሳ. 30፡1-5)

በኢሳይያስ ዘመን፥ ሁለት ዐበይት መንግሥታት ነበሩ። እነዚህም በስተ ሰሜን አሦርና በስተ ደቡብ ግብፅ ነበሩ። በአካዝ አገዛዝ፥ ይሁዳ ከአሦር ጋር ቃል ኪዳን አደረገች። በዚህም ሶርያና እስራኤል ይሁዳን እንዳያጠቁ ለመከላከል ችለዋል። ይሁንና፥ ይህ ቃል ኪዳን አሦር በይሁዳ ጉዳዮች ላይ የበላይ እንዲሆን አድርጎታል። ሕዝቅያስ ወደ ዙፋን ሲመጣ፥ ሕዝቡ ከአሦር አገዛዝ ነፃ ለመውጣት ፈለጉ። ይህንን ለማድረግ ግን ወታደራዊ ብቃት አልነበራቸውም። ስለሆነም ወደ ግብፅ ተመልሰው ቃል ኪዳን አደረጉ። ከአሦር ጋር በሚደረገው ትግል ግብጽ ካገዘቻቸው አሥራውያንን ለማሸነፍ እንደሚችሉ አሰቡ (2ኛ ነገ. 18፡21 ተመልከት)። በ715 ዓ.ዓ. ሻባኮ የተባለው አዲሱ ፈርኦን የግብፅ ንጉሥ ሆነ። በዚህን ጊዜ እንደ ሶርያ፥ ፍልስጥኤምና ይሁዳ የመሳሰሉ ትናንሽ አገሮች የአሦርን አገዛዝ ለመጣል ይተባበሩአቸው ዘንድ ወደ ግብፃውያን መጡ።

ላይ ላዩን ሲታይ፥ ይህ መልካም ዕቅድ ሊመስል ይችላል። አንድ አገር በራሱ ብቃት ሌላውን ለማሸነፍ ካልቻለ፥ ከሌሎች አገሮች ጋር መተባበሩ የማሸነፍ ዕድሉን ስለሚያሰፋ ከአስተዋይ የዘለለ አይደለም። ነገር ግን ለሕዝቅያስ መልካም የመሰለው ነገር እግዚአብሔር የፈለገው አልነበረም። ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡ ከአሕዛብ አገሮች በተለይም ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን እንዳያደርጉ አዝዞአቸው ነበር (ዘዳ. 17፡16 ተመልከት)። እስራኤል በታሪኳ ሁሉ፥ ቃል ኪዳን ለማድረግ የወሰደቻቸው አብዛኛዎቹ ጥረቶች ለሕዝቡ መንፈሳዊ ሕይወት አደገኞች ነበሩ። አይሁዶች ቃል ኪዳን ያደረጉባቸውን አገሮች አማልክት ለማምለክ ጊዜ አልወሰደባቸውም። እግዚአብሔር ሕዝቡ እርሱን ብቻ ለጥበቃ እንዲታመን ይፈልጋል። ሕዝቡ ለችግሮቻቸው ከሰዎች መፍትሔዎችን ከመፈለግ፥ እግዚአብሔር እንዲቀጣቸው የሚያደርግ ኃጢአት በሕይወታቸው ውስጥ እንዳለ ይመለከቱ ዘንድ ራሳቸውን መመርመር ነበረባቸው። ከዚያም እግዚአብሔር ጸሎታቸውን እንዲመልስ በንስሐና ራሳቸውን ዝቅ በማድረግ ወደ እርሱ ሊመለሱ ይገባቸው ነበር።

እግዚአብሔር የይሁዳን ሕዝብ «ዓመፀኞች ልጆች» ሲል ጠርቷቸዋል። ብዙውን ጊዜ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደማያደርግ በሚመስል ሁኔታ ይናገራል። በዚህ ስፍራ ግን ዓመፀኞች ቢሆኑም እንኳ የእርሱ ልጆች መሆናቸውን ይገልጻል። አይሁዶች እግዚአብሔር ከሌሎች

ወገኖች ጋር ቃል ኪዳን እንዳያደርጉ እንደከለከላቸው ያውቃሉ። እንደ ኢሳይያስ ያሉ የእግዚአብሔር ነቢያትም እንዲህ ዓይነቶቹን ቃል ኪዳኖች እንዳያደርጉ ነግረዋቸው ነበር። እነርሱ ግን የሰውን ጥበብ ተከትለው ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ወጡ። ከማይታያቸው የእግዚአብሔር ሠራዊት ይልቅ ፊት ለፊት የሚታያቸውን የፈርዖን ሠራዊት መታመኑ ቀለላቸው። ከአምልኮተ ጣዖት፥ ከሰካራምነትና ድሆችን ከመጨቆን ኃጢአታቸው ላይ ሌላ ኃጢአት አከሉ – ይኸውም ትክክለኛ ያልሆነ ቃል ኪዳን መፈጸም ነው።

ሕዝቅያስ ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን አደረገ። ኢሳይያስ ይህንን ቃል ኪዳን ይሁዳ በግብፅ «ጥላ» እንደታመነች አድርጎ ገልጾአል። ይህ ከዛፍ ጥላ ሥር ተቀምጦ ከፀሐይ ሙቀት የመከለልን ሁኔታ የሚያመለክተው ግብራሪያ ይሁዳ የግብፅን ጥበቃ እንደፈለገች የሚያመለክት ነበር። እግዚአብሔር ግን ጥላቸውና ጥበቃቸው ሊሆን ወደደ። [ኢሳ. 49፡2፤ 51፡16፤ መዝ. (91)፡1፤ 121፡5 ተመልከት።] እግዚአብሔር ለቃል ኪዳኑ እውቅና ስላልሰጠው፥ ይሁዳ ባለመታዘዝ ትመላለስ ነበር።

ይሁዳ ግብፅ ከአሦር ኃፍረትና ጭቆና እንደምታድናት ተስፋ አደረገች። ስለሆነም ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ገንዘብና የልዑካን ቡድን ወደዚያው ላከች። ነገር ግን ከቃል ኪዳኑ ጠብ የሚል ትርፍ አልነበረም። የይሁዳ የልዑካን ቡድኖች በታሪክ ወደሚታወቁ ሁለቱ የግብፅ ከተሞች – ጣኔዎስና ሓኔስ – ሄዱ። ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ነፃ እስኪያወጣቸው ድረስ ሕዝበ እስራኤል በባርነት ሲሠቃዩ የኖሩት በጣኔዎስ ከተማ ነበር። ይህ ምናልባት ወደ ባርነት ለመመለሳቸው ፍንጭ የሚሰጥ ክስተት ሊሆን ይችላል። ግብጽ ጠንካራና ቃል ኪዳን ለመግባት ጥሩ አገር ብትመስልም፥ እውነታው ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነበር። አይሁዶች የሚፈጽሙት የቃል ኪዳን ፍሬ ሥቃይን መውለዱ የማይቀር ነበር።

ይሁዳ ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ማድረጓ አሦርን አስቆጣት። ስለሆነም ይሁዳን ጨምሮ በከነዓን ከሚገኙት የተለያዩ አገሮች ጋር ጦርነት ገጠመች። እጅግ ብዙ አይሁዶች በምርኮኝነት ተወሰዱ። የግብፅ ሠራዊት ከአገሩ ተነሥቶ ወደ ከነዓን አገሮች ለእርዳታ ቢገሠግሥም፥ እንደሚሸነፍ ስለተገነዘበ ዓቅሙን አውቆ ሳይዋጋ ተመለሰ። ይሁዳ ተስፋ ያደረገችው የግብፅ ሠራዊት በሌለበት ውጊያ ለመግጠም ተገደደች። ያ ሁሉ ፖለቲካዊ ድርድርና ገንዘብ ባክኖ ቀረ። እንዲያውም ይህ ቃል ኪዳን ይሁዳን አርፋ በአሦር አገዛዝ ሥር ብትኖር ከሚደርስባት የላቀ ችግር አስከትሎባታል። በመጨረሻው እግዚአብሔር ለኢየሩሳሌም የሚያስፈልጋትን «ጥላ» አቀረበ። ያለ

ስብዓዊ ሠራዊት እገዛ፥ እግዚአብሔር የአሦርን ሠራዊት ደምስሶ ይሁዳን ነፃ አወጣ።

16ኛ ጥያቄ፦ ከዚህ ክፍል አላስፈላጊ ስለሆኑ ቃል ኪዳኖችና ስምምነቶች ምን እንማራለን? የተለያዩ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር መንፈስ ያልሆነ ቃል ኪዳን ሲያደርጉ ምን እንደሚከሰት ካየሃቸው ምሳሌዎች አንዳንዶቹን ጠቃቅስ።

## 2. በደቡብ (ኔጌቭ) ስላሉ እንስሶች የተነገረ ሸክም (ኢሳ.30፡6–7)

ወደ ግብፅ ገንዘብ መላኩ ከንቱ እንደሆነ ለማመልከት፥ ኢሳይያስ የግብፅን እርዳታ ለመሻመት ከእስራኤል አገር ሀብት ጭነው ስለሚሄዱት እንስሶች ቅኔ ተቀኘ። ኔጌቭ ከኢየሩሳሌም በስተ ደቡብ የምትገኝ በረሃማ ስፍራ ነበረች። (አማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «ኔጌቭ»ን «ደቡብ» ብሎ ተርጉሞታል።) ይህ አካባቢ በዱር እንስሳትና በእባቦች የተሞላ በመሆኑ፥ በዚያው በኩል አቋርጦ መሄዱ ለልዑካን ቡድኑ አደገኛ ነበር። ሕዝቅያስ ወርቅ የተጫነባቸውን አህዮች ብዙውን ጊዜ ሰዎች በማይጠቀሙበት መንገድ የላከው ምናልባትም አሦራውያንም ሆኑ አይሁዳውያን ቃል ኪዳኑን እንዳያውቁ ስለፈለገ ሊሆን ይችላል። የልዑካን ቡድኑ የተፈለገውን ገንዘብ ለመክፈል ይህንኑ አደገኛ መንገድ ማለፍ ነበረበት። ይሁዳ የግብፅን እርዳታ ለመግዛት ይህን ሁሉ ጥረት ለማድረግ ተገደደች።

በኢሳይያስ ቃላት ውስጥ ከይሁዳ ላይ የተሰነዘረ ጠንካራ ተግሣጽ ነበር። ከብዙ ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡን በዚህ አገር በኩል ወደ ተስፋዪቱ ምድር አምጥቶአቸው ነበር (ዘዳ. 8፡15)። አይሁዶች ዳግም በዚህ መንገድ እንዳይመለሱ ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶአቸው ነበር። በአንድ ወቅት እግዚአብሔር ነፃ ወዳወጣቸው አገር መመለስ ማለት ነፃ ባወጣቸው የእግዚአብሔር ጸጋ ላይ ማመፅ ነበር።

ስለሆነም ይህ የሕዝቅያስና የመልእክተኞቹ ጥረት ሁሉ መና ይቀራል። በመጨረሻው ግብፅ አትጠቅማቸውም። አይሁዶችን ከአሦር ለማዳን አትችልም። ስለሆነም ኢሳይያስ ለግብፅ አዲስ ስም አወጣ። «በቤት የሚቀመጥ ረዓብ» ሲል ሰየመ። «ረዓብ» ማለት «ማዕበል» ወይም «ዕቡይ» ማለት ሲሆን፥ የግብፅን ትዕቢት ያንጸባርቃል። በብሉይ ኪዳን፥ ረዓብ የሚለው ቃል ሌዋታን የተባለውን የአፈ ታሪክ አውሬ የሚያመለክት ነው። ረዓብ በባህር ውስጥ ትኖራለች ተብላ የምትገመት ሴት የሁከት አውሬ ነች። በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ ሁከት ሲረግብ በተምሳሌታዊ አገላለጽ ረዓብ እንደተገራች ይነገራል። (ለምሳሌ፥ የፍጥረት ፈር መያዝ እንደ ረዓብ መመታት ተገልጾአል። ኢዮብ 26፡12።) ይኸው ተምሳሌት የእግዚአብሔር ሕዝብ ነጻ ይወጡ ዘንድ ግብፅ ስለተሸነፈችበት ሁኔታም ለመግለጽ አገልግሎአል (መዝ. 89፡10፤ ኢሳ. 51፡9)። ረዓብ የግብፅ ሌላ ስም በመሆንም አገልግሎአል

[መዝ. (87)፡4፤ ኢሳ. 30፡7]። ይሁንና፥ ይህ የኃይለኛ አውሬ ተምሳሌት የሆነው የግብፅ ጉልበት ይዝላል። ከሚፈርድባት አምላክ ጋር ስትነጻጸር ግብፅ የማትጠቅም ከንቱ ነች።

3. ሕዝቡ የእግዚአብሔርን ነቢያት ቃል ቸል እንዳለ (ኢሳ. 30፡8–11)

የእግዚአብሔር የትእዛዝ ቃል ወደ ኢሳይያስ መጥቶ ሕዝቡ ባሉበት ስፍራ ትንቢቱን በሸክላ ጽላት (ሰሌዳ) እንዲጽፍ ነገረው። ይሽውም ምን እያደረገ እንደሆነ ይመለከቱ ዘንድ ነበር። ከብራና (የእንስሳት ቆዳ) በተቃራኒ፥ በርጥብ የሸክላ ጽላት ላይ በሚጻፍበት ጊዜ ጽሑፉ ዘላለማዊ ይሆናል። በብራና ላይ እንደተጻፈ ጽሑፍ ሊበሰብስ ወይም ሊደበዝዝ አይችልም። ስለሆነም እግዚአብሔር የኢሳይያስ መልእክት በፍጹም እንዳይጠፋ ለማድረግ ፈለገ። ኢሳይያስ ምን እንደሚጽፍ አናውቅም። አንዳንድ ምሑራን በሌሎች ላይ የመደገፍን ከንቱነት ለማሳየት ሲል «ረዓብ» የሚል ቃል እንደጻፈ ይናገራሉ። ወይም ደግሞ ስለ ይሁዳና በግብፅ ላይ መደገፍ እርባና ቢስ መሆኑን የገለጸበትን ትንቢት ማጠቃለያ ጽፎ ይሆናል። የተጻፈው አሳብ ምንም ይሁን ምን ዓላማው ግን ጽሑፉ ለሚመጡት ብዙ መቶ ዓመታት ቆይቶ አይሁዶች ከእግዚአብሔር ይልቅ በሌሎች አገሮች ላይ በመደገፍ የወሰዱትን የተሳሳተ ውሳኔ ማንጸባረቅ ነበር።

እግዚአብሔር ቃሉን በሰሌዳ ላይ መጻፍ ያስፈለገበትን ምክንያት በመግለጽ የሕዝቡን የልብ ድንዳኔ አመልክቷል። ሆን ብለው የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማድረግ ስላልፈለጉ «ዓመፀኞች» ነበሩ። እግዚአብሔርን የሚከተሉ ቢያስመስሉም ይህንኑ ስላላደረጉ «አታላዮች» ነበሩ። «የእግዚአብሔርን ሕግ ለመስማት የማይወዱ» ሰዎች ነበሩ። እግዚአብሔር ባለማቋረጥ ይናገራቸው ስለነበር፥ የሳቱት ፈቃዱን ባለማወቅ አልነበረም። ይልቁንም የራሳቸውን የልብ መሻት በመከተል እግዚአብሔርን ለመስማት አልፈቀዱም።

ኢሳይያስ ሕዝቡ ለነቢያቱ የነበራቸውን አመለካከት እግዚአብሔርን ለመስማት እንዳለመፈለግ አድርጎ ገልጾታል። አይሁዶች ነቢያቱ እግዚአብሔር የተናገረውን መልእክት እንዲያስተላልፉ እንደመጠየቅ፥ የእግዚአብሔርን ቃል እንዳይነግሩዋቸው ይማጸኑ ጀመር። አይሁዶች ነቢያቱ የሚናገሩዋቸውን የፍርድ መልእክቶች ለመስማት አልፈለጉም። «እግዚአብሔር እንደተቆጣንና እንደሚፈርድብን እየደጋገማችሁ የምትነግሩን መልእክት ሰልችቶናል። የእግዚአብሔርን ቅዱስነትና በእኛ ላይ የሚያመጣውን ፍርድ አስመልክቶ መናገራችሁን አቁሙ። ከእንግዲህ የእናንተን ድምፅ ለመስማት አንፈልግም!» የሚል አስተሳሰብ ነበራቸው። አይሁዶች ነቢያቱ ሕዝቡ ለመስማት የሚፈልገውን ጣፋጭ መልእክት ብቻ እንዲነገሩ ፈለጉ። ይህ የሐሰት

ነቢያት የሚያደርጉት ነገር ነበር። ወይም ደግሞ ነቢያቱ ጭራሽ አለመናገር ነበረባቸው። ነገር ግን እውነተኛ ነቢያት የእግዚአብሔርን ቃል መናገር አቁመው ሰዎች የሚፈልጉዋቸውን ነገሮች ብቻ በሚናገሩበት ወቅት፥ የሐሰት ነቢያት ይሆኑና የውሸት ተስፋን ይመግባሉ። አንድ የማብራሪያ መጽሐፍ እንዳለው፥ «እውነት ሳይታወጅ ሲቀር፥ የእውነት አምላክ ከሰዎች ልብ ይጠፋል።»

17ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ዛሬ ብዙ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን ጠቅሰው እግዚአብሔር ለኃጢአታቸው እንደሚፈርድባቸው በሚናገሩ አገልጋዮች ላይ የሚቆጡት እንዴት ነው? ለ) ለሰባኪዎች የእግዚአብሔር ቃል የሚያስተምረውን ሳይሆን ሰዎች ለመስማት የሚፈልጉትን መናገር የሚቀልባቸውን መንገዶች ግለጽ። ሐ) 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡21–31 አንብብና ይህ ክፍል ዛሬ እንዴት እንደተፈጸመ ግለጽ።

### 4. ለአይሁዶች የልብ ድንዳኔ የእግዚአብሔር ምላሽ (ኢሳ. 30፡12–18)

እግዚአብሔር አንድን ሰው ወይም ቤተ ክርስቲያን ለተግባራዊ እርምጃ አያስገድድም። ለእነርሱ የሚሻለውንና ፈቃዱ የሆነውን ይነግራቸዋል። እርሱ የሚላቸውን በመታዘዝ ስለሚያገኙት በረከት ይነግራቸዋል። ባለመታዘዛቸው ደግሞ ስለሚያፍሱት ፍርድ ያስጠነቅቃቸዋል። የሰው ልጅ የመታዘዝ ወይም ያለመታዘዝ ምርጫ አለው። ነገር ግን የትኛውን በረከት ወይም መርገም እንደሚቀበል ሊመርጥ አይችልም። የእግዚአብሔርን ቃል መስማት አለመስማታቸው ከቃሉ ላይ አንዳች ለውጥ አያመጣም። ቃሉ ለዘላለም ይኖራል። አንታዘዝም የሚሉ ሰዎች ግን ራሳቸውን ይጎዳሉ።

አይሁዶች እግዚአብሔር በኢሳይያስና በሌሎችም ነቢያት አማካኝነት የሰጣቸውን መልእክት ለመቀበል አልፈለጉም። በሙሴ አማካኝነት ከእግዚአብሔር ጋር ቃል ኪዳን ባደረጉ ጊዜ እንከተላለን ያሉትን መንገድ መልሰው ተቃወሙ። ስለሆነም እግዚአብሔር ያለመታዘዛቸው የሚያስከትላቸውን አስከፊ ውጤቶች ይነግራቸዋል።

ሀ. ይጠብቁናል ብለው የተማመኑባቸው ነገሮች ከመርዳት ይልቅ ይፈርሳሉ። አይሁዶች ሁለት ነገሮችን የመጠበቂያ ግንብ አድርገው እንደተደገፉ ተገልጾአል። እነዚህም «ጭቆና» እና «ማታለል» ናቸው። መሪዎች ከሕዝባቸው ከሚነሡት ችግሮች ለመጠለል ጭቆናን ይጠቀሙ ጀመር። ድሀውን ከቁጥጥር ሥር ለማዋል ኃይልን ተጠቀሙ። ሀብታሙንና ኃይለኛውን ለመጥቀም ጭቆናን ተጠቀሙ። «ሕዝባችንን በጉልበት ከተቆጣጠርን፥ የመንግሥት ባለሥልጣናትንና ነጋዴውን ኅብረተሰብ ካስደሰትን፥ የሚደርስብን ችግር አይኖርም» ሲሉ አሰቡ። በተጨማሪም ማታለልን በመሣሪያነት ተጠቀሙ። ይህ ምናልባትም ከሌሎች አገሮች ጋር

ለማድረግ ሲጣጣሩ የነበሩዋቸውን የውጭ ግንኙነቶች የሚያመለክት ይሆናል። ለአሦር መገበራቸውን የሚያቆሙ መሆናቸውን ሳይናገሩ በስውር ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን አደረጉ። የፖለቲካ ብልጠታቸውን በመጠቀም ራሳቸውን ከጦርነት እንደሚጠብቁ አድርገው አሰቡ።

እግዚአብሔር ግን የጥበቃ ቅጥሮቻቸው መፈራረስ እንደ ጀመሩ ነገራቸው። ሁኔታው በሚሰምጥ መሬት ላይ እንደ ተመሠረተ ቤት ነበር። መጀመሪያ አነስተኛ የመሰንጠቅ ሁኔታ ብቻ ይታያል። ስንጥቁ እየሰፋ ሲሄድ ባለቤቶቹ አይታወቃቸውም። አንድ ቀን ግን ሳይታሰብ ቤቱ ይፈርሳል። አይሁዶች እግዚአብሔር ከአሦር እንደሚጠብቃቸው እየተገነዘቡ ባለመታዘዛቸው በብሔራዊ ደኅንነት ውስጥ አነስተኛ የመሰንጠቅ ምልክት ታየ። በግብፅ ደካማ መሠረት ላይ ሲደገፉ ስፋቱ ጨመረ። አንድ ቀን የግብፅን (እና የእግዚአብሔርን) ድጋፍ በትክክል ሲሹ አያገኙትም። ቃል ኪዳን ይገቡላቸው ዘንድ እንዳታለሉዋቸው ያሰቡዋቸው አገሮች አይረዱቸውም። ተስፋቸውና ዕቅዳቸው ሁሉ ይወድቃል።

ከሴት ጀርባ እንደሚወድቅ ውኃ የተሞላ እንስራ፥ እግዚአብሔር ዕቅዳቸውን ይገለብጠዋል። ዕቅዳቸው ሙሉ ለሙሉ ስለሚደመሰስ ውኃ ለመቅዳት ወይም እሳት ለመጫር እንደማይችል የሸክላ ገል ይሆናል። ዕቅዶቻቸው እንደ ሸክላ መሰባበር ብቻ ሳይሆን፥ አንድ ቀን አይሁዶች ወደ ምርኮ ይወሰዳሉ። አሦር ኢየሩሳሌምን ባጠቃች ጊዜ ይህ ትንቢት የተፈጸመው በከፊል ብቻ ነበር ። በ586 ዓ.ዓ. ባቢሎን ኢየሩሳሌምን ስታወድምና በኋላ በ70 ዓ.ም. ሮማውያን ተመሰሳይ ድርጊት ሲፈጽሙ ትንቢቱ በከፍተኛ ደረጃ ተፈጸመ።

18ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዛሬ ሰዎች ራሳቸውን ለመጠበቅ እንደሚችሉ በማሰብ የሚገነቡዋቸው ቅጥሮች ምንድን ናቸው? ለ) እነዚህ ቅጥሮች ወድቀው በመፈራረስ ከንቱነታቸውን ሲያመለክቱ ያየኸው እንዴት ነው?

ለ. ብቸኛው የደኅንነት ምንጭ በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ በሙሉ መደገፍ ነው። እግዚአብሔር ሌላ ቅጥር፥ ሌላ የደኅንነትና የዋስትና ምንጭ ጠቆማቸው። ይህም በእግዚአብሔር ላይ ሙሉ ለሙሉ መደገፍ ነበር። <u>በመጀመሪያ</u>፥ ንስሐ መግባት ማለትም ከኃጢአት ሕይወት (ከጭቆናና ከማታለል) ተመልሰው እግዚአብሔር ወዳዘጋጀላቸው መንገድ ሊሄዱ ይገባቸዋል። (በመጽሐፍ ቅዱስ አገላለጽ፥ ንስሐ መግባት ማለት ለፈጸሙት በደል ይቅርታ መጠየቅ ብቻ አይደለም። ይልቁንም የአኗኗር ዘይቤን መለወጥ ያሻል።) <u>ሁለተኛ</u>፥ ዕረፍት ማለትም እግዚአብሔር በራሱ ጊዜ ነፃ እንደሚያወጣ ሙሉ ለሙሉ መደገፍ ያስፈልጋል። በእግዚአብሔር ላይ ተደገፍን እያሉ ሰብዓዊ መፍትኼዎችን መፈለጉ ትክክል አይሆንም። ሙሉ ለሙሉ በእግዚአብሔር ላይ

መደገፍ ያስፈልጋል። ወዲያ ወዲህ እየተሯሯጡ መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ «በጸጥታ» ተማምነው ሊቀመጡ ይገባል። በወጥመድ እንደተያዘ ወፍ ሳይፍጨረጨሩ እግዚአብሔር እንደሚረዳቸው በመተማመን ሊጠባበቁ ያሻል። እውነተኛ ብርታት የሚመጣው ከዚህ ነው። ከጠላቶቻቸው ነፃ የሚወጡት በዚህ ጊዜ ነበር። የሚያሳዝነው አይሁዶች የእግዚአብሔርን ነፃ የማውጣት መንገድ አልተከተሉም።

ሐ. በእግዚአብሔር ላይ ያለመታመን ውጤት። ሕዝቡ በማይታየው እግዚአብሔር ከመታመን በሚታዩ ነገሮች ለመታመን መረጡ። ስለሆነም፥ እግዚአብሔር ምን እንደሚከሰት ነገራቸው። መጀመሪያ፥ ችግሮችን ሁሉ ሊያመልጡ እንደሚችሉ በትምክሕት ተናገሩ። ይህም በፈጣን ፈረሶቻቸው እንደሚሸሹ ተደርጎ በተገለጸው ተምሳሌት ተመልክቷል። «በፈረሶቻችን ፈጥነን ወደ ግብፅ በመድረስ የነርሱን እርዳታ ልናገኝ እንችላለን» ሲሉ ምክንያት አቀረቡ። ነገር ግን በእግራቸው ሲሮጡ በፈጣን ፈረሶች ላይ የተቀመጡ ባላንጣዎቻቸው ይደርሱባቸዋል [መዝ. (33)፡17]። ሁለተኛ፥ ጠላቶቻቸውንና ችግሮቻቸውን በፈጣን ፈረሶቻቸው እንደሚቀድሙ ቢናገሩም፥ ጠላቶቻቸው ከእነርሱ የተሻሉ ፈረሶችን ተጠቅመው ያሸንፋዋቸዋል። ሦስተኛ፥ የውጊያ ወኔያቸውና ችሎታቸው ይከዳቸዋል። አንድ የጠላት ወታደር አንድ ሺህ የይሁዳ ወታደሮችን ያሳድዳል። አምስት የጠላት ወታደሮች ጠቅላላውን ሕዝብ ያባርራሉ። (ይህ አለመታዘዝን ተከትሎ የሚመጣው መርገም እንዴት እንደተፈጸመ የሚያመለክት መሆኑን ከዘዳግም 32፡30 ተመልከት።) በራሳቸው ወይም በግብፅ ወታደሮች ለመታገዝ የሚያደርጉት ጥረት ከንቱ ይሆናል። አራተኛ፥ ጥቂት ቅሬታዎች ብቻ ይቀራሉ። ኢሳይያስ ይህን ጦርነት የሚጀመርበትን ስፍራ ለማመልከት ከተራራ ላይ ተተክሎ ከሚውለበለብ ባንዲራ ጋር አመሳስሎታል።

መ. እግዚአብሔር ከፍርዱ ባሻገር ለይሁዳ ርኅራኄ ሊያሳይ ፈልጓል። ኢሳይያስ በሚዛናዊነት ስለሚጠበቁት ሁለት የእግዚአብሔር ባሕርያት ይናገራል። እነዚህም ኃጢአተኞችን እንዲቀጣ የሚያደርገው የእግዚአብሔር ጻድቅነትና ኃጢአተኞችን ይቅር እንዲል የሚያደርገው ርኅራኄው ናቸው። እግዚአብሔር ለማጥፋት አይፈልግም። እግዚአብሔር በአንድ ኃጢአተኛ ሞትና ያንንም ተከትሎ በሚመጣው ፍርድ አይደሰትም (ሕዝ. 18፡21–23 ተመልከት)። ስለሆነም እግዚአብሔር ሁልጊዜም ይቅር ለማለትና በሕዝቡ ላይ በረከቱን ለማምጣት ዝግጁ ነው። እርሱ የርኅራኄ

አምላክ ስለሆነ፥ ሁልጊዜም ይቅር ለማለትና አዲስ ጅማሬ ለመስጠት ጊዜ አይወስድበትም።

ነገር ግን እግዚአብሔር የፍትሕ አምላክም ነው። ስለሆነም ሁልጊዜም ትክክለኛውን ነገር ያደርጋል። ትክክል የሚሆነውም ከጽድቅና ከፍቅር ባሕርዩ ጋር ስለሚጣጣም ነው። እግዚአብሔር ለማፍቀርና ርኅራኄን ለማሳየት መፈለጉ በኃጢአት ላይ የመፍረድ ኃላፊነቱን አያዛንፍበትም። እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር ላላቸው መልካም ግንኙነት በመሸለም ወይም ለኃጢአታቸው በመፍረድ አድልዎ የሌለበትን ብያኔ ይሰጣል። የእግዚአብሔር ምሕረት እንደኛው ምልክት ሰዎች ወደ ንስሐ እስኪመለሱ ድረስ እየቀጣ ማስተማሩ ነበር። እግዚአብሔር የቅጣት እጁን ከይሁዳ ላይ ሲያሳርፍ ንስሐ የሚገቡበትንና የፈውስ ምሕረት የሚያገኙበትን ጊዜ ይናፍቃል። የእግዚአብሔር ምሕረት ከፍርዱ ቀድሞ ይገለጣል።

ብዙሃኑ ከእግዚአብሔር በመመለስ ፍርድን በሚቀበልበት ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ለመመለስ የመረጡት ሰዎች ጉዳይስ? እምነታቸውንና ተስፋቸውን መጣል አለባቸውን? የሚጨቁኑትንና የሚያታልሉትን ኃይላት መቀላቀል አለባቸው? እግዚአብሔር እንዳዳላ በማሰብ ማጉተምተም አለባቸው? አይደለም። ኢሳይያስ በልበ-ሙሉነት ተማምነው እግዚአብሔርን እንዲጠባበቁ ነግሮአቸዋል። የእግዚአብሔር የበረከት እጅ ሊባርካቸው የሚመጣበት ጊዜ ይደርሳል። በትዕግሥት በመጽናታቸውና ለእግዚአብሔር በታማኝነት በመታዘዛቸው ሽልማትን ያገኛሉ።

19ኛ ጥያቄ፡- በፊታችን ስለሚቆሙት ሁለት መንገዶች (ቅጥሮች) ከዚህ ክፍል ምን እንማራለን?

## 5. እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያመጣው በረከት

(ኢሳ. 30:19-26)

አንድ ቀን የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት አይሁዶች ኃዘን ወደ ደስታ ይለወጣል። አንድ ቀን የይሁዳ ሕዝብ ልብ ይለወጥና ወደ እግዚአብሔር ተመልሰው ይረዳቸው ዘንድ ይጮኻሉ። ሕዝቡ የሚያስማውን የንስሐና የእርዳታ ጩኸት እንደሰማ፥ እግዚአብሔር ምላሽ በመስጠት ነፃ ያወጣቸዋል። ምን ዓይነት አስደናቂ አምላክ ነው! እርዳታውን እስክንጠይቅ ድረስ ይጠብቅና ምንም ያህል ዓመፀኞች ብንሆን እንኳ ጉድለቶቻችንን ለመሙላት በምሕረት ይቀርበናል።

የልብን ለውጥ የሚያመጣው ምንድን ነው? ኢሳይያስ ኃጢአተኞች ንስሐ እንዲገቡና ወደ መንፈሳዊ ዕድገት እንዲያመሩ የሚያደርጉትን ሁለት የእግዚአብሔር መሣሪያዎች ጠቅሶአል። እነዚህም ጭንቀትና መከራ ናቸው። ኢሳይያስ የእስር ቤትን ምግብና ውኃ ምሳሌ

ይጠቀማል። ለምርኮ (እስራት) የሚዳረጉበት ዘመን ይመጣል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በዚህ ጊዜ ተጠቅሞ ልባቸውን ይለውጠዋል። ልባቸው ተለውጦ እግዚአብሔርን መከተል ሲጀምሩ፥ ከመቅጽበት ሁኔታቸው ይለወጣል። የዳዊት ከተማ በሆነችው በጽዮን ያድራሉ። ይህች እግዚአብሔር የሚኖርባት የኢየሩሳሌም ከተማ ነች። ይህች የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ድንኳንና የሕዝቡ ዘላለማዊ መኖሪያ የሆነችው የዘላለማዊቷ ኢየሩሳሌም ተምሳሌት እንደሆነ አይጠረጠርም።

አሥራውያን ኢየሩሳሌምን በከበቡና ሕዝቡ ንስሐ ገብቶ እግዚአብሔርን በተከተለበት ወቅት ይህ ትንቢት በከፊል ተፈጽሞአል። እግዚአብሔር ይቅር ብሎአቸው ኢየሩሳሌምን ነፃ አውጥቶአታል። ለአጭር ጊዜ በሰላም ለመኖር ችለው ነበር። በኋላ ባቢሎን አይሁዶችን በምርኮኛነት ስትወስድና ኃጢአታቸውን ሲናዘዙ፥ እግዚአብሔር ወደ ይሁዳና ኢየሩሳሌም እንዲመለሱ ፈቅዶላቸዋል። አይሁዶች ቤተ መቅደሱን ዳግም ሊያንጹና እግዚአብሔርም በሕዝቡ መካከል ሊኖር ችሏል። ዛሬም እግዚአብሔር ሲቀጣንና እኛም ንስሐ ገብተን ለይቅርታ ወደ እርሱ ስንመለስ፥ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የነበረውን ኅብረት ያድሳል። ይህ ትንቢት በተሟላ መልኩ የሚፈጸመው እኛ ወደ ሰማይ ስንሄድ ወይም ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ይሆናል። ለክርስቶስ ዘላለማዊ መንግሥት፥ ለዘላለማዊቷ ጽዮን በምንዘጋጅበት ጊዜ፥ እግዚአብሔር በሕይወታችን ዘመን የሚሰጠን ቅጣት ያጠራናል።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ሕዝብ በሚለወጥበትና የእግዚአብሔር መንግሥት በሚጀመርበት ጊዜ የሚከሰቱትን አያሌ በረከቶች ዘርዝሮአል።

ሀ. አይሁድ የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ የሚናገሩ አስተማሪዎች ይኖሩአቸዋል። ይህ የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው በትክክልና በግልጽ ለሕዝቡ የሚናገሩትን መንፈሳዊ ነቢያት የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። የስካር መንፈስ ከካህናትና ከነቢያት ይወገዳል (ከኢሳይያስ 28፡7–8 ተመልከት)። ወይም እግዚአብሔር አስተማሪያቸው እንደሚሆንና የኋላ ኋላ መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው እንደሚከፈቱ የሚያመለክት ይሆናል። አይሁዶች የሚታዘዝ ልብ ይኖራቸውና እግዚአብሔርም ይባርካቸዋል።

የእግዚአብሔርን ቃል በሚገባ የተማሩ ሰዎች ሳይኖሩ ጠንካራ የእግዚአብሔር ሕዝብ ማግኘት አይቻልም። ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያልተመሠረቱትን ነገሮች ለመስማትና ለመዘመር በሚመርጡበት ዘመን ይህ ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ነው። ጥልቅ የእግዚአብሔር ትምህርት ከሌለ፥ በእግዚአብሔር ላይ ማመፅ እንደሚከተል እሙን ነው። በሌላ አነጋገር፥ ጠንካራ የእግዚአብሔር

ሕዝብ መሆናችን የሚታወቀው እንደ ሰንበት አምልኮው ሁሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ቡድኖችና የሰንበት ትምህርት ቤቶችም በሰዎች ሞልተው ሲገኙ ነው።

ለ. እግዚአብሔር በግልጽ በራሱ መንገድ ይመራቸዋል። እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በሚያስከብር መንገድ ለመሄድ ይችሉ ዘንድ የሙሴ ሕግ ነበራቸው። መንገዱን የሚያመለክቱ ካህናትና ነቢያትም ነበሯቸው። አንድ ቀን ግን እግዚአብሔር ራሱ ከእነርሱ ጋር በመሄድ መንገዱን ያሳያቸዋል። ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ድምፅ፥ «እንድትሄድበት የምፈልገው መንገድ ይኼ ነው። በዚህ ሂድ» እያለ በእንያንዳንዱ ሰው ጆሮ እንደሚያንሾካሹክ ተናግሮአል። ይህ እግዚአብሔር ለእያንዳንዳችን በውስጣችን የሚኖር መንፈስ ቅዱስን በመስጠቱ በአዲስ ኪዳን ዘመን ተፈጻሚነትን አግኝቶአል። መንፈስ ቅዱስ በቀዳሚነት የእግዚአብሔርን ቃል በመጠቀም ሕሊናችንን ያበራዋል። ከዚያም እግዚአብሔር እንድንከተል የሚፈልገውን የአኗኗር ስልት በግልጽ ያስተምረናል። የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማወቅ የተሰወረ ምሥጢር አይደለም። መንፈስ ቅዱስ በቀዳሚነት በእግዚአብሔር ቃል አማካኝነት እንዲናገረን መፍቀድና የሚናገረውን መታዘዝ ነው።

ሐ. የእግዚአብሔር ሕዝብ ከጣዖቶቻቸውና ልባቸውን ካሸፈቱባቸው ነገሮች ሁሉ ይገላገላሉ። ከአብርሃም ዘመን እስከ ምርኮ ዘመን ድረስ፥ የእስራኤላውያን ታማኝነት የተከፋፈለ ነበር። በአመዛኙ እግዚአብሔርን ቢያመልኩም፥ የአሕዛብን ጣዖታት ለማምለክም ተፈትነዋል። ነገር ግን የመከራና የስደት እሳት የጣዖታትን ፍቅር ከልባቸው ያወጣዋል። ከባቢሎኑ ምርኮ ወዲያው አይሁዶች በፍጹም ጣዖታትን ለማምለክ አልተፈተኑም። በአንድ ወቅት ያመለኩዋቸው ጣዖታት ወድመዋል። ኢሳይያስ ይህንን ከአምልኮተ ጣዖት መገላገል ሴት በኃፍረት ከምትወረውረው የወር አበባ ማበሻ ጨርቅ ጋር ያነጻጽረዋል።

ጣዖት ልባችን ከእግዚአብሔር በላይ ወይም የእግዚአብሔርን ያህል የሚወደው ማንኛውም ነገር ነው። ይህ እንደ ቤተሰብ፥ ገንዘብ፥ ትምህርት የመሳሰሉትን መልካም ነገሮች ሊያካትት ይችላል። ብዙውን ጊዜ በእነዚህ ሌሎች ነገሮችና በእግዚአብሔር መካከል ታማኝነታችንን ለመከፋፈል እንፈተናለን። ነገር ግን ከእውነተኛ ልብ እግዚአብሔርን ካከበርን፥ ከሙሉ ልባችን ልንወደውና ልናገለግለው ይገባል። እግዚአብሔርን ከልባችን ልንወድና ልናገለግል፥ እግዚአብሔርም ሊባርከን የሚችለው ሌሎቹን ጣዖታት የወረወርናቸው እንደሆነ ብቻ ነው።

20ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በክርስቲያኖች ልብ ጣዖት ሊሆኑ የሚችሉትን ሌሎች ነገሮች ዘርዝር። ለ) ከእነዚህ ሌሎች ፍቅሮች መለየት አዳጋች የሚሆነው ለምንድን ነው? ሐ) ከእነዚህ ሌሎች ጣዖታት መለየት የሚያስፈልገው ለምንድን ነው?

## መ. እግዚአብሔር አይሁዶችን በረገመ ጊዜ ያስወገዳቸውን በረከቶች ይመልሳል።

21ኛ ጥያቄ፡– ዘዳ. 28፡1–14 አንብብ። በኢሳይያስ ምዕራፍ 30 የተጠቀሱትን በረከቶች እግዚአብሔር በዘዳግም ከቀጣቸው በኋላ እንደሚባርካቸው ከተናገረው አሳብ ጋር አነጻጽር።

በኢያሱ ዘመን፥ ሕዝበ እስራኤል ከሁለት ተራሮች ላይ ወጥተው እግዚአብሔርን ሲታዘዙ ስለሚመጡላቸው በረከቶችና አንታዘዝ ሲሉ ስለሚመጡባቸው መርገሞች የተነገረውን ቃል ሰምተዋል። ከዚያም ከእግዚአብሔር ጋር ቃላቸውን አደሱ (ኢያ. 8፡30–35)። አይሁዶች ቃል ኪዳኑን በመተላለፋቸው እግዚአብሔር እንደተናገረው መርገሙን አመጣባቸው። እነዚያ መርገሞች ግን ጊዜያዊ ብቻ ነበሩ። አንድ ቀን እግዚአብሔር በረከቶቹን እንደሚመልስላቸው ቃል ገብቶላቸዋል። በዚህ ጊዜ ዝናብና በቂ እህል ይኖራል። ከብቶቹ በዝተውና ተባርከው ይኖራሉ። ጠላት ከተሞቻቸውን ለማጥቃት ያነጹዋቸው ግንቦች ይፈርሳሉ፤ ጠላትም ይረታል። ከበረከቱ መብዛት የተነሣ የፀሐይና የጨረቃ ብርሃን ይጨምራል። የጨለማው ዘመን ማለትም በጠላት መረታት፥ በሽታና ረሃብ ያከትማል። የጨረቃና የፀሐይ ብርሃን ለአይሁዶች የእግዚአብሔር በረከት ተምሳሌት ነበር። አሁን ያ ብርሃን ሰባት እጥፍ ይሆናል። ሰባት ቁጥር ፍጹምነትንና ምሉዕነትን ያመለክታል። ስለሆነም ኢሳይያስ የመርገም ጽልመትና የጠላቶቻቸው ጭቆና ሙሉ ለሙሉ እንደሚወገዱና የእግዚአብሔር በረከት ምድራቸውን እንደሚሞላ እየተናገረ ነበር።

እግዚአብሔር ሐኪማቸው ይሆናል። የሕዝቡን ግለሰባዊና ብሔራዊ ቁስሎች እየፈወሰ ከስፍራ ወደ ስፍራ ይዞራል። ሕመማቸውና ሥቃያቸው ሁሉ ይወገዳል። ከእንግዲህ የቀደመውን ኀዘን አያስታውሱም። የሚቀረው ደስታ ብቻ ይሆናል።

ይህ ትንቢት መች ይፈጸማል? አይሁዶች ከባቢሎን ምርኮ በኋላ በዘሩባቤል፥ ዕዝራና ነህምያ መሪነት በተመለሱበት ወቅት ተፈጽሞ ይሆን? ይህ ከፊል ፍጻሜው ብቻ ነበር። ወይስ በቤተ ክርስቲያን አማካኝነት በምድር ላይ ተፈጽሞ ይሆን? አሁንም ይህ ከፊል ፍጻሜ ብቻ ነው። ነገር ግን እግዚአብሔር በዚህ ዓይነት ሁኔታ ምድርን ለመባረክ ቃል አይገባም። ብዙ ክርስቲያኖች በሚገኙባቸው አገሮች ሳይቀር ሰዎች ከተፈጥሮ አደጋ ሙሉ ለሙሉ የራቁ አይደሉም። ወይስ በመንፈሳዊ መልኩ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ተፈጽሞ ይሆን? አዎን፥

እግዚአብሔር ሕዝቡን ይባርካል። ይህ የሚሆነው ግን ብዙውን ጊዜ እነዚህ ጥቅሶች በሚገልጹት መንገድ አይደለም። እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ ልጆቹ መንፈሳዊና ሰማያዊ በረከቶችን ለመስጠት ቃል ገብቶአል (ኤፌ. 1፡3–14)። ይህ ግን በብሉይ ኪዳን ለነበሩት አካላዊ ሕዝብ ቃል እንደገባው ዓይነት ሥጋዊ በረከት አይደለም። በመሆኑም ብዙ ክርስቲያኖች ይህ ክፍል ሙሉ ለሙሉ የሚፈጸመው ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለመንገሥ በሚመጣበት ወቅት እንደሆነ ወደ ማመኑ አዘንብለዋል።

## 6. እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ በሚያወጣበት ጊዜ የሚዘመረው የነጻነት መዝሙር (ኢሳ. 30፡27–33)።

ፍትሕ–አልበኝነት በምድር ላይ ሰፍኖ ሳለ በትዕግሥት መጠባበቁ ለሕዝበ እግዚአብሔር ምን ይረዳል? ይህ ከእግዚአብሔር ማንነት የተነሣ የሚሆን ነገር ነው። እግዚአብሔር ኃይለኛ ተዋጊ ነው። የሥራ ጊዜው ሲደርስ ለሕዝቡ የሚዋጋም እርሱ ነው። ሕዝቡ ከሥቃይ ወጥተው ይደሰቱ ዘንድ የዓለምን መልክ ይለውጣል። እግዚአብሔር እንዴት እንደሚመጣና ሕዝቡን እንደሚያድን ኢሳይያስ በቅኔያዊ ስንኞች ይናገራል።

ሀ. እግዚአብሔር ኃያል ተዋጊ ነው። በሥዕላዊ ቋንቋ፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔርን እንደ ኃያል ተዋጊ አድርጎ ገልጾታል። ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር በቀጥታ እንደሚናገር ስሙ የራሱ ማንነት ያለው ይመስል «የእግዚአብሔርም ስም» ብሎ መጥቀሱ አስገራሚ ነው። ይህ አይሁዶች የእግዚአብሔርን ስም ሲጠሩ ሙሉ ማንነቱንና ኑባሬውን እንደሚጠቅሱ ለመረዳት በምሳሌነት ያገለግላል። ተዋጊው እግዚአብሔር እንጂ ስሙ አልነበረም።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ታላቅነት፥ ኃይልና በሕዝቡ ጠላቶች ላይ የሚወርደውን የጽድቅ ፍርድ ለማመልከት በርካታ ተምሳሌታዊ ምሳሌዎችን ተጠቅሞአል። እግዚአብሔር ዓለምን ለመፍረድ በሚመጣበት ጊዜ በትክክል ኢሳይያስ እንደገለጸው ሆኖ እንደሚመጣ ማሰቡ አስፈላጊ አይሆንም። ኢሳይያስ በቅኔያዊ አገላለጽ ሊያሳየን የፈለገው በዚያን የፍርድ ዕለት እግዚአብሔር ምን ያህል ኃያልና ታላቅ ሆኖ እንደሚሠራና በፍርዱም ሂደት ውስጥ በቀጥታ እንደሚሳተፍ ነው።

1. እግዚአብሔር ለሕዝቡ ሊዋጋ ይመጣል። ምናልባትም ኢሳይያስ እግዚአብሔር ከሲና ተራራ እንደሚመጣ እያሰበ ይሆናል። ይህም በመዝሙራት ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡን ነፃ ለማውጣት የሚነሣው ከሲና ተራራ እንደሆነ ስለተገለጸ ነው [መዝ. (68)፡17–18]። በተጨማሪም ኢሳይያስ በመብረቅ፥ በነጎድጓድና በደመና በተሞላ

ታላቅ ማዕበል መካከል እንደሚመጣ ተናግሮአል። እነዚህ ሁሉ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ቁጣ፥ በዓለም ላይ የሚሰጠውን ፍርድ የሚገልጹ ናቸው (ዘጸ. 13፡21፤19፡18)።

2. በተጨማሪም ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ከንፈሮቹ በቁጣ እንደተሞሉ አድርጎ ገልጾአል። ከከንፈሩ የሚወጡ የማጽናኛ ቃላት የሉም።

3. እግዚአብሔር ምላሱ በመርዝ ከተሞላ እባብ ጋር ተነጻጽሮአል። ይሁንና፥ ከእግዚአብሔር አፍ የሚወጣው መርዝ ሳይሆን እሳት ነው። (ይህም እግዚአብሔር በጦር መሣሪያዎች ሳይሆን በሚናገረው የቃሉ ፍርድ እንደሚዋጋ ያሳያል።)

4. የእግዚአብሔር ኃይል ቆሻሻውን ለማስወገድ ጨፍን በወንፊት ከምትነፋ ሴት ጋር ተነጻጽሮአል። እግዚአብሔርም የዓለምን አገሮች ሁሉ በፍርድ በማንቀጥቀጥ፥ ሐሰተኛውንና ከንቱውን ይለየዋል።

5. ሰው ይታዘዘው ዘንድ በፈረስ አፍ ውስጥ ልጓም እንደሚከትት፥ እግዚአብሔርም በዓለም ሕዝብ አፍ ውስጥ ልጓምን ይከታል። እግዚአብሔር ሕዝቡን ይሄዱ ዘንድ ወደሚፈልግበት መንገድ ይመራል። በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ለምንድን ነው? ይህ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ተጨማሪ ፍርድ እንደሚያመጣ የሚያመለክት ነበር። ሕዝቡ ሆን ብለው በእግዚአብሔር ላይ ዓምፀዋል። የፈጸሙት በደል ያልታሰበበት ስሕተት ሳይሆን፥ ግልጽ ዓመፅ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡ በዓመፃቸው እንዲቀጥሉ በመፍቀድና በማበረታታት የፍርድ ተግባሩን ይፈጽማል። በዚህ ዓይነት የባሰ ፍርድ ከእግዚአብሔር ይቀበላሉ።

ለ. ሕዝበ እግዚአብሔር በማዳኑ ደስ ይላቸዋል። እግዚአብሔር በክፉ የዓለም ሕዝብ ላይ እንደሚፈርድ እየተናገረ ሳለ፥ ኢሳይያስ ፍርዱ በሚፈጸምበት ጊዜ ሕዝበ እግዚአብሔር ምን እንደሚመስሉ ከመቅጽበት ይገልጽ ጀመር። እግዚአብሔር የሕዝቡን አመለካከት አይሁዶች ሁሉ በእግዚአብሔር ቸርነት ደስ ከሚሰኙበት እንደ ፋሲካ ካለ ታላቅ ሃይማኖታዊ በዓል ጋር አነጻጽሮታል። በበዓላት ወቅት ሕዝቡ በሙሉ ኃይላቸው በዜማ መሣሪያዎችና በመዘምራን ማኅሌት ደስ እየተሰኙ ወደ ቤተ መቅደሱ ይመጣሉ። ኢሳይያስ አይሁዶች እግዚአብሔር ጠላቶቻቸውን በመፍረድ የሚፈጽመውን የጽድቅ ተግባር በመመልከት እየዘመሩ የሚደሰቱበትን ሁኔታ ገልጾአል። (እንቢልታና በገና ከአይሁዶች ተወዳጅ የሙዚቃ መሣሪያዎች መካከል ሁለቱ ነበሩ።) በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር በጠላቶቻቸው ላይ እንዲፈርድ ለምእተ-ዓመታት ሲያቀርቡት የኖረው ጥያቄ ምላሽ ሲያገኝ ሕዝቡ በደስታ ይጥለቀለቃል።

ሐ. እግዚአብሔር አይሁዶች እጅግ የፈሩትን የአሦርን ሕዝብ ያጠፋል። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ታላቅ ተዋጊ እንደሆነ ሲገልጽ ቆይቶአል። አሁን ግን በዚያ ዘመን አይሁዶችን ለማጥፋት በሚሯሯጠው የአሦር ሕዝብ ላይ እግዚአብሔር የሚፈርድባቸው መሆኑን ይናገራል። አይሁዶች ከግብፅ እርዳታ እስከመጠየቅ የደረሱት አሦርን እጅግ ከመፍራታቸው የተነሣ ነበር። አሁን ግን እግዚአብሔር እንዴት ከአሦር እንደሚታደጋቸው ይናገራል። ተዋጊና የምድር ንጉሥ የሆነው እግዚአብሔር በፍርድ ይነሣል። አሁንም ከዙሪያው ያለውን የማዕበል ምስል በመጠቀም፥ እግዚአብሔር አሦርን ለመቅጣትና ለማጥፋት በትሩን ተጠቅሞአል።

ኢሳይያስ ቀደም ሲል የንጉሡንና የሕዝቡን ሞት ለማመልከት ወደ ተጠቀመው የመቃብር ምሳሌ እንደገና ይመለሳል (ኢሳይያስ 14፡9–11 ተመልከት።) በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው የአገሩ ወኪል የሆነው የአሦር ንጉሥ ነው። እግዚአብሔር በአሦር ንጉሥ ላይ የሚያመጣው ፍርድ ሕዝቡን ሁሉ ያጠፋዋል። የአሦር ውድመት ደግሞ እግዚአብሔር በሚያምፁበት አገሮች ሁሉ ላይ እንደሚፈርድ የሚያመለክት ነበር። የአሦር ታሪካዊ ፍርድ በመጨረሻው ዘመን እግዚአብሔር በአገሮች ላይ እንደሚፈርድም የሚያሳይ ነው።

ኢሳይያስ የአሦራውያንን ታላቅ ውርደት ለማሳየት በሰው አእምሮ ሊታሰብ የሚችለውን እጅግ የከፋ ተግባር በአስረጅነት ተጠቅሞአል። ቶፌት ነገሥታት ልጆቻቸውን ለሞሎክ ጣዖት የሚሠዉበት ከኢየሩሳሌም ወጣ ብሎ የሚገኝ አነስተኛ ሸለቆ ነበር (2ኛ ነገ. 23፡10፤ ኤር. 7፡31–32)። ሞሎክ በከነዓን ከሚመለኩት እጅግ ክፉ ጣዖታት አንዱ ነበር። ሞሎክ የአሞናውያን ጣዖት ሲሆን፥ አምልኮቱ ሰውን እስከ መሠዋት ይደርስ ነበር። በኋላም አይሁዶች ይህንን ሸለቆ ለቆሻሻ መጣያነት ይጠቀሙ ጀመር። በተወሰነ ጊዜ ቆሻሻው ይቃጠል ነበር። በመሆኑም፥ ከዚህ ስፍራ በተደጋጋሚ እሳትና ጢስ ይወጣ ነበር። (በኢየሱስ ክርስቶስ ዘመን፥ ይህ ስፍራ የዘላለማዊ ጥፋት ስፍራ የሆነው የሲኦል ተምሳሌት ሆኖ ተጠቅሶአል።) ስለሆነም ኢሳይያስ በዚህ ስፍራ የሚያስተላልፈው መልእክት የሰው መሥዋዕት የሚቀርብበትና ቆሻሻ የሚቃጠልበት ይኸው ሸለቆ የአሦርን ንጉሥ (ሕዝብ) ሰውነት ለመቀበል በእንጨትና እሳት እንደተዘጋጀ ነው። በፍርድ ቀን፥ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ሰዶምንና ጎሞራን እንዳጠፋው የሰማይ እሳት አሦርን ያጠፋዋል። የአሦር ንጉሥ ኢየሩሳሌምን እንደሚወጋና ድልን እንደሚቀዳጅ አስቦ ነበር። እርሱ ያልተገነዘበው ነገር ቢኖር ይህ ሞቱን እንደሚያፋጥንና በጥንታዊ የነገሥታት የቀብር ሥነ–ሥርዓት በኃይለኛ እሳት እንደሚቃጠል ነበር።

22ኛ ጥያቄ፡–እግዚአብሔር ትክክል ስላልሆኑ ቃል ኪዳኖችና ስለ ሕዝቡ ጠላቶች ምን ዓይነት አመለካከት እንዳለው ከዚህ ክፍል የተማርኸውን ግለጽ።

## ኢሳይያስ 31

አራተኛውም ወዮ በይሁዳ ለሚኖሩት አይሁዶች የተነገረ ነው። ይህም አሦርን ለመውጋት ይቻላቸው ዘንድ ልዑካኖቻቸውን ወደ ግብፅ ለሚልኩት መሪዎች የተላለፈ የ‹ወዮ› ማስጠንቀቂያ የዚህ ምዕራፍ ትኩረት እግዚአብሔር ያለማንም እርዳታ ኢየሩሳሌምን ከአሦር ነፃ እንደሚያወጣ መግለጽ ነው። ለአይሁዶች እውነተኛ ማዳን የሚገኘው በእግዚአብሔር እጅ ሆኖ ሳለ የሰውን እርዳታ የመጠበቅን ከንቱነት የሚያሳይ ነበር።

23ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ 31ን አንብብ። (ሀ) እግዚአብሔር በቁጥር 1 ይሁዳን የሚወቅሰው ለምንድን ነው? (ለ) በዚህ ክፍል እንደተመለከተው፥ እግዚአብሔር ሊሰጥ የሚችለውን እርዳታ ግብፅ ልትሰጥ ከምትችለው ጋር አነጻጽር። (ሐ) እግዚአብሔር በአሦር ላይ እርምጃ በሚወስድበት ሁኔታና በአንበሳ መካከል ያለው ተመሳሳይነት ምንድን ነው? (መ) አይሁዶች እግዚአብሔር ለእነርሱ እንደሚሠራ በሚረዱበት ጊዜ የሚገኘው የመጨረሻ ውጤት ምንድን ነው? (ቁ.6) (ሠ) ስለ አሦር የተነገሩትን የተለያዩ ትንበያዎች ዘርዝር። (ረ) የዚህን ምዕራፍ ዐበይት ትንቢቶች በራስህ አገላለጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

### 1. የእግዚአብሔርና የግብፅ ይሁዳን የመርዳት ችሎታ

**ሲነጻጸር (ኢሳ. 31፡1–3)**

ሰዎች የሚፈልጉዋቸው ሦስት ዓይነት እርዳታዎች አሉ። እነዚህም አጋንንታዊ፥ ሰብዓዊና መለኮታዊ ናቸው። በዚህ ምንባብ እግዚአብሔር ሰብዓዊና መለኮታዊ እርዳታዎችን በማነጻጸር፥ ሰዎች መለኮታዊ እርዳታ ሊያገኙ ሲችሉ በሰብዓዊ ሀብቶች ላይ መደገፋቸው ሞኝነት የሆነበትን ምክንያት ያሳያል። እግዚአብሔር ሁለቱንም ለማነጻጸር በሚዛን ላይ አስቀምጠአቸዋል። የትኛው ይበልጣል?

ከሚዛኑ በአንደኛው ወገን የግብፅ እርዳታ አለ። በአምንታዊ መልኩ ሲታይ፥ ግብፅ ብዙ ወታደራዊ ዓቅም ያላት ይመስላል። ብዙ ፈረሶችና ሰረገሎች ነበሯቸው። በአብዛኛው እግረኛ ጦር ብቻ ላላት እንደ ይሁዳ ላለች አገር እነዚያ ሁሉ ፈረሶች ያሉት ወታደራዊ ኃይል አስደማሚ ሊመስል ይችላል። ከአሉታዊ ጎኑ ሲታይ ግን ግብፆች ሰዎች ነበሩ። ሰዎች እንደ መሆናቸው፥ ወታደሮቻቸው በጦርነት ተሰናክለው ይወድቃሉ። የማይሸነፉ አልነበሩም፤ እንደ ማንኛውም ሰው አልመች ካላቸው ቃላቸውን አይጠብቁም። ግብፆች አሦር ከእነርሱ የበለጠ ኃይል እንዳላትና በጦርነቱ እንደሚሸነፉ ካሰቡ፥ ከይሁዳ ጋር የገቡትን ቃል ያጥፉ ነበር። በኋላም ይኸው እውነታ ነበር የተከሰተው።

በሚዛኑ ሌላ አቅጣጫ የእግዚአብሔር እርዳታ አለ። በአሉታዊ ገጹ ሲታይ፥ እግዚአብሔር መንፈስ በመሆኑ ለሰዎች አይታይም። ስለሆነም በእርሱ ላይ መደገፉ አዳጋች ይሆናል። እምነትን ይጠይቃል። በአዎንታዊ ገጹ ሲታይ ግን እግዚአብሔርን ከሁሉም የላቀ አጋዥ የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች አሉ።

ሀ. እግዚአብሔር *የእስራኤል ቅዱስ* ነው። በሌላ አገላለጽ፥ እርሱ በምድር ላይ ካሉት ነገሮች ሁሉ የተለየ ነው። ከእርሱ ጋር ሊነጻጸር የሚችል ኃይል የለም። እርሱ የእስራኤል አምላክ ሲሆን፥ ለእርሱ በመታዘዝ ከተመላለሱ እንደሚዋጋላቸው ቃል ገብቶላቸዋል።

ለ. እግዚአብሔር *ጠቢብ* ነው። የግብፅንና የአሦርን ነገሥታት ውስጣዊ አሳቦች ስለሚያውቅ፥ ዕቅዶቻቸውን ሁሉ ሊያናጋ ይችላል። ሁልጊዜም ፍሬያም ውጤት የሚያስገኝ ዕቅድ ሊያወጣ ይችላል። ከእግዚአብሔር ታላቅ ጥበብ ጋር ሲነጻጸር፥ የይሁዳ መሪዎች በራሳቸው ወይም በግብፅ ጥበብ *መመካታቸው* አሳፋሪ ነበር።

ሐ. እግዚአብሔር *አደጋን ሊያመጣ* ይችላል። (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «ክፉን ነገር ያመጣል» ይላል። ትክክለኛው ትርጉም ግን «አደጋን ያመጣል» የሚለው ነው።) ይህ እውነት ሁለት ገጽታዎች አሉት። እግዚአብሔር የሕዝቡ ጠላቶች በሆኑት አሦራውያንና ግብፃውያን ላይ እንደፈለገ አደጋን ሊያመጣ ይችላል። ስለሆነም ሕዝቡን ከማንኛውም ሁኔታ ነፃ የማውጣት ችሎታ አለው። እርሱ አምላክ ስለሆነ፥ የሚቋቋመው ሰብዓዊ ኃይል አይኖርም። ነገር ግን እግዚአብሔርን ባለመታዘዝ በሚመላለሱት ልጆቹም ላይ አደጋን ሊያመጣ ይችላል። ከኢየሩሳሌም በስተቀር ብዙ የይሁዳ ከተሞች በአሦር እንዲወረሩና የሰው ሕይወት እንዲጠፉ ያደረገው እግዚአብሔር ነበር።

መ. እግዚአብሔር *መንፈስ* ስለሆነ፥ ከእርሱ ጋር ሊዋጋ የሚችል ሰብዓዊ ሠራዊት የለም።

ሠ. እግዚአብሔር *ስለማይዋሽ*፥ እርሱ የተናገረው ቃል ሁሉ ሁልጊዜም ይፈጸማል (ዘኍ. 23፡19)።

ረ. በጦርነት ውስጥ አይደክምም፤ ወይም የሰዎችን እርዳታ አይፈልግም።

እንግዲህ አይሁዶች የትኛውን እርዳታ *መምረጥ* አለባቸው? በግልጽ እንደሚታየው፥ እግዚአብሔርን መምረጡ የበለጠ አስተዋይነት ነው። እግዚአብሔር የማይታይ አምላክ ቢሆንም፥ ለሕዝቡ ከሁሉም የተሻለ የእርዳታ ምንጭ ነው። ከግብፅ ጋር የሚደረግ ቃል ኪዳን ጊዜንና ገንዘብን በከንቱ ማጥፋት ነበር። የሚያሳዝነው ግን ሕዝቅያስ እንደ አባቱ አካዝ ሁሉ ከእግዚአብሔር ይልቅ በግብፅ *መታመንን* መረጠ።

ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ የወሰዱት እርምጃ በእግዚአብሔር አለማመናቸውን እሳይቷል።

24ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ይኸው በእግዚአብሔር እንጂ በሰዎች ላይ ያለመደገፉ ጠቃሚ እውነት ዛሬም ለእኛ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ በእግዚአብሔር ሳይሆን በሰው እርዳታ ላይ እንዴት እንደሚደገፉ የሚያሳዩቱን አንዳንድ ምሳሌዎች ግለጹ።

## 2. እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል (ኢሳ. 31፡4–7)

ሁለት ምሳሌዎችን በመጠቀም፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን እንዴት ከጠላቶቻቸው እንደሚጠብቅ ገልጾአል። <u>መጀመሪያ</u>፥ የአንበሳ ምልክት አለ። ይህንን አስመልክቶ ሁለት ዓበይት አተረጓጎሞች አሉ።

ሀ. አንበሳው በግ የሆነችውን ኢየሩሳሌምን ለማጥፋት የሚመጣው አሦር ነው። ዋጋ የሌላቸው እረኞች ግብፆች ናቸው። አሦር ኢየሩሳሌምን እንዳታጠቃ ለማድረግ ግብፅ የምትመታው መላ አልነበራትም። ይህንን ሊያደርግ የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

ለ. አንበሳው እግዚአብሔር ሲሆን እረኛው አሦር ነው። በግን የገደለ አንበሳ የእረኞችን ጫጫታ እንደማይፈራ ሁሉ፥ እግዚአብሔር በአሦር ሠራዊት ብዛት አይደናገጥም። ይልቁንም እንደ ኃያል ተዋጊ፥ እግዚአብሔር ለጽዮን ተራራ ወይም ለኢየሩሳሌም ለመዋጋት ከሰማይ ይወርዳል። እግዚአብሔር የአሦርን ሠራዊት በማጥፋት ኃይላቸውን አውድሞታል። ከዓውደ–ንባቡ አንጻር ይኼኛው አተረጓጎም የበለጠ ተስማሚ ይመስላል።

<u>ሁለተኛ</u>፥ የንስር ምሳሌነት ተጠቅሶአል። (የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «እንደሚበርር ወፍ» ሲል ተርጉሞታል።) ንስር እንቁላሎቿንና በኋላም ጫጩቶቿን ለመከላከል ከጎጆዋ ላይ ትበራለች። እንስሳ ወይም ሰው ቢመጣ ጥቃት ትሰነዝራለች። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ እግዚአብሔርም በኢየሩሳሌም ላይ በመስፈራ ከአሦር ሠራዊት ይጠብቃታል። በቁጥር 5፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ከተማዪቱን እንደሚከልልና እንደሚታደግ ገልጾአል። ኢሳይያስ የእግዚአብሔር መልአክ በበር መቃኖቻቸው ላይ ደም የተቀባባቸውን የአይሁዳውያን ቤቶች «እያለፈ» የግብፃውያንን በኩራት የገደለበትን ሁኔታ የሚገልጹትን የዘጸአት 12፡13፥ 23 ቃላት ተጠቅሞአል። ለአይሁዶች ደም ትንሽ ነገር ቢመስላቸውም፥ እነርሱን ከሞት የመጠበቅ ኃይል ነበረው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ኃይላቸው ትንሽ ቢመስልም እግዚአብሔር ከተጠቀመበት የአሦርን ሠራዊት ያወድማል። በተመሳሳይ መንገድ፥ የእግዚአብሔር መልአክ የኢየሩሳሌምን ከተማ በማለፍ የአሦርን ሠራዊት ያጠፋል። ያለምንም የሰው እርዳታ፥ የእግዚአብሔር መልአክ አንድ መቶ ሰማኒያ አምስት ሺህ ወታደሮች ገድሎአል ( ኢሳ. 37፡36)።

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ሕዝብ እንደሚያድን እየገለጸ ሳለ ለይሁዳ ነዋሪዎች ልመና አቀረበ። ከጠላት ለመዳን በሰዎች ሳይሆን በእግዚአብሔር ይታመኑ ዘንድ ለመናቸው። በተጨማሪም፥ ጣዖታትን በማስወገድና ለቃሉ በመታዘዝ ወደ እግዚአብሔር ሊመለሱ ይገባቸው ነበር። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕዝቡን በመቅጣት ከአምልኮተ-ጣዖታት የሚመልስበትን የወደፊት ዘመን «በዚያም ቀን» ሲል ገልጾአል። በኋላ እግዚአብሔር በባቢሎን ምርኮ አማካኝነት አይሁዶች በአካባቢያቸው የነበሩትን ጣዖታት ለማምለክ የነበራቸውን ፍላጎት አስወግዶአል። ይሁንና፥ ትንቢቱ በዋናነት የሚፈጸመው ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመለስና የሰዎች ልብ ሙሉ ለሙሉ ተለውጦ እግዚአብሔርን መከተል ሲጀምሩ ነው።

3. እግዚአብሔር አሦርን ያጠፋታል (ኢሳ. 31፡8–9)

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የአሦርን ሠራዊት የሚደመስስበት ጊዜ ሲደርስ፥ በሰዎች ሳይሆን በራሱ መለኮታዊ ጣልቃ-ገብነት ተግባሩን እንደሚያከናውን ገልጾአል። እግዚአብሔር አንድን ሠራዊት በተለያዩ መንገዶች ሊደመስስ ይችላል። ለመቅጣት የሚፈልገውን አገር ሌላ ሠራዊት እንዲያጠቃው ሊያደርግ ይችላል። ወይም ደግሞ እንደ ጎርፍ፥ የመሬት መንቀጥቀጥና ረሃብ የመሳሰሉትን የተፈጥሮ አደጋዎች ሊያመጣ ይችላል። በዚህ ጊዜ ግን እግዚአብሔር በቀጥታ ራሱ እንደሚሠራ ገልጾአል። ስውር ሰይፉ የአሦርን ሠራዊት ይበላል። መልአኩን ልኮ ኢየሩሳሌምን የከበቡትን ወታደሮች በመፍጀት እግዚአብሔር የአሦርን ውድመት የመጀመሪያ ክፍል ያከናውናል።

የአሦር ውድመት ሁለተኛ ክፍል በአገሪቱ ውስጥ ይፈጸማል። እግዚአብሔር ሌላ ሠራዊት ያመጣበታል። ሠራዊቱ በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር በወጣት ተዋጊዎች ላይ ፍርሃትን ይለቃል። ፈርተው የማያውቁት አሁን በፍርሃት ርደው በጦርነቱ ይሸነፋሉ። የጠላትን የውጊያ ስልት ሲመለከቱ ሳይዋጉ ሩጠው ይጠፋሉ። ከዚያም በቀላል ውጊያ ምሽጋቸው የሆነችው ነነዌ ትያዛለች። ከታሪክ እንደምንረዳው፥ ይህንኑ ውጊያ ያካሄደችው እና ነነዌን የተቆጣጠረችው ባቢሎን ነች።

እግዚአብሔር ተናግሮአል። በኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ የሚያድረው የእስራኤል አምላክ ታላቅ ፈራጅ ነው። እንደ አጥፊ እሳት ፍርዱን በአሦራውያን ላይ በማምጣት ሕዝቡን ከእነርሱ ጭቆና ያድናል። እግዚአብሔር እንደዚህ ታላቅ አምላክ ከሆነ ሕዝቡ ንስሐ ገብተው እርሱን በመታዘዝ መኖር አይገባቸውም? በእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ ሊታመኑ አይገባቸውምን?

25ኛ ጥያቄ፡– ከዚህ ምዕራፍ ክርስቲያን ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት አንዳንድ አስፈላጊ ትምህርቶችን ዘርዝር።

## ኢሳይያስ 32

26ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን መምሰል ማለት ምን ማለት ነው? አጭር ገለጻ ጻፍ። ለ) ክርስቲያኖች እንደ ኢየሱስ መሆናቸውን የሚያመለክቱትን አንዳንድ አጠቃላይ ባሕርያት ጻፍ። ሐ) ኢሳይያስ 32፡1–2 አንብብ። ይህ ክፍል እንደሚለው፥ እግዚአብሔርን የሚወድ ሰው ምን መምሰል አለበት? የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቀው እንዴት ነው? በቁጥር 2 የተመለከቱትን ነገሮች የምትገልጽባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

ጨረቃ ከፀሐይ የተቀበለችውን ብርሃን እንደምታንጸባርቅ ሁሉ፥ የክርስቲያኖችም ባሕርይ የኢየሱስ ክርስቶስን ባሕርይ ማንጸባረቅ አለበት። ኢሳይያስ 32፡1–2 ሰዎች ከአዳምና ሔዋን ዘመን ጀምሮ ያወቁአቸውን የአገዛዝ መንገዶች የሚቀይር እና በጽድቅ የሚያስተዳድር መሪ እንደሚመጣ ይናገራል። ኢሳይያስ ከጻድቅ መሢሕ ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ያለው ሰው ምን መምሰል እንዳለበት ገልጾአል። ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር ለመግለጽ የተጠቀመባቸውን ተመሳሳይ ቃላት በመጠቀም ገልጾታል። ያ ሰው ከማዕበል የሚጠልልና የሚጎዱትን ሰዎች የሚያስጠጋ ይሆናል (ኢሳ. 25፡4 ተመልከት)። እርሱ በበረሃ ውስጥ እንደተገኘ የውኃ ምንጭና በችግር ሐሩር ለተቃጠሉት ጥላ ይሆንላቸዋል (ኢሳ. 35፡6–7፤ 41፡18፤ 49፡10 ተመልከት)።

እግዚአብሔር ሰዎችን ለመባረክ ይፈልጋል። ብዙውን ጊዜ ግን ይህንን የሚያደርገው ልጆቹን በመጠቀም ነው። ልጆቹ እግዚአብሔር የችግርተኞችን ጉድለት የሚሞላባቸው አሸንዳዎች ናቸው። በዚህም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማንጸባረቅ ብቻ ሳይሆን፥ ለሚሠቃየውና ለሚጎዳው ዓለም እግዚአብሔርን ይወክላሉ። እግዚአብሔርን መወከልና ፍቅሩን በውስጣችን እንዲፈስ ማድረግ ሲሳነን እግዚአብሔር ለዓለም ሊሰጥ የሚፈልገውን በረከት እንገድባለን።

27ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 32ን አንብብ። ሀ) አንድ ቀን የሚመጣው ንጉሥ ምን እንደሚመስል ግለጽ። ለ) ያ ንጉሥ በሚመጣበት ጊዜ የመሪዎች አገዛዝና የሰዎች አኗኗር ምን እንደሚመስል ግለጽ። ሐ) ይህ ለሰዎች ምን ዓይነት ለውጦችን ያመጣል? (ቁ. 3–8)። መ) በሰነፍና በከበርቴ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት አነጻጽር። ይህ ዛሬ በዓለም ውስጥ የሚታየው እንዴት ነው? ሠ) እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን ሴቶች ባሕርይ የሚገልጸው እንዴት ነው? ምንስ ይደርስባቸዋል? ረ) የኢየሩሳሌምን ሁኔታ የሚለውጥ ምን ይከሰታል? (ቁ. 15) ሰ) የእግዚአብሔር በረከት በሚመለስበት ጊዜ በምድር ላይ የሚከሰቱትን ነገሮች ዘርዝር። ሸ) የዚህን ምዕራፍ ዐቢይ ትምህርት በራስህ አገላለጽ ጠቅለል አድርገህ ጻፍ።

ኢሳይያስ በአይሁዶችና በአሕዛብ ላይ ፈጥኖ ከሚደርሰው ፍርድ ወደ መጨረሻው የምድር የበረከት ዘመን እንዴት ፈጥኖ ዘወር እንደሚል ከትንቢተ ኢሳይያስ ጥናት በተደጋጋሚ ተመልክተናል።

የአሦርን ውድመት ከገለጸ በኋላ፥ ኢሳይያስ መጭውን መሢሕና የእርሱ መምጣት በምድር ላይ የሚያስከትላቸውን ነገሮች ይዘረዝራል። በጠንካራ የፍርድ ትንቢቶች መሀል፥ ኢሳይያስ ስለ ውጭው የእግዚአብሔር መንግሥት በመግለጽ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሰዎች በታማኝነታቸው ተስፋ በማድረግ እንዲቀጥሉ ያበረታታቸዋል።

1. የሚመጣው የጽድቅ መንግሥት ውጤቶች (ኢሳ. 32፡1–8)

በዚህ ክፍል፥ ኢሳይያስ የሚያተኩረው በዘመን መጨረሻ ላይ በሚነግሠው መሢሕ በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አይደለም። ይልቁንም፥ በእነዚያ ዘመናት ሰዎች ምን እንደሚመስሉ ገልጾአል። ይህንንም የሚያደርገው በዚያን ጊዜ የሚኖሩ ሰዎች ከዛሬዎቹ እንዴት እንደሚለዩ በማስረዳት ነው። እነዚህ ጥቅሶች እኛም ዛሬ እግዚአብሔር ለሰጠን ደረጃ በማለም እንደ እግዚአብሔር ልጆች እንዴት ልንኖር እንደሚገባን ያሳያሉ። (ማስታወሻ፡ በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ እነዚህ ጥቅሶች መጭውን ንጉሥ ብቻ ወይም ሌሎችንም ነገሥታት የሚያመለክቱ ለመሆናቸው ቁርጥ ውሳኔ ላይ ለመድረስ የሚያደናግሩ ናቸው። ስለሆነም አንዳንድ ምሑራን ይህንን ምዕራፍ በሁለቱም አቅጣጫ ያያሉ። እኛ ደግሞ በሌሎች ሰዎች ሕይወት የሚከሰቱትን ለውጦች ጭምር እንደሚናገሩ አድርገን ለመመልከት እንፈልጋለን።)

ሀ. መሪዎች በፍትሕ ይገዛሉ። የመጨረሻው ዘመን አሁን ዓለም ካለችበት ሁኔታ በጣም የተለየ ይሆናል። ገዥዎች በሥልጣናቸው ሕዝቡን የበዘበዙበት ወቅት ያልፋል። በቤተሰቦችና በነገዶች መካከል አድልዎ የተደረገባቸው ቀናት ያልፋሉ። መሪዎች ሁሉ ለሰዎች ጥቅም ተግተው በመሥራት ከአድልዎ የጠራ ተግባር ያከናውናሉ። መጭው ንጉሥ ማለትም መሢሑ በጽድቅ ይገዛል። የእርሱ መንግሥት አካል የሆኑት በተለይም ሌሎች ነገሥታት ሁሉ እንደ እርሱው በጽድቅ ይገዛሉ።

ለ. እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ሰው ጥቅም ይሠራል። (ማስታወሻ፥ ይህ ጥቅስ በዕብራይስጥ የሚያመለክተው እያንዳንዱን ሰው ይሁን ወይም መሢሑን ግልጽ አይደለም። የተለያዩ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉሞች በተለያዩ መንገዶች ይረዱታል።) መጽሐፍ ቅዱስ ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር የሕይወት ውጣ ውረድ ላለባቸው ሰዎች መጠጊያ እንደሆነ ያሳያል። በመጨረሻው ዘመን ግን ሰዎች ከራስ-ወዳድነት መንገዶቻቸው ተመልሰው ሌሎችን ይረዳሉ። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚያደርጋቸውን አገልግሎቶች በመውሰድ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ እያንዳንዱ ሰው የእግዚአብሔርን አገልግሎቶች እንደሚያከናውን ይገልጻል። የችግር ነፋሳት ሰውን ለመጣል ሲሹ፥ ሌሎች እጆቻቸውን ዘርግተው ይረዱታል። የበሽታ ማዕበል ሲከሰት፥ መጠጊያና ረዳት ይሆኑታል። ለግል ጥቅም ከመሯሯጥ ይልቅ በበረሃ

ውስጥ እንደሚፈስ የምንጭ ውኃ እያንዳንዱ ሰው ለሌላው የበረከት ወንዝ ያፈልቅለታል። በቁረሃ መካከል ከፀሐይ እንደሚከልል የዛፍ ጥላ ወይም ትልቅ ድንጋይ እያንዳንዱ ሰው ለሌላው ደስታን ይፈጥርለታል።

ሐ. መንፈሳዊ ዓይኖች ተከፍተው ሰዎች ስለ ሕይወት አስፈላጊ ነገሮች ግንዛቤ ይኖራቸዋል። ከአዳምና ሔዋን ዘመን ጀምሮ የዓለም ችግር ሰዎች መንፈሳዊ እይታቸውና መንፈሳዊ ግንዛቤአቸው በኃጢአት የተገደበ መሆኑ ነው። ምንም እንኳ በዓለም መመዘኛ ጠቢባን ተደርገው ሊታሰቡ ቢችሉም፥ በእግዚአብሔር ዓይኖች ሞኞች ናቸው። ሁልጊዜም እውነተኛው ጥበብ የሚበየነው አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ግንኙነት አኳያ ነው። ሰሎሞን ይህንን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» ሲል ይገልጻል (ምሳሌ 1፡7)። እውነተኛ የጽድቅ ንጉሥ በሚመጣበት ጊዜ ሰዎች ነገሮችን ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር የማይረዱባቸው ጊዜያት ያልፉና አይሁዶችም ሆኑ አሕዛብ እንደ ቃሉ መኖር ይጀምራሉ (ይህን ከኢሳይያስ 6፡9–10 ጋር አነጻጽር)።

ኢሳይያስ በዓለም ውስጥ ሁለት ዓይነት ሰዎች እንዳሉ ገልጾአል። እነዚህም ሞኞችና ጠቢባን ናቸው። ዓለም በዓለማዊ እውቀትና ጊዜያዊ ነገሮች ላይ ስለምታተኩር፥ ራሷን እንደ ጠቢብና ለሕይወት ችግሮች መፍትሔ እንዳላት አድርጋ ታስባለች። ስለሆነም ማታለልንና ማጭበርበርን ታበረታታለች። በፈጣን ምላሳቸው ከችግር የሚወጡትን ወይም ውሸትን እውነት ነው ብለው የሚያሳምኑትን ሰዎች ታደንቃለች። በመሆኑም ዓለማዊ ጥበብ ብዙውን ጊዜ ሰዎችን እግዚአብሔር ካዘዘው መንገድ ይመልሳቸዋል። ክፉትን በመለማመድ ሌሎችም በክፉት ውኃ ውስጥ እንዲንቦራጨቁ ያደርጋቸዋል። ሰነፍ ሰው ራስ–ወዳድ በመሆኑ ዘወር ብሎ የእግዚአብሔርን መንገዶች አይመለከትም። ነገር ግን ሌሎችን ለመጉዳት ኃይሉን ይጠቀማል። በሰው ዓይን ፊት ብልህ የሚመስሉትም ቢሆኑ በእግዚአብሔር ፊት ሞኞች ናቸው። ከአፍንጫቸው ሥር ያሉትንና ሊሞቱ የሚቀሩትን ጊዜያዊ ነገሮች በመከታተል ይኖራሉ። በዓይን በሚታዩና ጠንካራ በሚመስሉ፥ ነገር ግን አሳሳቢው ሁኔታ በሚከሰትበት ጊዜ የእርዳታ እጃቸውን ሊዘረጉ በማይችሉ ነገሮች ይታመናሉ።

ጠቢብ ሰው ግን ከዚህ የተለየ ነው። (ኢሳይያስ እግዚአብሔርን የሚያስከብር ባሕርይ ያላቸውን ሰዎች ለማመልከት ከበርቴ የሚል ቃል ተጠቅሞአል።) ሕይወቱና አስተሳሰቡ በእግዚአብሔር ቃል የሚመሩ በመሆናቸው ዘላለማዊ ውጤት አለው። የሚያስበው በራስ–ወዳድነት ችግሮቹን ለማሟላት ሳይሆን፥ ሌሎችን የሚጠቅሙ ዘላቂ ውጤቶችን ለማምጣት ነው። ግብሮቹ ወደ ኃጢአት ሳይሆን ወደ በጎነት የሚመሩ ናቸው። ጠቢብ ሰው እንደ ብዙ ሰዎች መልካም

ዕቅድ ማውጣት ብቻ ሳይሆን፥ ሥራዎቹ ተግባራዊ ውጤት ይኖራቸው ዘንድ ተግቶ ይሠራል። የሚያደርጋቸውም ተግባራት ለዘለቄታዊ ጸንተው የሚቆሙ ናቸው።

የሰዎች መንፈሳዊ ዓይኖች በሚከፈቱበት ጊዜ ከሚከሰቱት የመሢሑ መንግሥት በረከቶች አንዱ ሰዎች እውነተኛውን ጥበብ ከሐሰተኛው ለይተው ማወቅ የሚችሉ መሆናቸው ነው። ብያኔ የሚሰጡት እውነት የሚመስለውን በማየት ሳይሆን፥ ከእግዚአብሔርና ከዘላለም እይታ አንጻር በትክክል ተረድተው ነው።

28ኛ ጥያቄ፡- ሀ) ኢሳይያስ ስለ ጠቢብ ሰው ያቀረበው ሥዕላዊ መግለጫ በአብዛኛው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚታየው የሚለየው ለምንድን ነው? ለ) ዛሬ ክርስቲያኖች የሚመስሉት ጠቢቡን ነው ወይስ ሰነፉን? ለምን? ምሳሌዎችን ስጥ።

## 2. በኢየሩሳሌም ሴቶች ላይ የተሰጠ ጊዜያዊ ፍርድ

(ኢሳ. 32፡9–14)

በኢሳይያስ 3፡16–4፡1 ኢሳይያስ በኩራት ለተወጠሩ የኢየሩሳሌም ሴቶች ስለተሰጠው የእግዚአብሔር ፍርድ ገልጾአል። እግዚአብሔር ወንዶቻቸውን በማጥፋትና በምርኮ እንደሚያዋርዳቸው ተናግሯል። አሁን ኢሳይያስ ወደዚያው አሳብ በመምጣት በኢየሩሳሌም ሴቶች ላይ ስለሚመጣው ፍርድ እግዚአብሔር የሰጠውን ውሳኔ ያብራራል። እነዚህ ሴቶች በኩራታቸው ምክንያት ጥጋበኞች ሆነው ነበር። በኢየሩሳሌም ቅጥር ውስጥ ስለሚኖሩት ይሁዳም ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ስላደረገች ተማምነው ይኖሩ ነበር። «ማን ወንድ ሊነካን? ሠራዊታችን ቁሞ ይሂድ! ምንም ክፉ ነገር አይደርስብንም» የሚል አሳብ ነበረባቸው። እግዚአብሔር ግን ከዚህ የተለየ ዕቅድ ነበረው።

ሀ. የሰብል መውደም የምግብ እጥረት ያስከትላል። ከአንድ ዓመት ትንሽ በሚያልፍ ጊዜ ውስጥ እግዚአብሔር እነዚህ ሴቶች የተደገፉባቸውን ነገሮች ያነሣል። ይህም ምናልባትም የ710 ዓ.ዓ. የአሦርን ሠራዊት መምጣት የሚያመለክት ይሆናል። የአሦር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን በመክበቡ ከኢየሩሳሌም ቅጥር ውጭ የሚገኘው ሰብል ሁሉ ወድሞአል። ሴቶች አብዝተው ይደሰቱበት የነበረው ወይን ስለሚወድም አልያም ከከተማዪቱ ቅጥር ውጭ ስለሚቀር ሊያገለግላቸው አይችልም። በጠላት ሠራዊት ተከብበው በሚኖሩበት ወቅት የእርሻውን ተግባር ለማከናወን የደፈረ ወንድ አልነበረም። ይህም የእህልን እጥረት አስከተለ። ማንም ስለማይሠራበት የእርሻ መሬቱ እሾህና ኩርንችት ያበቅላል። (ማስታወሻ፥ ይህ በኢሳይያስ ምዕራፍ አምስት ለቀረበው ቅኔ ፍጻሜ ይሆናል።) ሴቶች ለቤተሰቦቻቸው ምግብ የማቅረብ ኃላፊነት ነበራቸው። አሁን ግን

ለቤተሰባቸው የሚሰጡት ምግብ ስለማይኖር ችጋር ይቆላቸዋል። ይህም ባለቤቶቻቸውን እንዳጡት ሴቶች ልቅሶ እንዲቀመጡ ያደርጋቸዋል።

ለ. የኢየሩሳሌም ከተማ ውድመት። አሦር በኢየሩሳሌም ላይ የምትፈጸመውን ጥቃት ማየቱ ኢሳይያስ ስለ ባቢሎን ውድመት እንዲያስብ አደረገው። ምናልባትም የአሦር ጥቃት አይሁዶች በባቢሎናውያን ወደሚወድሙበት ፍርድ የሚያሸጋግር ጊዜያዊ ቅጣት ይሆናል። የአሦር ሠራዊት በዚህ ጊዜ ወደ ኢየሩሳሌም ከተማ ገብቶ አላጠፋትም ነበር። በ586 ዓ.ዓ. የባቢሎን ሠራዊት የኢየሩሳሌምን ቅጥር አፍርሰው በመግባት ንጉሡንና ቤተ መንግሥቱን በመያዝ፥ ቅጥሩን ጨምሮ ቤተ መቅደሱንና ሌሎች በርካታ ሕንፃዎችን አውድመዋል። ይህም እግዚአብሔር በአይሁዶች ላይ እንደሚያመጣ የተናገረውን የሰባ ዓመታት ምርኮ ጀመረው። በኢየሩሳሌም ላይ ከፍተኛ ጥፋት የደረሰው በዚህ የምርኮ ወቅት ነበር። ሕዝቡ ወደ ምርኮ ሲሄዱና ቤቶቻቸው ሲፈርሱ፥ በሚጠብቁት ሕንፃዎች ተኩራርታ የኖረችው አምባይቱ ኢየሩሳሌም ወናዋን ትቀራለች። በዚህ ጊዜ በከተማይቱ ውስጥ ሰዎች አይኖሩም ነበር። ነገር ግን በአንድ ወቅት ሰዎች ይኖሩባት በነበረችው ከተማ እንስሳት ሣር ይግጣሉ።

### 3. የእግዚአብሔር መንፈስ በረከቱን መልሶ ያመጣዋል (ኢሳ. 32፡15–20)

ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር መንፈሱን የሚልክበት ጊዜ ስለሚመጣ፥ ኢየሩሳሌም አትወድምም። በእግዚአብሔር ፍርድ ምክንያት የተከሰተው የኢየሩሳሌም ውድመት ይቀለበሳል። (ማስታወሻ፥ በብሉይ ኪዳን አንዱ አምላክ በሦስት የመገለጡ እውነት በግልጽ አልተብራራም ነበር። ምንም እንኳ በዚህ ክፍል ስለ መንፈስ ቅዱስ የተሰጠው አሳብ ለዚህ እውነት እንደ ፍንጭ ቢያገለግልም፥ የአሀዱ–ሥሉስነትን መረጃ ሙሉ ለሙሉ የምናገኘው ከአዲስ ኪዳን ነው። በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር መንፈስ በሥራ ላይ የሚገኝ የእግዚአብሔር ኃይል እንጂ ሌላው የእግዚአብሔር አካል ተደርጎ አይታሰብም ነበር። ይሁንና፥ እግዚአብሔር በአዲስ ኪዳን ውስጥ የገለጠውን በምንመለከትበት ጊዜ የሰዎችን ልብ ለመለወጥ የእግዚአብሔርን ተግባር የሚያከናውነው መንፈስ ቅዱስ እንደሆነ እንረዳለን።)

መንፈስ ቅዱስ በሚመጣበት ጊዜ የእግዚአብሔር መንፈስ በሕዝቡ ላይ የበረከትን ዝናብ ያስከትላል። ይህም ሕዝቡን ብቻ ሳይሆን የሚኖሩበትን ምድር ጭምር ይለውጣታል (ኢሳ. 44፡3፤ ኢዩ. 2፡28–32)። ኢሳይያስ የእግዚአብሔር መንፈስ በሕዝበ እስራኤል (እና

በዓለም ሁሉ ላይ) በሚመጣበት ጊዜ ብዙ ነገሮችን እንደሚለውጥ ተናግሮአል።

ሀ. ምድሪቱ ተለውጣ ዳግም ፍሬያማ ትሆናለች። ምድረ በዳውም እህል ወደሚበቅልበት ፍሬያማ እርሻነት ይቀየራል። ፍሬያማውም እርሻ ወደ ዱርነት ይቀየራል። ይህም በኢሳይያስ ዘመን በሊባኖስ እንደነበረው ደን መሆኑ ነው። ባለማቋረጥ ምድሪቱን ከሚያጠጡት ወንዞች ሳቢያ ሁልጊዜም ምግብና መልካም መከር ይኖራል። ሰዎች በሕይወት ደስ ለመሰኘት የሚፈልጉትን ሁሉ ያገኙ ዘንድ ለሁሉም የሚበቃ ስፍራ ይኖራል። ሕዝብ ከመበርከቱ በፊት እንደነበረው የቀድሞ ዘመን ከብቶች በነጻነት ለመንቀሳቀስ ይችላሉ።

ለ. የሰዎች ባሕርይ ይለወጣል። ፍትሕ-አልበኝነትና የመብት ረገጣው ቀርቶ ጽድቅ ይሰፍናል። የሰዎች ልብ ስለሚለውጥ በአገሮችና በነገዶች መካከል ሰላም ይነግሣል። ሰዎች ወደ ጽድቅ እየተጠጉ ሲመጡ፥ የምድሪቱ መለያ የሚሆን መተማመንና ልበ-ሙሉነት ይኖራል። በሰዎች መካከል የነበረው ፍርሃት ለታማኝነት፥ ለእውነተኛነትና ጓዳን ለመከፋፈት ስፍራን ይለቃል። ይኸው የፍጹም መተማመንና ሰላም ሁኔታ ሌላ መሪ እስኪመጣ ድረስ የሚቆይ ጊዜያዊ ክስተት ብቻ አይሆንም። ነገር ግን በመሢሑ የአገዛዝ ዘመን የሚሠራ የመንፈስ ቅዱስ ውጤት በመሆኑ፥ ለዘላለም ይኖራል።

ሐ. ሕዝቡ ከጠላት ይድናል። ሕዝቡ በወራሪ ጠላት፥ ጉቦን በሚቀበሉ ዳኞች፥ በእሳት፥ በምድር መንቀጥቀጥ፥ ወዘተ. . . ከመረበሽ ተርፎ በሰላም ይኖራል። ፍጹም ሰላም ይሰፍናል።

ኢሳይያስ 32፡19 ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት መረዳቱ አስቸጋሪ ነው። በረዶ ምንድን ነው? ዱሩስ ማን ነው? በዚህ ክፍል የተጠቀሰችው ከተማ ማን ናት? በርግጠኝነት ልንናገር አንችልም። በረዶ እንደ ባቢሎን ባሉት የዓለም ጠላቶቹ ላይ እግዚአብሔር የሚያመጣው ፍርድ ተምሳሌት ይሆናል። ዱር ደግሞ ዓለምን በመቆጣጠር በሰዎች ዓይን ፊት ታላላቅ የሚመስሉትን እንደ አሦር ያሉ አገሮች የሚያመለክት ይመስላል። (ዱር አሦርን የሚያመለክት የሚመስልበትን የኢሳይያስ 10፡33-34 ምንባብ ተመልከት።) ቀደም ብለን እንደተመለከትነው፥ ከተማ የሰውን ልጅ ተቃውሞና ዓመፅ ሊያመለክት ይችላል። ኢሳይያስ እንደ እግዚአብሔር ልጆች የተባረኩትን ከሌሎች ሰዎች ጋር በግልጽ እያነጻጸረ ነበር። ሊሸነፉ የማይችሉ መስለው የሚታዩ ታላላቅ ዱሮች (ታላላቅ የጠላት ኃይላት) አንድ ቀን በእግዚአብሔር የፍርድ እጅ ይጠፋሉ። ለእግዚአብሔር ሕዝብ ግን የማያቋርጥ በረከት ይሆናል። ያ የበረከት ጊዜ እስኪደርስ ድረስ ሕዝቡ እግዚአብሔርን በሚያስከብር ተግባር ጸንቶ እንዲኖር ተመክሯል።

29ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ዓለም ፍጹም ሰላም፥ ደኅንነትና በረከት ወዳለበት ስፍራ እየመጣ መሆኑን ማስታወሱ ለክርስቲያኖች ለምን ያስፈልጋል? ለ) በምድር ላይ ስንኖር ስለሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት ግልጽ መረዳት ማግኘታችን የሚጠቅምባቸውን መንገዶች ዘርዝር። ሐ) የዘላለሙን መንግሥት በምንዘነጋበት ጊዜ የክርስትና ሕይወታችን ምን ይሆናል?

ይህ ትንቢት የመጨረሻውን ዘመን ሁኔታ በቀጥታ የሚገልጽ ነው ወይስ ተምሳሌታዊ? ይህ እግዚአብሔር የአሦርን ሠራዊት በሚያወድምበት ጊዜ ስለሚመጣው በረከት የሚናገር ነው ወይስ ስለ ሌላ ወቅት? ምሑራን በእነዚህ ጥያቄዎች ዙሪያ የየራሳቸውን አሳብ ሰንዝረዋል። ምንም እንኳ አሦር በወደቀችበት ወቅት እግዚአብሔር በምድረ ይሁዳ ጊዜያዊ በረከቶችን ቢያመጣም፥ በእነዚህ ምዕራፎች ውስጥ የተጠቀሰው ዓይነት ዘላቂ በረከት አልነበረም። ስለሆነም በኢሳይያስ አእምሮ ውስጥ የነበረው የመጨረሻው ዘመን ነበር ማለት ነው።

በክፍሉ ውስጥ የሚገኙ ሐረጎች «እግዚአብሔር በመጨረሻው ዘመን ሕዝቡን ይባርካል» ከሚለው የላቀ መልእክት የሚያስተላልፉ ይመስላል። የኢሳይያስ ዝርዝር ትንቢቶች በረከቶች በምድር እንጂ በሰማይ እንዳልሆኑ የሚያሳዩ ይመስላል። ምድር ትለወጣለች። በምድር ላይ የሚገኙ ዝምድናዎች ይለወጣሉ። የሰዎች የሕይወት ዘይቤ ይለወጣል። ስለዚህ ነው የቅድመ–ሺህ ዓመታት አመለካከት አራማጆች እነዚህ ትንቢቶች እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን በኩል በሰማይ የሚያመጣቸውን በረከቶች በተምሳሌትነት የሚያመለክቱ ናቸው የሚለውን አሳብ አልፈው፥ ትንቢቶቹ ኢየሱስ ክርስቶስ በሺህ ዓመት መንግሥት በምድር ላይ በሚነግሥበት ጊዜ በቀጥታ የሚፈጸሙ መሆናቸውን የሚገልጹት።

30ኛ ጥያቄ፡– በዚህ ክፍል ውስጥ የተጠቀሱትን ትንቢቶች ከሁሉም በተሻለ ሁኔታ የሚያብራራው የትኛው አመለካከት ነው ብለህ ታስባለህ? ለምን?

## ኢሳይያስ 33

31ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እግዚአብሔርን መፍራት ማለት ምን ማለት ነው? ለ) እግዚአብሔርን በምንፈራበትና በማንፈራበት ጊዜ ነገሮች እንዴት እንደሚለወጡ አነጻጽር። ሐ) በኢሳይያስ 33፡5–6፥ እግዚአብሔር እርሱን በምንፈራው ጊዜ የሚሰጠን አንዳንድ ሀብቶች (መዛግብት ምንድን ናቸው?

32ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ 33ን አንብብ። ሀ) አጥፊውና ከዳተኛው ምን ይሆናሉ? ይህ ማንን የሚያመለክት ይመስልሃል? ለ) በቁጥር 2 ኢሳይያስ ለሕዝቡ የሚጠይቀው ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር በሕዝቡ ፋንታ መሥራት ሲጀምር አገሮች ምላሽ የሚሰጡት እንዴት ነው? (ቁ. 3–4)። መ) እግዚአብሔር ለልጆቹ የሚሰጣቸውን መዛግብት ዘርዝር። እነዚያን መዛግብት የሚያገኙት ምን ዓይነት ምላሽ ሲሰጡ ነው? ሠ) ስምምነቱ በሚፈርስበት ጊዜ የሕዝቡ ምላሽ ምን ይሆናል? (ቁ. 7–9)። ረ) ከቅዱሱ

አምላክ ጋር የሚኖረውን ሰው ብቃቶች ዘርዝር (ቁ. 14–16)። የእያንዳንዱን አሳብ ምንነት አስረዳ። ሰ) እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚሠራበት ጊዜ ውጤቱ ምን ይሆናል? (ቁ. 17–24)። ሸ) የዚህን ትንቢት ቁልፍ አሳብ በራስህ ቃላት አጠቃልለህ ጻፍ።

በዚህ ምዕራፍ ኢሳይያስ በአሦር ላይ የተሰጠውን ስድስተኛ ወዮ ማለትም የፍርድ ትንቢት ይናገራል። (አንዳንድ ምሁራን በምዕራፍ 30–31 ያሉትን ሁለት ወዮዎች አንድ ላይ በማድረግ የወዮዎቹን ቁጥር ወደ አምስት ያወርዱአቸዋል።) ኢሳይያስ እግዚአብሔር በአሕዛብ በተለይም በአሦራውያን ላይ የሚያመጣውን ፍርድ በእስራኤላውያን ላይ ከሚያመጣው በረከት ጋር ያነጻጽራል። የዚህ ምዕራፍ ሥረ-መሠረት ምናልባትም አሦራውያን ወደ ኢየሩሳሌም እየገሠገሡ ለወረራ መሰማራታቸውና ቀደም ሲል በእስራኤል መንግሥት ላይ የፈጸሙትን ጥቃት በይሁዳ ላይ እንደሚደግሙ መስጋቱ ሳይሆን አይቀርም። ነገሮች ተስፋ የሌላቸው ይመስሉ ነበር። አጋራቸው የነበረችው ግብፅ ኃላፊነቷን በመውጣት ከይሁዳ ጎን አልተሰለፈችም። ከግብፅ ጋር ቃል ኪዳን ለማድረግ ያወጡት ገንዘብና ጊዜ ሁሉ ከንቱ ሆነ። ሊረዳቸው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ በመሆኑ በኢሳይያስ በኩል እንደሚታደጋቸው ተናገረ። ይሁንና፥ ሊታደጋቸው ቃል በሚገባበት ጊዜ የበረከቶቹን መዝገብ ለመቋደስ ምን ዓይነት ሰዎች መሆን እንዳለባቸው ገለጸላቸው። እግዚአብሔር ይሁዳን ከጠላት በማዳን ጊዜያዊ በረከት እንድታገኝ አድርጎአል። ነገር ግን በዚህ ክፍል የተጠቀሱት ብዙዎቹ የተስፋ ቃሎች የሚፈጸሙት መሢሕ በሚመለስበት በመጨረሻው ዘመን ነው።

## 1. አሦር የምትወድምበት ጊዜ ደርሶአል (ኢሳ. 33፡1ን)

ኢሳይያስ ይህንን የመጨረሻ ወዮ ያቀረበው «ለአጥፊው» እና «ከዳተኛው» ነው። አጥፊውና ከዳተኛው ማን እንደሆነ አልተገለጸም። ለዚህም ምክንያቱ ኢሳይያስ ትንቢቱን በሚናገርበት ጊዜ ስለ ማን እንደሚናገር ሕዝቡ የሚያውቁ መሆናቸው ነው። አንዳንድ ሰዎች አሦር «ከዳተኛ» (የ1980 እትም) የተባለው ሕዝቅያስ ገንዘብ ስለሰጠው እንደሆነ ይናገራሉ። አሦር ግን ስምምነቱን አልፎ ይሁዳን አጠቃ። ኢሳይያስ ይህንን ትንቢት የተናገረው የአሦር ሠራዊት ኢየሩሳሌምን ለማጥቃት ይበልጥ እየተጠጋ ባለበት ወቅት ነበር። ይህም ተስፋ የሌለው ይመስል ነበር።

አሦር የማይሸነፍ ይመስል ነበር። ቀደም ሲል ሌሎችን አገሮች አውድመው ነበር። ስምምነት ካደረጉ በኋላ ያመኑዋቸውን ሰዎች በመክዳት ጥቅማቸውን ያስከብሩ ነበር። እግዚአብሔር ግን ተቆጣጣሪያቸው እንደ መሆኑ ነገሮች እንደሚለወጡ ተናገረ። አሦራውያን በሌሎች አገሮች በተለይም በእስራኤልና ይሁዳ ላይ

ፍርድን ለማምጣት የተጠቀመባቸው የእግዚአብሔር መሣሪያዎች ነበሩ። የቅጣት መሣሪያነታቸው በሚያበቃበት ጊዜ ግን አሦራውያን በተራቸው ይወድማሉ። አሦራውያን የተመኩባቸው ሌሎች አገሮችም ይከዱዋቸዋል። በሌሎች ላይ የፈጸሙትን ክሕደት፥ ያደረሱትን ሞትና ምርኮ ሁሉ ይቀምሳሉ። ከአንድ መቶ ዓመታት በኋላ የባቢሎን መንግሥት ተነሥቶ ከአሦራውያን ጋር ያደረገውን ስምምነት ቸል በማለት ለውድመትና ለምርኮኛነት ዳረጋቸው። (አንድ ምሑር የዚህን መርህ እንደሚከተለው ገልጾታል፤ «ለሁሉም አታላይ ከእርሱ የተሻለ አታላይ ለመኖሩ እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ ያለው ፍጹም አስተዳደር ዋስትና ይሰጠናል። ይህም በመጨረሻው አታላዮች ሁሉ በብልጠታቸው እስከሚጠፉበት ጊዜ ድረስ የሚቀጥል ይሆናል።»)

## 2. ኢሳይያስ እግዚአብሔር ያድናቸው ዘንድ ያቀረበው ጸሎት (ኢሳ. 33፡2–3)

የአሦር ሠራዊት እየቀረበ ሲመጣ፥ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ካልረዳቸው በቀር ችግሮች ውስጥ መግባታቸውን ተመለከተ። ስለሆነም በጭንቀት ውስጥ ሆኖ እግዚአብሔር ቸርነቱን ያሳያቸው ዘንድ ጮኸ። ሊያድናቸው የሚችለው ነገር ቢኖር እግዚአብሔር ሳይገባቸው ለሰዎች የሚሰጠው ጸጋ ብቻ ነበር። ኢሳይያስ ቅጣት እንደሚገባቸው ቢያውቅም፥ የእግዚአብሔርን ሞገስ ለመነ። እግዚአብሔርን የጠየቀው ለሁለት ነገሮች ነበር። አንደኛ፥ የዚያን ዕለት ተግዳሮት የሚጋፈጡበትን ክንድ ወይም ብርታት ጠየቀ። ከሕዝቡ ለሚደርሰው ስድብ፥ በጦርነት ወቅት ለሚከሰት ረሃብ፥ ወዘተ. . . እግዚአብሔር «ጥዋት ጥዋት ክንዱ» ይሆናቸው ዘንድ ለመነ። ሁለተኛ፥ «በመከራም ጊዜ ማዳን ሁነን» ሲል ጸለየ። ኢሳይያስ ከአሦር ያድናቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ጠየቀ።

ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ኃይል ስለሚያውቅ በልበ-ሙሉነት ጸለየ። እግዚአብሔር ለሕዝቡ በሚሠራበት ጊዜ ኃያላን ኃይላቸውን ያጣሉ። እግዚአብሔር በፍርዱ በሚሠራበት ጊዜ አገሮች ከፍርዱ ለማምለጥ ይሸሻሉ። እግዚአብሔር የሕዝቡን ጠላቶች በሚያሸንፍበት ጊዜ ሀብታቸውን የአንበጣ መንጋ እንደወረድበት ሰብል ሙሉ ለሙሉ ይበዘበዛል።

## 3. እግዚአብሔር ለሚወዱት ያዘጋጀው መዝገብ (ኢሳ. 33፡5–6)

ኢሳይያስ በጸለየበት ጊዜ የልበ-ሙሉነት ምንጭ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነበር። ለዚህ ነው የእግዚአብሔርን ባሕርያት ማጥናት የሚያስፈልገው። የእግዚአብሔርን ማንነት እስካላወቅን ድረስ መከራ በሚደርስብን ጊዜ በእምነት የምንጓዝበትን መተማመን ለማግኘት እንቸገራለን። እግዚአብሔር ብቻውን ሕዝቡን ከወራሪ ጠላት

ለመጠበቅና ለመንከባከብ ይችል ነበር። ወደ ግብፅ ማዘንበሉ አስፈላጊ አልነበረም። ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር የተናገረውን ልብ በል።

ሀ. እግዚአብሔር ከፍ ያለ እና በከፍታ የሚኖር ነው። እግዚአብሔር ሰዎች በምናባቸው እንደቀረጹዋቸውና ወደ ጣዖትነት እንደለወጡዋቸው አማልክት ደካማ አልነበረም። እግዚአብሔር እንደ አጽናፈ-አቀፉ ንጉሠ-ነገሥት በሰማያት የሚኖር እውነተኛ አምላክ ነው። ቀደም ብለን በኢሳይያስ 32፡15 እንደተመለከትነው፥ እግዚአብሔር መንፈሱን በሕዝቡ ላይ የሚያፈስሰው ከላይ ነው። ከእርሱ ቁጥጥር ውጭ በምድር ላይ የሚከሰት ነገር የለም። በምድር ላይ ሊያሸንፈው ወይም ዕቅዶቹን ሊያከሽፍበት የሚችል ነገር የለም። አሥራውያን የይሁዳን አምላክ በአማልክቶቻቸው እንደሚያሸንፉ አስበው ነበር። ነገር ግን እውነተኛው አምላክ በሰማይ ስለሚገኝ፥ ሊደርሱበት አይችሉም ነበር። ይልቁንም እነርሱና አማልክቶቻቸው ተሸነፉ። እንዲያውም አሦር በእግዚአብሔር እጅ ውስጥ ያለ በትር ብቻ ነበረች።

ለ. በሕዝቡ መካከል ፍትሕና ጽድቅ እንዲኖር የሚያደርገው እግዚአብሔር ነው። ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ ስለሚፈጸመው ነገር ግድ የሌለው የሩቅ አምላክ እንዳልሆነ ያውቅ ነበር። እግዚአብሔር ድሆችና እርሱን ፈርተው ለመኖር የሚፈልጉ ሰዎች የሚጋፈጡአቸውን ፍትሕ-አልበኝነቶች ያውቃል። ነገር ግን ኢሳይያስ እግዚአብሔር ቃል ኪዳን የገባላቸው ሕዝብ የሚኖሩባት የጽዮን ተራራ በፍትሕና ጽድቅ እስከትሞላ ድረስ እንደሚሠራ ያውቅ ነበር።

ሐ. እግዚአብሔር እውነተኛ *መሠረት* ይሆናል። የሕዝብ ወይም የቤት ጥንካሬ የሚለካው እንደ *መሠረቱ* ነው። *መሠረቱ* ወታደራዊ ጥንካሬ ከሆነ፥ ጊዜያዊ እንጂ ዘለቄታዊ ብቃት አይኖረውም። የሃብት ወይም የጥበብ *መሠረትም* ቢሆን *መፈራረሱ* አይቀርም። እጅግ ኃይለኛ በሆነው ማዕበል ሳይቀር ጸንቶ የሚኖረው አንድ *መሠረት* ብቻ ነው። ያ *መሠረት* እግዚአብሔር ነው። የአሦርና የባቢሎን ሠራዊት በሚመጣበት ጊዜ ሳይቀር ሁልጊዜም ሕዝቡን የሚታደገው እግዚአብሔር ብቻ ነው።

መ. እግዚአብሔር የበለጠ የደኅንነት ምንጭ ይሆንላቸዋል። መንፈሳዊ ደኅንነትና አካላዊ ነፃ *መውጣት* የሚገኘው ከእግዚአብሔር ነው። አይሁዶች ሠራዊታቸው ምንም ያህል ቢበዛ እንደማያድናቸው ማወቅ ነበረባቸው። ወይም ደግሞ ሌላ የትኛውም አገር ሊያድናቸው እንደማይችል ማወቅ ነበረባቸው። እግዚአብሔር ብቻ ሊያድናቸው ይችል ነበር። እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ፈቃደኛ ባለመሆን፥ ሌላ ጊዜ ደግሞ ዓቅም በማጣት የሚቸገር ደካማ የደኅንነት ምንጭ

አልነበረም። ይልቁንም የደኅንነት ጉድለታቸውን የሚሞላ ብቁ አምላክ ነው። የእግዚአብሔር የደኅንነት ቤተመዛግብት ምን ጊዜም አይራቆትም።

ሠ. እግዚአብሔር የማይወሰን የጥበብና የማስተዋል ምንጭ ይሆናል። አይሁዶች በጣም ውስብስብና ግራ አጋቢ ሁኔታ ውስጥ ነበሩ። አይሁዶች ከአሦር ጭቆና ነፃ ለመውጣት ፈልገው ነበር። እንደ ግብፅ ያለ ሌላ አገር ይህን የሚያደርግላቸው መስሎአቸው ነበር። ነገር ግን አሦራውያን ወዲያውኑ ሊያጠቁዋቸው ደረሱ። የታመኑባቸው ሰዎች ግን ብቅም ሳይሉ ቀሩ። አይሁዶች ምን ማድረግ ነበረባቸው? እንዴት መቆም ነበረባቸው? ጊዜው አደናጋሪ ሲሆንና ግልጽ መፍትሔ ሳይኖር ሲቀር እንዴት እንደሚኖሩ ማስተዋልንና ጥበብን ሊሰጣቸው የሚችለው እግዚአብሔር ብቻ ነበር።

ይሁንና፥ ኢሳይያስ እነዚህ በረከቶች ከመቅጽበት እንደሚመጡ አልተናገረም። ወደ እግዚአብሔር ቤተመዛግብት የሚያስገባውን በር የሚከፍት ቁልፍ (ይህ ቃል በአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አልተጠቀሰም) ነበር። ይህ ቁልፍ እግዚአብሔርን መፍራት ነበር። ምንም እንኳ በከፊል እውነት ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱስ፥ ፈሪሃ እግዚአብሔር ማለት ለእግዚአብሔር ኃይልና ግርማ የምንሰጠው ስሜታዊ ምላሽ አይደለም። ፈሪሃ እግዚአብሔር የሚጀምረው የእግዚአብሔርን ማንነት ከማወቅ ነው። ይኸውም እግዚአብሔር ፈጣሪ፥ ቃል ኪዳን አድራጊ፥ ነፃ አውጪ፥ የደኅንነት ምንጭ፥ ወዘተ. . . መሆኑን ማወቅ ነው። እንዲሁም ደግሞ እንዲህ ላለው ታላቅ አምላክ የሰው ልጅ ሊሰጥ የሚገባውን ትክክለኛ ምላሽ መረዳትን ያካትታል። ሁለንተናችን በትሕትና ለእግዚአብሔር መገዛቱን የሚጨምር መሆን አለበት። በመጨረሻም፥ ከወላጁ ላይ የተቀመጠ ልጅ ያለው ዓይነት እምነት ሊኖረን ይገባል። ፍርሃትና ትግል ሳይኖር በእግዚአብሔር ማረፍ ወሳኝ ነው። እንዲህ ዓይነቱ አመለካከት የእውነተኛ ደኅንነት ምልክት ነው።

33ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ምንም ዓይነት ምላሽ እስከማይኖርህ ድረስ እጅግ ከባድ የሆነብህን አንድ ሁኔታ ግለጽ። ለ) የእግዚአብሔርን ባሕርይ ማወቅ ያንን ሁኔታ በተሻለ መንገድ እንድትጋፈጥ የረዳህ እንዴት ነው? ሐ) ግልጽ ምላሽ በሌለን ጉዳይ በምንወዛገብበት ጊዜ ስለ እግዚአብሔር እነዚህን ነገሮች ማወቅ እንዴት ይረዳናል?? መ) ፈሪሃ እግዚአብሔር ለዚያ ሁኔታ የሰጠኸውን ምላሽ ሊለውጥ የሚችለው እንዴት ነው?

## 4. በኢየሩሳሌም የሚኖሩ አይሁዶች ተስፋ –የለሽ ሁኔታ (ኢሳ. 33፡7–9)

ኢሳይያስ እግዚአብሔርንና «እግዚአብሔርን ለሚፈሩት» የሰጠውን ልበ–ሙሉነት ከተመለከተ በኋላ፥ በ701 ዓ.ዓ. አሦር ኢየሩሳሌምን

በከበባት ጊዜ ወደ ነበረው ትክክለኛ ሁኔታ ይመለሳል። ከተማዪቱን ይጠብቃሉ የተባሉት «ኃይለኞች» ወታደሮች በፍርሃት ተዋጡ። «የሰላም መልእክተኞች» የግብፅን እርዳታ ለመሻት ወደዚያው የተጓዙት ወይም ከአሦር ንጉሥ ጋር ለመደራደር የሄዱት የሕዝቅያስ መልእክተኞች ተስፋ በመቁረጥ አምርረው አለቀሱ (ኢሳ. 36፡3፥ 22)። የአሦር ሠራዊት ከተማዪቱን በመክበቡ በመንገዶቹ ላይ የሚጓዝ አልነበረም። ሁሉም በኢየሩሳሌም ከተማ ውስጥ ተደበቀ። ሰዎች ወጣ-ገባ ብለው ሊገዙ፥ ሊሸጡ፥ ምግብም ወደ ከተማዪቱ ሊገባ ባለመቻሉ ኢየሩሳሌም ውስጥ የመሸጉ ሰዎች ለችጋር ተዳረጉ። ለስምምነቱ ዋጋ የሰጡ ምስክሮች መኖራቸው ከቁም ነገር ሳይቆጠር ከግብፅና ከሌሎች አገሮች ጋር ያደረጉት ስምምነት ፈረሰ። ይህ ከግብፅ ጋር የተደረገውንና ነገር ግን ግብፅ አሦር እንዳታጠፋት በመስጋት ያፈረሰችውን ቃል ኪዳን የሚያመለክት ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ንጉሥ ሕዝቅያስ ከአሦር ጋር ያደረገውና በኋላ የአሦር ንጉሥ የነበረው ሰናክሬም ያፈረሰው ሊሆን ይችላል (2ኛ ነገ. 18፡14 አንብብ።)

ምድሪቱ ሳይቀር በዚህ ጊዜ እንዴት እንደምትጎዳ ለማሳየት ኢሳይያስ ቅኔያዊ አገላለጽ ተጠቅሟል። ግብርናው ሳይካሄድና ወራሪው ጦር የእርሻ መሬቶችን እየረገጠ በሚመላለስበት ወቅት ይሁዳ ከፍተኛ ጉዳት ይደርስባታል። እሾህ ሲበቅልባትና ወደ ባድማነት ስትለወጥ ምድሪቱ እንደ መበለት ታለቅሳለች። ለዝግባ ዛፎችና እንስሳት የታወቀው ሊባኖስ ዛፎቹ በመቆረጣቸውና ምድሪቱ በመጎሳቆሏ ለአደጋ ይጋለጣል። በሜድትራኒያን ዳርቻ በለምለምነቱ የሚታወቀው የሳሮን ሜዳማ ስፍራ በሙት ባሕር ያለውን ምድረ በዳ መስሎ ይለወጣል። መስኮቹ ባለመታረሳቸውና እህል ባለመዘራቱ ምድሪቱ ከጥቅም ውጭ በመሆን ነዋሪዎቿን መመገብ ይሳናታል። ከዮርዳኖስ ወንዝ በስተ ምሥራቅ የሚገኘውና በልምላሜው የታወቀው ባሳንና «ለምለም መስክ» የሚል ፍች ያለው ቀርሜሎስ ከእንግዲህ ምግብ የማቅረብ ዓቅም አይኖረውም። ነገር ግን ከወራሪው ጦር የተነሣ ባላገሩ ውኃ በማጣት እንደጠወለጉና እንደታመሙ ዛፎች ይሆናል። በመሆኑም፥ ቅጠሎቻቸውን አራግፈውና ዕድገታቸውን አቅበው ይሞታሉ። 185,000 ወታደሮች ያሉት ወራሪ ጦር በአንድ አገር ላይ የሚያደርሰውን አደጋ መገመቱ አስቸጋሪ አይሆንም።

### 5. እግዚአብሔር በሕዝቡ ፋንታ ይሠራል (ኢሳ. 33፡10–24)

#### ሀ. እግዚአብሔር ሕዝቡን ለማዳንና ጠላቶቹን ለማጥፋት ይነሣል (ኢሳ. 33፡10–14)

ነገሮች ጽልመታዊ ገጽታ በተላበሱ ጊዜ እግዚአብሔር ለመሥራት ቃል ገባ። እግዚአብሔር ሕዝቡ በራሳቸው ኃይል ወይም ጥበብ

ራሳቸውን ያዳኑ እንዳይመስላቸው ቀደም ብሎ ከጠላቶቻቸው ሊያድናቸው አልፈለገም። ነገር ግን ነገሮች እጅግ አስጨናቂ ሲሆኑና ሁሉም ሰው ተስፋ በቆረጠ ጊዜ እግዚአብሔር ሊሠራ መረጠ። ኢሳይያስ የሁኔታውን ተስፋ ቢስነት ለመግለጽ በተጠቀመው ተምሳሌታዊ ቋንቋ ሴት አርግዛ ስትወልድ የተገኘው ገለባ ብቻ መሆኑ ተናግሯል። እስትንፋሳቸውም የምትበላቸው እሳት ትሆናለች። ኢሳይያስ ይህን ሲል አይሁዳውያን እግዚአብሔርን ከዕቅዳቸው ውጭ አድርገው በራሳቸው ጥበብና ችሎታ የአሦርን ሠራዊት ለማሸነፍ እንደጣሩ መግለጹ ነበር። ይህ በእግዚአብሔር ላይ አለመደገፍ ኃጢአት ያጠፋቸው ነበር። ትንሽ ያለማመን ተግባር እንደ ትንሽ እሳት ስለሆነ ተስፋ ያደረጉትን ሁሉ ይበላዋል። እግዚአብሔር የዘገየው የደኅንነታቸው ምንጭ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ስለፈለገ ነው። ያን ጊዜ እርሱ ብቻ ይከብራል።

(ማስታወሻ፡ ምናልባትም ኢሳይያስ አሦርን እንደ እርጉዝ ሴት እየገለጻት ይሆናል። ኢየሩሳሌምን ለማሸነፍና ለማጥፋት የያዟቸውን ዕቅዶቻቸውን አርግዘው ነበር። ነገር ግን ዕቅዶቻቸው ምንም ያህል ታላቅ ቢሆኑም የመጨረሻው ውጤት ዕቅዶቻቸው የትም እንደማይደርሱ ነው። የእግዚአብሔር የፍርድ እስትንፋስ እሳት ገለባን እንደሚያጠፋ ያጠፋቸዋል።)

34ኛ ጥያቄ፡– እግዚአብሔር አንዳንድ ጊዜ ጸሎታችንን ዛሬውኑ የማይመልሰው ለምንድን ነው?

እግዚአብሔር በአንድ ሌሊት 185,000 ወታደሮችን በገደለ ጊዜ ኢየሩሳሌምን እንዳዳናት ታወቀ። በዓለም ሁሉ የሚገኙ አገሮች ይህንን ሲሰሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደተዋጋ በማወቅ ይፈሩታል። በኢየሩሳሌምና በይሁዳ የሚኖሩትም የእግዚአብሔርን ታላቅ ኃይል በመገንዘብ ወደፊት ችግሮች በሚገጥሟቸው ጊዜ በእግዚአብሔር ላይ ይደገፋሉ።

እግዚአብሔር በአሦር ላይ የመፍረዱን ተግባር በሌሎች ሕዝቦች መካከል ፍርሃትና አክብሮት ሲያሳድር እግዚአብሔርን በተቃወሙት አይሁዳውያን ላይ ግን ፍርሃትን አሳድሯል። እግዚአብሔር እርሱን ባላወቁትና ስለ እግዚአብሔር መንገዶች ግልጽ ግንዛቤ ባልነበራቸው አሦራውያን ላይ እንዲህ ያለ ፍርድ ካመጣ፥ በአይሁዶችስ ላይ ምን ያመጣ ይሆን? አይሁዶች የእግዚአብሔርን ቃል ያውቁ የነበረ ሲሆን፥ ኢሳይያስና ሌሎችም ነቢያት ስለ ሥራዎቻቸው ውጤቶች ያስጠነቅቋቸው ነበር። ስለሆነም አይሁዶች ለሕይወታቸው መፍራት ነበረባቸው። እግዚአብሔር ይፈርድባቸው ይሆን?

በተመሳሳይ ሁኔታ ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር ለእነርሱ በመቆም በማያምኑ ሰዎች ላይ ፍርድን በሚሰጥበት ጊዜ ለራሳቸው

ማስጠንቀቂያ ሊወስዱ ይገባል። እግዚአብሔር እርሱንና የወንጌሉን እውነት ባላወቁት ላይ ፍርድን ካመጣ፥ የወንጌልን እውነት እያወቁና እንከተለዋለን እያሉ ሆን ብለው ኃጢአት በሚሠሩት ሰዎች ላይ የበለጠ ፍርድ አያመጣባቸውምን? እግዚአብሔር ሲፈርድ አያዳላም። እርሱም እከተልሃለሁ እያለ በኃጢአታቸው የሚያምፁትን ይቀጣል።

**ለ. ከቅዱስ አምላክ ጋር የመኖር ብቃት ያላቸው (ኢሳይያስ 33፡14–16 አንብብ)**

ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ምን ያህል ታላቅና ኃያል እንደሆነ በመረዳት፥ «የሚባላ እሳት ከሆነ አምላክ ጋር ማን ሊኖር ይችላል?» ሲል ራሱን ጠየቀ። ዛሬ በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ ከፍተኛ ትኩረት ስለምናደርግ አስፈሪነቱን በቀላሉ ልንዘነጋ እንችላለን። እግዚአብሔር ጠላቱን የሚያጠፋ እሳት ከሆነ በሕዝቡ ላይ የሚፈርድ እሳትም የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም። ኢሳይያስ እንዳለው እግዚአብሔር «ለዘላለም የሚነድድ እሳት» ነው። (አንዳንድ የማብራሪያ መጻሕፍት ጸሐፊዎች ይህንን የሚናገሩት ኃጢአተኞቹ አይሁዶች እንደሆኑ ያስባሉ። የአሦር ሠራዊት ስለደረሰና የእግዚአብሔር የፍርድ እጅ ስለተገለጠች፥ በከፍተኛ ደረጃ እየቀጣቸው ካለው አምላክ ጋር እንዴት እንደሚኖሩ በማሰብ መጠየቃቸው ነበር። በእነዚህ ምሑራን አመለካከት በዚህ ስፍራ የተጠቀሱት ሁለት ጥያቄዎች «በገዛ ከተማችን የእግዚአብሔርን ጊዜያው ቅጣት ለመቋቋም ካልቻልን እንዴት አድርገን ዘላለማዊ ቅጣቱን እንታገሣለን?» የሚል መልእክት የሚያስተላልፉ መሆናቸውን ያስረዳሉ።)

35ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር «የሚባላ እሳት» እና «ለዘላለም የሚነድ እሳት» መሆኑን የምንዘነጋው ለምንድን ነው? (ዕብራውያን 12፡25–29 ተመልከት።) ለ) በአምልኮአችንና በአኗኗራችን እግዚአብሔር የሚባላ እሳት እንደሆነ ብናስታውስ፥ ሕይወታችን እንዴት ይለወጣል?

ኢሳይያስ አምልኮተ እግዚአብሔር በጉባኤ ውስጥ መዝሙሮችን በምንዘምርበት ጊዜ ከሚሰማን ስሜት የላቀ መሆኑን ተገንዝቦአል። ቆሻሻዎችን ሁሉ እንደሚያጠፋ እሳት ኃይለኛ ለሆነው አምላክ የምናቀርበው አምልኮ ሕይወታችን እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ መቃኘት እንዳለበት የሚጠይቅ ነው። ኢሳይያስ የጠቅላላውን አካል ምሳሌ በመጠቀም እሳቱ ሳይጎዳው ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ሰው ባሕርያት ዘርዝሮአል።

1. በጽድቅ የሚሄድ። በዕብራይስጥ ቋንቋ፥ መሄድ የሚለው ፈሊጣዊ አገላለጽ አጠቃላይ የሕይወት አኗኗር ተደርጎ ይታያል። ስለሆነም አንድ ሰው እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው በሁለንተናው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ ሲኖር ነው። አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር

ትክክለኛ ግንኙነት የሚኖረው እንደ እግዚአብሔር ቃል ትእዛዛትና መርሆዎች ለመኖር ሲችል ነው። እንዲህ ዓይነቱ ሰው የእግዚአብሔር ቃል በፍቅር ራሱን ለሌሎች እንዲሰጥ በሚያስተምረው መርህ ስለሚኖር ከሰዎች ጋር ትክክለኛ ግንኙነት ይኖረዋል። (ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ባሕርያት ሁሉ በጽድቅ መመላለስ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ያስረዳሉ። እግዚአብሔር ሊቀበል የሚችለውን ሰው መሠረታዊ ግንዛቤ ያስጨብጣሉ።)

2. ቅን ነገርን የሚናገር። ምላሳችን ወይም ንግግራችን ውስጣዊ ሕይወታችንን ለመለካት የሚረዳ ጥሩ ‹ቴርሞ ሜትር› ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ አፋችን የሚናገረው ነገር የልባችንን ሁኔታ እንደሚያሳይ ገልጾአል (ማቴ. 12፡32–37፤ 15፡10–20)። ስለሆነም በቁጣ፥ ወይም በሀሜት፥ ወይም በወቀሳ ቃላት የተሞላ ሰው እንደ እግዚአብሔር ፈቃድ እንደማይመላለስ ያሳያል። ኢሳይያስ የሕዝበ እግዚአብሔር ንግግር ትክክል መሆን እንዳለበት ገልጾአል።

3. በሽንገላ የሚገኝ ትርፍን የሚንቅ። እግዚአብሔር ክርስቲያን ተግቶ በመሥራት ገንዘብ እንዳያገኝ አላዘዘም። ነገር ግን ገንዘቡን የምናገኝበት መንገድ ያሳስበዋል። አንድ ሰው የመንግሥት ወይም የቤተ ክርስቲያን ሥልጣኑን በመጠቀም ከሌሎች ገንዘብን ከተቀበለ ወይም የሌሎች ግለሰቦችን ጥቅም ለራሱ ካዋለ፥ እግዚአብሔር እንዲህ ዓይነቱን የአኗኗር ስልት ይጠላዋል። (ኢሳ. 1፡16–17፥ 23፤ 3፡14–15 ተመልከት።)

4. መማለጃን ከመጨበጥ እጁን የሚያራግፍ። ከብዙ ታላላቅ አገሮች ውድቀቶች ምክንያት አንዱ ባለሥልጣኖቻቸው ጉቦ የሚቀበሉ መሆናቸው ነው። ጉቦ ካልተሰጣቸው መደበኛ ተግባራቸውን አያከናውኑም። እንዲህ ዓይነቱ ሙስና የማኅበረሰቡን መሠረታዊ መዋቅር ስለሚያጠፋ፥ ውሳኔዎች የሚተላለፉት በፍትሕ ሳይሆን በገንዘብ አማካኝነት ይሆናል። በዚህ ዓይነቱ አሠራር እጅግ የሚጎዱት ገንዘብ የሌላቸው ድሆች ናቸው። ለዳኞችና ለባለሥልጣናት የሚያቀርቡት እጅ መንሻ ስለማይኖራቸው ፍትሕን ሊያገኙ አይችሉም። ከዚህ የተነሣ የአገሪቱ መሠረት እኩልነትና ፍትሕ መሆኑ ቀርቶ ፍትሕ–አልበኝነት ይሆናል። የኋላ ኋላ የብዙዎች ሥቃይ እና ሙስና አገሪቱን ስለሚያጠፉት እንዲህ ዓይነቱ አገር ጸንቶ ሊቆም አይችልም። ብዙ ክርስቲያኖች «ጉዳይህን ቶሎ ለመፈጸም የሚቻለው በዚህ መንገድ ነው» እያሉ ጉቦ መስጠታቸውን ይቀጥላሉ። በዚህ ዓይነት አገራቸውን የሚያጠፋውን አሠራር ይከተላሉ። በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡ ክርስቲያኖችም፥ «ሁሉም የሚያደርገው ነው፥ ባለሥልጣናት እንደ መሆናችን ይህ የሚገባን ስጦታ ነው» እያሉ ጉቦ (ገንዘብ፥ ስጦታና ግብዣን) መቀበላቸው አልቀረም። እንዲህ ዓይነቶቹ

ሰዎች ግን በራሳቸው፥ በአገራቸውና በቤተ ክርስቲያናቸው ላይ የእግዚአብሔርን ፍርድ እየጋበዙ መሆናቸው አይታያቸውም።

5. ደም ማፍሰስን ከመስማት ጆሮዎቹን የሚያደነቁር። ብዙውን ጊዜ ወደ ጋጢአት የሚመራን የመጀመሪያው ነገር ጆሮአችን ነው። እግዚአብሔርን የሚያስከብሩ ሰዎች የሚሰሙትን ነገር ይመርጣሉ። አንድ ሰው ስለ ደም ማፍሰስ ሊሰማ የሚችለው ሰውን መግደል በአእምሮአቸው ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ ጥያቄ በማይፈጥርባቸው ሰዎች አካባቢ የተገኘ እንደሆነ ነው። ስለሆነም ትክክለኛ ያልሆኑትን ነገሮች ከመስማትና የተሳትፎ እንቅስቃሴ ከመውሰድ (ለምሳሌ ከሐሜት) መታቀብ የሚቻልበት አንዱ መንገድ አብረውን የሚያሳልፉ ሰዎች ከእንዲህ ዓይነት ባሕርያት የጸዱ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። ነገር ግን ሰዎች ስለ ክፉ ነገሮች በሚነጋገሩባቸው አካባቢዎች ስንገኝ እንኳ ስፍራውን ለቅቀን በመሄድ ጆሮዎቻችንን ልናደነቁር እንችላለን። ወይም ደግሞ ሌሎች ክርስቲያኖችን ሐሜቱን አቁመው በገንቢ ውይይት ላይ እንዲያተኩሩ ልናደፋፍራቸው እንችላለን። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ከሚከሰቱ ክፍፍሎች አብዛኞቹ የሚፈጸሙት ሰዎች ተጨባጭነት የሌላቸውን ወሬዎች በመስማታቸውና በማዛመታቸው ምክንያት ነው።

6. ክፋትን ከማየት ዓይኖቹን የሚጨፍን። ዓይን ሌላው የክፋት ጎዳና ነው። ብዙውን ጊዜ የምንመለከተው ነገር የተሳሳተ ተግባር ወደማከናወኑ መስመር ይመራናል። ኢዮብ ሴትን ላለማየት ከዓይኑ ጋር ቃል ኪዳን እንዳደረገ ተናግሯል (ኢዮብ 31፡1)። ኢዮብ ይህንን ሲል ክፋት ልቡንና ሕይወቱን እንዳይገዛ የሚመለከተውን ነገር እንደሚመርጥ መግለጹ ነው። በቴሌቪዥን፥ በቪድዮ ፊልሞች ወይም በመጻሕፍት ውስጥ የምንመለከተው አሳብ ለክፋት የሚያነሣሣን ከሆነ፥ እነዚህን ነገሮች ላለማየት ከዓይናችን ጋር ቃል ኪዳን ማድረግ አለብን።

36ኛ ጥያቄ፡- ሀ) በቅርቡ የፈጸምሃቸውን አንዳንድ ጋጢአቶች ዘርዝር። አንተን በጋጢአት ለመፈተን ሰይጣን የተጠቀመው የትኛውን የአካል ክፍልህን ነው? (ዓይን፥ ጆሮ. . .) ለ) በምታደርጋቸው፥ በምትናገራቸው ወይም በምትመለከታቸው ነገሮች አማካኝነት ጋጢአትን እንዳትሠራ በንቃት የወሰድሃቸውን እርምጃዎች ዘርዝር።

ለመሆኑ በዚህ ዓይነት ሁኔታ የሚኖሩት ሰዎች ሽልማት ምንድን ነው? ኢሳይያስ ሦስት ነገሮችን ዘርዝሮአል።

ሀ. ከፍ ባለ ስፍራ ይቀመጣል። በመንፈሳዊ አገላለጽ፥ ለእግዚአብሔር ቅርብ ይሆናል ማለት ነው። እግዚአብሔር በጽዮን ተራራ ላይ እንደሚቀመጥ ተደርጎ ተገልጾአል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ አንድ ሰው ከሌሎች በላይ ሲኖር ከእግዚአብሔር ጋር የቅርብ ግንኙነት

ስላለው እግዚአብሔር ባለበት እንደሚኖር ተደርጎ ይታያል። ይህም ሙሴ ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ጓደኛ ፊት ለፊት የመነጋገር ዕድል እንደነበረው ማለት ነው(ዘጸ. 33፡11)። በጽድቅ የሚኖሩ ሰዎች እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው ሊያጠፉዋቸው ከሚፈልጉ ጠላቶች ርቀው ይኖራሉ።

ለ. እግዚአብሔር መጠጊያ ይሆነዋል። በጥንት ዘመን እንደ ቀድሞዱቱ ኢትዮጵያ ሁሉ ዐበይት የአይሁዳውያን ከተሞች ከጠላቶቻቸው ለመጠበቅ ሲሉ በጠንካራ አምባ በታጠሩ ኮረብታዎች ላይ ይኖሩ ነበር። እንደዚሁም ጻድቅ ሰው ወደ እግዚአብሔር በመቅረብ ሊያጠቃው ከሚፈልገው ጠላት ሁሉ ይጠበቃል [መዝ. (18)፡1–3 ተመልከት]። እንዲህ ዓይነቱ ሰው ከሰዎች ተለምዶአዊ ኃጢአቶች በላይ በመኖሩና ሕይወቱን ከእግዚአብሔር ጋር በማስተካከሉ የማያቋርጥ የእግዚአብሔር ጥበቃ ይሆንለታል። እርሱን ሊያቃጥል የነበረው እሳት አሁን ጠላቶቹን ያቃጥላል።

ሐ. እግዚአብሔር መሠረታዊ ፍላጎቶቹን ሁሉ ያሟላል። መሠረታዊ የሕይወት ፍላጎቶች እንጀራና ውኃ ናቸው። ይህ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ተቀራርቦ ስለሚኖር እግዚአብሔር ፍላጎቶቹን ያሟላለታል። የዓለምን መመዘኛ የሚያረካ ብልጽግና ላይሰጠው ቢችልም፥ መንፈሳዊ በረከትን ያጎናጽፈዋል፤ ቁሳዊ ፍጆታውንም ያሟላለታል።

## ሐ. እግዚአብሔር ሕዝቡ ያለፈበትን አሠቃቂ ሕይወት እንዲዘነጋ ያደርጋል (ኢሳ. 33፡17–19)

ኢሳይያስ አይሁዶችን ወደሚመጣው የጽድቅ ንጉሥ አመልክቷቸዋል (ኢሳ. 32፡1 ተመልከት)። ምንም እንኳ ኢሳይያስ ወደ መልካሙ ንጉሥ ሕዝቅያስ እያመለከተ ሊሆን ቢችልም፥ ይበልጥ ግን ፍጹም መንግሥት ስለሚመሠርተው መሢሕ የሚናገር ይመስላል። መሢሑ ውብ የሚሆነው በአካላዊ ገጽታው ሳይሆን በባሕርያቱ የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያንጸባርቅ በመሆኑ ነው። በአካዝና በሕዝቅያስ ዘመን፥ የይሁዳ ነገሥታት እንደ ሶርያ፥ እስራኤልና አሦር በመሳሰሉት የውጭ ነገሥታት ተዋርደው ነበር። መጭው ንጉሥ ግን በአገሮች ሁሉ ላይ በሙሉ ንጉሣዊ ኃይል ይገዛል። በዚያን ጊዜ ውርደት መታሰቢያ አይኖረውም። ሕዝብ በታዛዥነት ስለሚኖር፥ የእግዚአብሔር በረከት በምድረ እስራኤል ላይ ይሆናል። የይሁዳና እስራኤል ዳርቻ በዚያን ጊዜ ከነበረበት በላይ ይሰፋል። በሌሎች የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች በመጨረሻው ዘመን የእስራኤል ዳርቻ ከኤፍራጥስ ወንዝ እስከ ግብፅ ድንበር እንደሚዘልቅ ተገልጾአል።

እግዚአብሔር በፍርሃት ተሸብበው የኖሩበትን አሠቃቂ የቀድሞ ሕይወት እንዲዘነጉ ያደርጋል። በአሦርና በባቢሎን ተማርከው

የተሠቃዩበትን ሁኔታ ይረሱታል። ጸሐፊውን፥ መዛኙንና ግንቦቹን የቆጠረውን ሁሉ ከእንግዲህ አያስታውሱም። ምናልባትም እነዚህ የአይሁዶችን ታዛዥነት ለማረጋገጥ አሦር በኢየሩሳሌም የሾመቻቸው ባለሥልጣናት ሊሆኑ ይችላሉ። ምናልባትም ጸሐፊው የአሦር መንግሥት የፖለቲካ ተወካይ (አምባሳደር) ይሆናል። መዛኙ ደግሞ ግብር እየሰበሰበ ለአሦር መንግሥት የሚያስገባው ባለሥልጣን ሊሆን ይችላል። የግንቦቹ ቆጣሪ ደግሞ የይሁዳን ንጉሥ ታዛዥነት ይቆጣጠር ዘንድ በኢየሩሳሌም የቀረ ወታደራዊ አዛዥ ሊሆን ይችላል።

ከእንግዲህ ይሁዳ በዕቡያን አሦራውያን አትገዛም። ማንም የማይረዳውን ቋንቋ የሚናገሩ አሦራውያንም በመካከላቸው አይኖሩም። አይሁዳውያን ከአሦር አገዛዝና ቁጥጥር ሙሉ ለሙሉ ነፃ ይወጣሉ። ምንም እንኳ እግዚአብሔር በቀዳሚነት የሚያስወግደው አሦራውያንን ቢሆንም፥ ኢሳይያስ የእግዚአብሔር ጠላቶች ሁሉ የሚጠፉበትን የወደፊት ዘመን አቅንቶ እየተመለከተ ነበር።

ይህም የአሦርን መንግሥት ውድቀት ባስከተለው የአሦር ሠራዊት ውድመት ፍጻሜን አግኝቶአል። ይሁንና፥ መሢሑ ለመግዛት እስከሚመለስበት የመጨረሻው ዘመን ድረስ ሙሉ ተፈጻሚ አይሆንም። በዚያን ጊዜ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች ሁሉ ይደመሰሳሉ። ፍርሃትና የእነርሱ ክፉ ትዝታም ይጠፋል። በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስ ወደ ምድር ሊመለስ ሲል በምድር ላይ የሚፈጸመውን ክፋት ስናገናዝብ ይህ በጣም አስፈላጊ ነው (ራእይ. 6–19)።

**መ. የኢየሩሳሌም ከተማ በእግዚአብሔር መሪነት በአስተማማኝ ሁኔታ ትኖራለች (ኢሳ. 33፡20–22)**

ኢየሩሳሌም ከየትኛውም የውጭ አገዛዝ ነፃ ሆና በሙሉ ደኅንነትና ብልጽግና ትኖራለች። ሃይማኖታዊ በዓሎቿን በደስታ ታከብራለች። ይህም ፍጹም ሃይማኖታዊ ነጻነትንና ሕዝበ እግዚአብሔር ከአፋቸው ብቻ ሳይሆን ከሙሉ ልባቸው እንደሚያመልኩት በማሳየት የሚከናወን ይሆናል። ኢየሩሳሌም በደስታና በደኅንነት ትሞላለች። ሰዎች የድንኳኑን ካስማ ነቅለው እንደሚገለብጡት የኢየሩሳሌም ጠላቶች ሊያሸንፉዋት አይችሉም። (ማስታወሻ፥ ምናልባትም ኢሳይያስ ሕዝቡን ከድንኳን ጋር ያነጻጸረው እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን «ፍጹም» ግንኙነት ለማመልከት ይሆናል። ይህም አይሁዳውያን በምድረ በዳ በድንኳኖች ውስጥ በሚያድሩበት ወቅት የነበረውን ሁኔታ የሚያዛምድ ይሆናል። የድንኳኑ አለመነቀል ደግሞ የምናኔ ጉዞአቸው እንዳበቃና የእግዚአብሔር ሕዝብ ከአምላኩ ጋር ለዘላለም ደስ ወደሚሰኝበት ስፍራ እንደደረሰ የሚያሳይ ሊሆን ይችላል።)

የዚህ ሁሉ ሰላምና ደኅንነት ምክንያቱ በመካከላቸው የሚኖረው አካል ማንነት ነው። «ሁሉን ቻይ» የሆነው አምላክ በመካከላቸው ይሆናል። (ኢሳይያስ ስለ መሢሑ ወይም ስለ እግዚአብሔር እየተናገረ ይሆናል።) ሁሉን ቻይ አምላክ በሕዝቡ መካከል ሰላሰ አያሌ ልዩ በረከቶች ይመጡላቸዋል።

አንደኛ፥ የእግዚአብሔር ኃይል በኢየሩሳሌም በነቦሩት ላይ ቁሳዊ በረከቶችን ያመጣል። ይህም በረከት ባለማቋረጥ ከሚፈሰው ወንዝ ጋር ተነጻጽሮአል። በፍልስጥኤም የነበረው አንዱ ችግር የውኃ አለመኖር ነው። እንዲያውም የማያቋርጥ የውኃ ፍሰት በሌለበት አካባቢ የተመሠረተች ታላቅ ጥንታዊ ከተማ ኢየሩሳሌም ብቻ ሳትሆን አትቀርም። ለዚህ ነው ብዙውን ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የእግዚአብሔር በረከት ባለማቋረጥ ከሚፈስ ውኃ ጋር የሚነጻጸረው (ራእ. 22፡1-2)።

ሁለተኛ፥ የእግዚአብሔር ኃይል ኢየሩሳሌምን ከየትኛውም ጎጂ ነገር ይጠብቃታል። ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን ጥበቃ ለማብራራት የጥንቱን ዓለም ታላላቅ የንግድ መርከቦች አመልክቷል። በአይሁድ ሕዝብ ላይ አደጋ የሚመጣበት አንዱ መንገድ ከሜዲትራኒያን መርከቦች ነበር። ብዙ ጠላቶች አይሁዶችን የሚያጠቁት ከዚያ በኩል ነበር። ወይም ደግሞ ከዚያ የሚመጡ መርከቦች ሕዝቡን ወደ ባርነት ያፈልሳሉ። እግዚአብሔር ስለሚጠብቃቸው የዚህ ዓይነቱ ሁኔታ አይቀጥልም። (ማስታወሻ፥ ምናልባትም ኢሳይያስ ለማለት የፈለገው እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ስለሚያሟላላቸው አይሁዶች ከሌሎች አገሮች ጋር የንግድ ልውውጥ እንደማያደርጉ ይሆናል።)

ኢሳይያስ እግዚአብሔር የበረከትና የጥበቃ ምንጭ መሆኑን ለማመልከት ከታወቁት ስሞቹ መካከል ጥቂቶቹን ገልጾአል።

ሀ. ሁሉን ቻይ አምላክ። (ይኼ ሐረግ በአማርኛው መጽሐፍ ቅዱሳችን ውስጥ በዚህ ክፍል አልተጠቀሰም።) የነገሮች ሁሉ ፈጣሪ የሆነው እግዚአብሔር ለሕዝቡ የሚደርሰው በረከትና ጥበቃ ምንጭ ይሆናል። (ይህ በኢሳይያስ 9 ይወለዳል ተብሎ የተተነበየው መሢሕ ከሚይዛቸው ማዕረጎች አንዱ እንደሆነ አስታውስ።)

ለ. ፈራጅ። የአይሁድ ሕዝብ ሥልጣናቸውን ተገን በማድረግ ጉቦ የሚቀበሉ ዳኞች ነበሩት። እግዚአብሔር ግን አድልዎ የሌለውና እውነተኛ ዳኛ ይሆንላቸዋል። በተጨማሪም «ዳኛ፥ መስፍን የሚለው ቃል ቀደም ሲል ሕዝቡን ነፃ ያወጡ የነበሩትን ታላላቅ ሰዎች ጭምር ሊያስታውሳቸው ይችል ነበር። እነዚህም እስራኤላውያንን ከጠላቶቻቸው ሊታደጉ የኖሩ እንደ ጌዴዎን፥ ሳምሶን፥ ዮፍታሔና የመሳሰሉት ናቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ መሢሑ ዓለም አይቶ የማያውቀው መሪ ይሆናል።

*ሐ.* ሕግ ሰጭ። ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሕጉን እንዴት በሙሴ አማካኝነት እንደሰጠ በማስታወስ አሁንም እንዴት ለእስራኤል ልጆች ይህንኑ እንደሚያደርግ ያሳያል። መንግሥት በተለወጠ ጊዜ ሁሉ ሕግጋት (ሕገ-መንግሥት) ይለወጣሉ። ሕግጋቱ የሚጻፉት ለሕዝቡ አድልዎ የሌለው ፍትሕ ለማስገኘት ሳይሆን በሥልጣን ላይ ያሉትን ሰዎች ለመጥቀም በሚያስችል መልኩ ነው። እግዚአብሔር በሚገዛበት መጪው መንግሥት የሚሰጡ ሕግጋት ግን የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቁና ለአንድ ቡድን ጥቅም የማይቆሙ ይሆናሉ። እግዚአብሔር ከሰዎች ጉቦ ስለማይቀበል ገንዘብና ሥልጣን ያላቸው ሰዎች አሳቡን ሊያስለውጡት አይችሉም። ሕግን የሚሰጠውና ተግባራዊነቱን የሚቆጣጠረው ራሱ እግዚአብሔር ይሆናል።

*መ.* ንጉሥ። ዳዊት የብሉይ ኪዳን ምሳሌያዊ ንጉሥ ቢሆንም ኃጢአትን ሠርቷል። አንድ ቀን ግን ከእርሱ እጅግ የላቀ ንጉሥ ይመጣል። እግዚአብሔር መጀመሪያ የእስራኤልን ሕዝብ በመሠረተ ጊዜ እርሱ ንጉሣቸው በመሆኑ ሌላ ንጉሥ አላስፈለጋቸውም ነበር። ሕዝቡ ግን እንደ ሌላው ሕዝብ ለመሆን ንጉሥ ስለፈለገ እግዚአብሔር እንዲያነግሡ ፈቀደላቸው (1ኛ ሳሙ. 8፥ 10፡17–19)። የሚያሳዝነው እነዚህ ነገሥታት እግዚአብሔር የበላይ ንጉሥ እንደሆነና እነርሱ ግን ከእርሱ በታች መግዛት እንደነበረባቸው ዘነጉ። ዛሬ እንደምናያቸው ብዙ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እነዚህ ነገሥታት አግባብነት በጎደለው መልኩ ሥልጣናቸውን ይዘው ለመቆየት ጥረት ያደርጉ ጀመር። ሕዝቡን እንደማገልገል ነገሥታቱ በኃይል ጨቆኑአቸው። ጻድቅ ንጉሥ በሚመጣበት ጊዜ ግን መሢሑ በፍትሕና በጽድቅ ይገዛል። ንግሥናው ፍጹም ስለሚሆን አገዛዙን የሚፈታተን ሰው አይኖርም። ነገር ግን የመሢሑ አገዛዝ ከፍቅር የመነጨ ስለሚሆን፥ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ከሁሉም የላቁትን ውሳኔዎች ያስተላልፋል።

እንዲህ ዓይነት ንጉሥ ስለሚያስተዳድራቸው ሕዝብ ሙሉ ደኅንነት (ስሜታዊ፥ አካላዊ፥ መንፈሳዊ) ያገኛሉ።

*መ.* እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከአሦር ጥቃት ያድናታል

(ኢሳ. 33፡23–24።)

ኢሳይያስ ኢየሩሳሌምን ከግዙፍ መርከብ ጋር አነጻጽሮአታል። መርከብ ለጉዞ በሚዘጋጅበት ጊዜ ሁሉም ነገር ስፍራውን ይይዛል። ዕቃዎች ሁሉ ተጭነው ያልቃሉ። ደቀሎች፥ ገመዶችና መቅዘፊያዎች ሁሉ ለጉዞው ዝግጁ ይሆናሉ። የኢየሩሳሌም ሁኔታ ግን የዚህ ተገላቢጦሽ ነበር። እነዚያ ሁሉ መርከቦች በአቅራቢያዋ ስለሌሉ ከአሦር ጋር ጦርነት ለመግጠም እንዳልተዘጋጀች ግልጽ ነው። ነገር ግን ከመቅጽበት ነገሮች ተለውጠው አሦር ትሸነፋለች። ሕዝቡ የሠራዊቱን ንብረት ይበዘብዛል። ሰዎች ሁሉ በተማረከው ሀብት

ስለሚደሰቱ፥ ሩጦ ለመሰብሰብ የማይችል አንካሳ ሳይቀር የሚፈልገውን ሁሉ ያገኛል።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ መሥራቱ ጠላቶቻቸውን በመፍራት እንዳይታመሙ ያደርጋቸዋል። እንዲሁም ደግሞ የኃጢአታቸውን ይቅርታ አግኝተው ከእግዚአብሔር ጋር በኅብረት ይኖራሉ።

ይህንን ምዕራፍ ለመረዳት አስቸጋሪ የሚያደርገው ኢሳይያስ ሕዝቡ አሦርን እየተጋፈጠ ከነበረበት ሁኔታ ወደ መጨረሻው ዘመን የሚሻገር መሆኑ ነው። ይህም እግዚአብሔር ከአሦራውያን የሚያወጣቸው ነጻነት ጊዜያዊ ብቻ እንደሆነ የሚያውቅ ያስመስለዋል። ያ ነጻነት ግን መሢሑ በሚመጣበት ጊዜ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከሚሰጠው የመጨረሻው ነጻነት ጋር ሲታይ በጣም አነስተኛ ነበር። በዚያን ጊዜ የዓለም ችግሮች ሁሉ ይወገዳሉ። እግዚአብሔር በሕዝቡ መካከል ሆኖ የጽድቅ አገዛዙን፥ ጥበቃውንና በረከቱን ያጎናጽፋቸዋል። የእግዚአብሔርም ሕዝብ ተለውጦ የእርሱን ባሕርይ በሚያንጸባርቅ መንገድ ይኖራል። ምንም እንኳ ኢሳይያስ እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ከአሦር ነፃ በሚያወጣበት ጊዜ እንዲህ ዓይነቱ መንግሥት እንዲመጣ ቢመኝም፥ እስከ ዘመን መጨረሻ ድረስ የሚዘገይ መሆኑን ያውቅ ነበር።

37ኛ ጥያቄ፡– ከዚህ ምዕራፍ ያገኘሃቸውን ጠቃሚ መንፈሳዊ ትምህርቶች ዘርዝር።

**አራተኛ ቀን፤ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ስብሰባ ለመዘጋጀት የመወያያ ጥያቄዎችን ተመልከት።**

## ሳምንታዊ ስብሰባ

### የመወያያ ጥያቄዎች

1. ሀ) እግዚአብሔር በኢሳይያስ 28–29 የእስራኤልን ኃጢአት በመግለጥ የሚያጋፍጣት እንዴት ነው? ለ)የሰጡዋቸው የተሳሳቱ ምላሾችና የምላሾቻቸው ውጤቶች ምንድን ናቸው? ሐ) እግዚአብሔር ንስሐ ለመግባት ለሚፈልጉ ሰዎች የሰጣቸው የበረከት ተስፋዎች ምንድን ናቸው) መ) ዛሬ ለመንፈስ ቅዱስ ድምፅ ሰዎች ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉባቸው የተሳሳቱ መንገዶች የትኞቹ ናቸው? የእንደ እነዚህ ዓይነት ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት የመጨረሻው ውጤት ምንድን ነው? ሠ) የእግዚአብሔር ቃል እንደሚለው፥ ከኃጢአታችን ብንናዘዝ ምን እናገኛለን? ረ) በባዶ ቃላት በታጠረው የውሸት ንስሐና የሕይወት ለውጥ ባለው እውነተኛ ንስሐ መካከል ያለውን ልዩነት እንዴት እናውቃለን?

2. ሀ) ኢሳይያስ የካህናቱንና የነቢያቱን መንፈሳዊ ሕይወት የሚገልጸው እንዴት ነው? ለ) የካህናትና የነቢያት ተግባር ምን ሊሆን

ይገባ ነበር? ለካራምነትን በተያያዙ ጊዜ ምን ተከሰተ? ሐ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በግብረገባዊ ወይም በመንፈሳዊ ጎጢአት ከመውደቃቸው የተነሣ የእግዚአብሔርን ቃል ለሌሎች ለማካፈል ወይም ለራሳቸው ለመስማትና ለመረዳት የማይችሉባቸውን ሁኔታዎች ግለጽ። መ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ለዚህ ዓይነቱ ጎጢአት እንዳይዳረጉ ምን ማድረግ አለባቸው?

3. ሀ) ኢሳይያስ እግዚአብሔርን ከማዕዘን ድንጋይ ጋር ሲያነጻጽር ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት ምንድን ነው? ለ) አይሁዶች ደኅንነታቸውን ሊመሠርቱበት የፈለገው የማዕዘን ድንጋይ ምን ነበር? ውጤቱ ምን ነበር? ሐ) ዛሬ ሰዎች ሕይወታቸውን ለመገንባት የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ የማዕዘን ድንጋዮች ምንድን ናቸው? የመጨረሻው ውጤት ምንድን ነው? መ) ኢየሱስ ክርስቶስ ለችግሮች ዘላቂ መፍትሔና ደኅንነት የሚያስገኝ ብቸኛ የማዕዘን ድንጋይ የሆነው በምን መንገድ ነው?

4. ሀ) በኢሳይያስ 29፡9–14፥ ኢሳይያስ አይሁዶች እግዚአብሔርን ሰምተው ንስሐ በመግባት ሕይወታቸውን ለመለወጥ ባለመፈለጋቸው ምን እንደሚደርስባቸው ተናገረ? ለ) ዛሬስ እግዚአብሔርን ላለመስማት ልባቸውን በሚያደነድኑት ሰዎች ላይ ተመሳሳይ ፍርድ የሚመጣው እንዴት ነው? ሐ) ክርስቲያኖች ከልባቸው ሳይሆን በሰው ሥርዓት እግዚአብሔርን የሚያመልኩባቸውን መንገዶች ዘርዝር። መ) አምልኮ ከቃላት እንደሚልቅና ከልብ የሚመነጭ መሆኑን ለማረጋገጥ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ምን ሊያደርጉ ይችላሉ?

5. ሀ) ሕዝቅያስ ያደረገው ቃል ኪዳን ምንድን ነው? ለምን? ለ) ይህ ቃል ኪዳን ለአይሁዶች ያስከተለው ውጤት ምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ቃል ኪዳኑን ያልወደደው ለምንድን ነው? መ) ክርስቲያኖች እግዚአብሔርን የማያስከብሩ ቃል ኪዳኖች የሚያደርጉት እንዴት ነው? ሠ) የተሳሳቱ ቃል ኪዳኖች ስለ እምነታችን የሚያሳዩት ነገር ምንድን ነው? ረ) ክፉ ባልንጀርነትና የተሳሳተ ቃል ኪዳን በእምነታችን ላይ የሚያስከትላቸው ተጽዕኖዎች ምንድን ናቸው? ሰ) ከኢሳይያስ 30 እንደምንመለከተው፥ ሰዎች የሚታመኑባቸው ሁለት ቅጥሮች ምንድን ናቸው? ሸ) ለአይሁዶች (እና ዛሬም ለእኛ) እውነተኛው የደኅንነት ምንጭ ምን እንደሆነና ያንኑ ደኅንነት ለማግኘት ምን ማደረግ እንደነበረባቸው ግለጽ።

6. ሀ) በመጨረሻው ዘመን የእግዚአብሔር ሕዝብ የእግዚአብሔርን ማንነት የሚያንጸባርቅ ምን ዓይነት ባሕርይ ይኖራቸዋል? (ኢሳ. 32)። ለ) ዛሬ በመንፈስ ቅዱስ እርዳታ እነዚህን ባሕርያት ማንጸባረቅ የሚኖርብን እንዴት ነው? ሐ) ብዙ ክርስቲያኖች እነዚህን ባሕርያት የማያንጸባርቁት ለምንድን ነው? መ) በአብያተ ክርስቲያናችን ሰዎች

እነዚህን ባሕርያት እንዲያሳድጉ ለማድረግ እንዴት ልናግዛቸው እንችላለን?

7. ሀ) ሕዝበ እግዚአብሔር ነፃ ለመውጣት በእግዚአብሔር እንዲታመኑ ለማበረታታት በተሰጠው በኢሳይያስ 33 ኢሳይያስ እግዚአብሔርን የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ክርስቲያኖች በመከራ ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ማወቅ የሚያበረታታቸው እንዴት ነው? ሐ) በሕይወት ትግል ላይ በምንሆንበት ጊዜ የሚያጽናኑንን የእግዚአብሔር ባሕርያት ዘርዝር።

8. ሀ) ከኢሳይያስ 30፥ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ያለውና እግዚአብሔርን እርሱ በሚፈልገው መንገድ የሚያመልከው ሰው ምን ዓይነት እንደሆነ ግለጽ። ለ) ለኢትዮጵያ ክርስቲያኖች ከእነዚህ ነገሮች በጣም ከባድ የሚሆኑት የትኞቹ ናቸው? ለምን? ሐ) ሰዎች በዚህ ዓይነት ሁኔታ በማይኖሩበት ጊዜ በቤተ ክርስቲያን፥ በአገርና በግለሰቦች ላይ የሚያስከትለው ተጽዕኖ ምንድን ነው?

9. ሀ) ኢሳይያስ እነዚህን ምዕራፎች በሚጽፍበት ወቅት አይሁዶች የነበሩበትን ሁኔታ ግለጽ። ለ) ኢሳይያስ በአስቸጋሪ ጊዜ በእግዚአብሔር ስለ መታመን አስፈላጊነት ያስተማራቸው ጠቃሚ ትምህርቶች ምንድን ናቸው? ሐ) እግዚአብሔር ስለ ወደፊት ሕይወታቸው ለአይሁዶች የሰጣቸው የተስፋ ቃሎች ምንድን ናቸው? መ) ከእነዚህ ምዕራፎች እግዚአብሔርን በሚያስደስት መልኩ ስለ መኖር ምን ምን ትምህርቶችን እናገኛለን?